# ምዕራፍ ሐያ አራት

## የኢትዮጵያና የመስኮብ ግንኙነት

ምኒልክ በአንኮበር ካባታቸው ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ጋር ካሳለፉት ያሥር ዓመት እድገታቸው ዘመን ይልቅ ፣ በጐንደር በደብረ ታቦር ባፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ያሳለፉት ያሥር ወይም የዐሥራ አንድ ዓመት ዘመን ብዙ ትምህርት የሰጣቸው ይመስላል ። በ1857 ዓ.ም በ21 ዓመታቸው ከመቅደላ አምልጠው ወደ አንኮበር ሲመለሱ ፣ ከፉና በጐን በመለየት ካፄ ቴዎድሮስ ደገኛውን ወገንና አገር የማሠልጠኑን ስሜት ወርሰው ተመልሰዋል ።

ያፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዞች ፣ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ባፄ ዮሐንስ መሸነፍ ፣ የርሳቸውም በ1870 ዓ.ም. ላፄ ዮሐንስ መገበር መሠረታዊው ምክንያት ፣ በጦር መሣሪያ ብዛትና ጥራት ልዩነት መሆኑ በትክክል ገብቷቸዋል ። የጐራዴ ፣ የሰይፍ ፣ የካራ ፣ የጩቤ ፣ የጦርና የጋሻ መሣሪያነት ጊዜው ያለፈበት መሆኑና ላሉበት ዘመን እምብዛም እንደማያገለግል ተረድተዋል ። በነዚህ ፈንታ ከጠላት ለመከላከል ወይም ጠላትን ለማጥቃት ፣ ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ዙፋን ለመውጣትና በዚያም ለመቆየት ፍቱን መፍትሔው በባሩድና በጥይት ተተኳሹ ዘመናዊው ጠበንጃና መድፍ መሆኑን በደንብ ተገንዝበውታል ።

ስለዚህም ፣ ከሁሉ በፊት የመሣሪያዎቹ ባለቤት ከሆኑት ከአውሮፓ መንግሥታት መሪዎች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ለማድረግ ፣ በቅድሚያ የነዚህን አገር የተለያዩ ዜጐች ባጠገባቸው አስቀምጠው መንከባከብን ሥራዬ ብለው ተያያዙት ። ቀጥሎ በነዚህ ወዳጆቻቸው አማካይነት ወርቅና የዝሆን ጥርስ እየላኩ በመዠመሪያ ከኢጣልያ በወዳጅነቱ ዘመን ፣ ቀጥሎ ከኢጣልያ ጋር ወዳጅነቱ ወደ ጠብ ስለ ተለወጠ በነሙሴ ኢልግ ፣ በነሙሴ ሸፍነና በነሳቡሬ አማካይነት ከፈረንሳይ መንግሥት የጦር መሣሪያ በግዥ መሰብሰባቸውን ባለፈው አንብበናል ።

ከነዚህ ከወዳጅ አገሮች አንዱ ፣ የመስኮብ መንግሥት ሆኖ ተገኝቷል ። ይህ አውሮፓዊና እስያዊ መንግሥት በአፍሪካ ዙሪያ ምንም ዓይነት ቅኝ አገር ስለሌለው ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም እንኳን ካፄ

ዮሐንስ ዘመን ዠምሮ ከሁለቱም ወገን የግንኙነት ፍላጎት ባይጠፋ በቅድሚያ በቱርኮች ፣ ቀጥሎም በእንግሊዞች ተጽእኖ ሥጋት ስለነበር ግንኙነቱ እየተወጠነ መልሶ ሲቋዘቅዝ ቆይቶ ነበር ። አሁን ግን ፣ የኢጣልያ አጥቂነት ፣ የእንግሊዝ ተባባሪነት እየተጫጫነ በሚሔድበት ጊዜ ፣ የኢትዮጵያ ወዳጆች መስለው የቀረቡት ፈረንሳይና መስኮብ ናቸው ። ለመስኮብ ወዳጅነት ወጣኞቹ አቺኖቭ ኒኮላይ ኢቫኖቪችና ማሽኮብ ባሲሊ የተባሉት የጦር መኰንኖች ፣ እንደዚሁም ኤፍሬም የሚባሉት የቤተክህነት ሰው ናቸው ። ከነዚህ ሁሉ የበለጠ ካፄ ምኒልክ በመተዋወቅና በመወዳጀት ለመስኮብና ለኢትዮጵያ መቀራረብና መወዳጀት ዋና አማካይ የሆነው ሊዎንቴቭ ኒኮላይ ስቲቫኖቪች የሚባለው የጦር መኰንን ነው ። እሱም ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ፣ የእስክንድር ምርጥ የክብር ዘበኛ መኰንን ነበር ። እንዳንዶቹ ኰሎኔል ፣ ብዙዎቹ ኮንት ሊዎንቴቭ እያሉ ስለሚጠሩት ፣ የቤተሰቡ ደረጃ ከመሳፍንቱ ዝቅ ያለ ፣ የባላባትነት ደረጃ ጭምር ነበረው ማለት ነው ። ይኸንንም የኮንት ሥያሜ እንዲጠራበት ከኒሻን ሽልማት ጋር ዐፄ ምኒልክ በደብዳቤ የምስክር ወረቀት ፈቅደውለታል ።*

ኮንት ሊዎንቴቭ ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፣ ከመስኮብ ወደ አዲስ አበባ ፣ ከዚህም ወደዚያ እየተመላለሰ ፣ ሁለቱ መንግሥታት የሚጠቃቀሙበትን መንገድ ያከናውን ነበር ። የመስኮቡን ንጉሠ ነገሥት የሣልሳዊ እስክንድርንና እሳቸው እ. ኤ. አ. በ1894 ዓ. ም. ከሞቱ ወዲህ የልጃቸው የዳግማዊ ኒኮላን አሳብና ምኞት ላፄ ምኒልክ ፣ የምኒልክን አሳብና ምኞት ላገሩ ንጉሠ ነገሥት እየገለጠ የበለጠ አቀራርቧል ። ኒሻኑን የተሸለመውና ኮንት የተባለውም ከዚህ አገልግሎት በኋላ ነው ። የመቀራረቡ ዓላማ የፖለቲካና የጥቅም ጉዳይ ባይጠፋበትም ፣ ዋናው ሁለቱን ያቀራረባቸው ኦርቶዶክሳዊ የክርስትና ሃይማኖት ተመሳሳይነት ነው ። የነዚህንም ሁለት አገሮች ግንኙነት የእንግሊዝና የኢጣልያ የፖለቲካ ባላጋራ የነበረው ፈረንሳይ በመልካም ዐይን ተመልክቶታል ። የኢጣልያ መንግሥትና ከርሱ ጋር ተባባሪ የሆነው የእንግሊዝ መንግሥት ግን ፣ በክፉ ዐይን በመመልከት ግንኙነቱን ለማሰናከል ከመጣር አላረፉም ።

ስለዚህ ፣ በዚህ የኢጣልያኖች አጥቂነት በከፋበት ሰዓት ፣ ሊዎንቴቭ ካፄ ምኒልክ ተልኮ በመስኮብ አገር የኢትዮጵያን ጉዳይ ሲነጋገር

* ሞዓ አንበሳ . . .ዳግማዊ ምኒልክ . . . ከመስኮብ መንግሥት ተልኮ መጥቶ የኔን መንግሥት በመልካም ስላገለገለ ወዳጃችንን ሙሴ ሊዎንቲፍን በኒሻናችን አከብረን . . . ስለ ማገልገሉ ኮንት ብለነዋል ። በሰኔ 4 ቀን 1888 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ።



ከሰነበተ በኋላ ፣ በ1887 ዓ.ም. ሌሎች መስኮቦች አስከትሎ በጥር ወር ላይ ፣ በጅቡቲ በኩል ወደ ሐረር መጓዛቸው ተሰማ ። ንጉሠ ነገሥቱ ፣ “ አክብረህ ተቀብለህ ወደኔ ላካቸው” የሚል አስቸኳይ ደብዳቤ ለራስ መኰንን ላኩ ። መልክተኞቹም ከሐረርጌ በአዋሽ በኩል ፣ በየረርና በከረዩ አድርገው ምንጃር ሲደርሱ ፣ መልካም አቀባበልና መስተንግዶ እየተደረገ ፣ በየካቲት ወር ላይ አዲስ አበባ ሲደርሱ ከሁሉም የበለጠ ያክብሮትና የወዳጅነት አቀባበል ተደርጎላቸው ሰነበቱ ።[1]

የመስኮብ መንግሥት መልክተኞች በኮንት ሊዎንቴቭ መሪነት መጥተው ስጦታውንም ፣ የወዳጅነት ደብዳቤውንም አቅርበው ሲወያዩና ሲመካከሩ ከሰነበቱ በኋላ ፣ በዚህ በኮንት ሊዎንቴቭ አማካሪነት አንድ የኢትዮጵያ የመልእክተኛ ጓድ ወደ ፒዮትሮቡርግ* እንዲላክ ታስቦ ተወሰነ ። በተለይ አሁን የኢጣልያኖች አጥቂነት እየተጫነ ሲሔድ ከፈረንሳይ በተጨማሪ የመስኮብንም ወዳጅነት ማግኘቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆነ ። በመዠመሪያ ላይ የመልእክተኞቹ መሪ የሚሆነው ሲመረጥ ፣ ምርጫው ከሊቀ መኳስ አባተ ቧያለው ላይ ወድቆ ነበር ። በኋላ ግን ፣ አባተ ቀርተው ለዚህ መልእክት ፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ ተመረጡ ። ከርሳቸውም ጋር ቀኛዝማች (በኋላ ደጃዝማች) ገነሜ ፣ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ፣ ልጅ በላቸው ፣ አቶ ዮሴፍ (አስተርጓሚ) ፣ ልጅ ረዳ (የሊዎንቴቭ አስተርጓሚ) ተመደቡ ።

ፊታውራሪ ዳምጠው** አቋቋማቸው ያማረ ፣ ንግግራቸው የሚጥም ፣ የሸዋ ተወላጅ መሆናቸውን ጸሐፊው ሁሉ ስለሚጠቅስ ፣ ምናልባት ለዚህ የመልእክት መሪነት ያስመረጣቸው ይኸው ያቋቋምና የመልክ ማማር ይሆናል ። ሊቀ መኳስ አባተ ያፄ ምኒልክ ዋና ባለሟል ቢሆኑም ፣ ብልህነታቸው ቢነገርም ፣ የሰውነታቸው አጠር ቀጠን ማለት አስቀርቷቸው ይሆናልና ወይም ባሁኑ ጊዜ ወደፊት ከኢጣልያኖች ጋር ውጊያው እንደማይቀር ስለታመነ ከፈረንሳይም ፣ ከሌላም አገር ከመጣው አዳዲስ ጠበንጃና መድፍ ጋር የጦር ሠራዊቱ ከመለማመድ ላይ ስለሚገኙ ፣ ለዚህ ቴክኒካዊ ተግባርና የጦር መሣሪያ ልምምድ ያባተ መጉደል ይጐዳል ተብሎ ይሆናል ።

በመስኮብ አገር አባትየው እስክንድር ሞተው በዙፋን ላይ ለወጡት ልጃቸው ለዳግማዊ ኒኮላና ለባለቤታቸው የሚቀርበው ገጸ በረከትና

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 59 ።
Chronique du Regne de Menelik II . . .M. de Coppet. Vol 1, PP 369 - 370.

* ከሞስኮ በፊት የነበረው ዋና ከተማ አሁን ሌኒንግራድ የሚባለው ነው ።

** የራስ ደስታ አባት

ደብዳቤ ሲዘጋጅ ሰነበተ ። የግጸ በረከቱን ዓይነት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ዕፁብ ድንቅ የሆነ ዘውድ ፤ ማስፌያ የወርቅ መስቀል ፤ አርባዕቱ ወንጌል መጽሐፍና ሌላም የኢትዮጵያ ብዙ ዕቃ ፤ ንግሥቲቱም እቴጌ ጣይቱ ለመስኮብ ንግሥት (አሌክሳንድራ) በረከት (ስጦታ) የሚሔድ ዕፁብ ድንቅ የተባለ በወርቅ አጫዋች ያጌጠ የሐር መሶብ ፤ የሴት ወይዘሮ መጫሪያ የወርቅ የእግር ከታብ ፤ወርቅ አልቦ ጠልሰም ፤ ወርቅ ድሪ ፤ ወርቅ ወለባ . . .[1] መሆኑን ገልጸውታል ። ካፄ ምኒልክ የተላከው ደብዳቤም እንደዚህ የሚል ነው ።

ይድረስ ከክቡር ወልዑል ቄሣር ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ኒኮላ . . .

ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን ። ከርስዎ ዘንድ የተላኩ መነኩሴና መኳንንቶች በደህና ደረሱ ። እኛም በክብርና በደስታ ተቀብለናቸው የክቡር አባትዎን ሞት ሰምተን እጅግ አዝነን ነበር ። እርስዎ በእግዚአብሔር ፈቃድ በሕዝብዎ መውደድ ባባትዎ ዙፋን መቀመጥዎን ሰምተን በጣም ደስ ብሎናል ። ግዛትዎና ዕውቀትዎ እየበዛ እየተረፈ እንዲሔድ እጅግ ተስፋ አለን ። ያባትዎን የጥንት ፍቅርና ወዳጅነት አለመርሳታችንን ለማስታወቅ ኃዘንዎና ኃዘናችን አንድ ዘንድ እንዲተባበር ብለን ከንጉሠ ነገሥት (እስክንድር) መቃብር ላይ የሚደረግ የኢትዮጵያ ዘውድ ሰደናል ። ከዘውዱም ጋራ የታመኑ ሰዎቻችንን ሰደናል ። ዳግመኛም የክርስቲያን ሃይማኖት እርቶዶክሳዊት ወንድሞቻችሁ መሆናችንን የሚያስረዳ ፍቅራችንንም የሚያሳይዎ ወንጌልና የወርቅ መስቀል ልከናል ። እርስዎም በክቡር (አክብረው) እንዲቀበሉን ተስፋ አለን ። ክቡር አባትዎ ዊክቶር (ቪክቶር) ማሽኮፍን ወደኛ የላኩ ጊዜ የጻፉልኝን የፍቅር ደብዳቤያቸውን ቃል እርስዎም እንዳይረሱ እናውቃለን ። ዕድሜዎን እንዲያራዝም መንግሥትዎን የእርቅ የሰላም አድርጎ እንዲያስነብትዎ ፤ መልካም አሳብዎን ሁሉ እንዲፈጽምልዎ ይልቁንም ክርስቲያን በመርዳትዎ እንዲጠብቅዎ ልዑል እግዚአብሔርን እለምናለሁ ። በሚያዝያ በ22 ቀን ባዲስ አበባ ከተማ በ1887 ዓ.ም. ተጻፈ ። [2]

የኢጣልያ መንግሥት ፤ በውጫሌ ውል በማታለል አጭበርብሮ ያገባውን ያሥራ ሰባተኛውን አንቀጽ እየጠቀሰ ፤ "ኢትዮጵያ በኔ ቁጥጥር ሥር ስለሆነች በኔ በኩል ካልሆነ በቀር ከማንም መንግሥት ጋር በቀጥታ መነጋገርም መዋዋልም አትችልም" በማለት አሁንም ከመስኮብ መንግሥት ጋር የምታደርገውን ግንኙነት ከመቃወም ላይ ይገኛል ። ሁኔታውንም ሌሎች ኢጣልያኖች ሲባረሩ ፤ በመሐንዲስነትና

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ምዕ 59 ፤ ገጽ 223 - 224 ።

2 ከቤተ መንግሥት መዝገብ የተገኘ ደብዳቤውን የገለበጠው እበበ ይባላል ። ዓመተ ምሕረቱና ወሩ የተጻፈው በአማርኛ ነው ።



በአናጢነት ስለ አስደሰታቸውና ቤተ መንግሥቱን ስለሠራ ፤ ምኒልክ ወደው ባስቀሩት በእንጂኒየር ሉዊጂ ካፑቺ አማካይነት በዝርዝር ተረድተውታል ።

እርሱም ፤ ዐፄ ምኒልክ በወዳጅነት ከሚያደርጉለት አስተያየትና ቸርነት ያገኑ ጉዳይ ስለባሰበት ፤ ወደርሱ የቀረቡትን በተለይ አስተርጓሚውን የልጥ ማረፊያውን አቶ ዮሴፍን በገንዘብና በመጠጥ እያባበለ ፤ በካቶሊክ የሃይማኖት አንድነት እየተጠቀመ ፤ ምስጢር የሆነውን ሁሉ ከርሳቸው በመረዳት በምስጢራዊ የቁጥር ቃል እያደረገ ወደ አሰብ ፤ ወደ አሥመራም ፤ ወደ ሮማም ይልካል ። አሁንም የዮሴፍ የመልክተኞቹ አባል ሆነው ሲቆጠሩ ፤ "አይሆንም እርሱ ልክ ኢጣልያዊ ነው" ብለው ራስ መኰንን አሳስበው ነበር ይባላል ።

በእርግጥ ፤ መላክተኞቹ ከአዲስ አበባ ከመነሣታቸው በፊት ይኸው ካፑቺ ፤ "ዮሴፍ መልካም ሰላያችን ስለሆነ ሁሉንም ነገር ከርሱ ትረዳላችሁ" የሚል የቁጥር ቃል በቁጥር 95 እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 26 ቀን 1895 ዓ.ም ወደ ካይሮም ፤ ወደ ሮማም ለባለሥልጣኖቹ ማስተላለፉን ካርሎዛጊ በመጽሐፋቸው ጠቅሰውት[1] ይገኛል ። በዚሁ መሠረት የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ፒዮትሮቡርግ ለሚገኘው ሲልቬስትሬሊ ጁሴፒ ለሚባለው ጉዳይ ፈጻሚያቸው ፤ መልክተኞቹ መስኮብ ከተማ ከደረሱ ዠምሮ በዮሴፍ አማካይነት ጉዳዩን በጥብቅ እንዲከታተል ትእዛዝ አስተላልፈውለት ነበር ። ነገር ግን የኢትዮጵያ መላክተኞች በመስኮብ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ ጉዳይ ፈጻሚው በብዙ ረገድ ዮሴፍን ለመገናኘት ቢፈልግም ዮሴፍ እጠረጠራለሁ ብለው በመፍራት ሊገናኙት አልፈለጉም ።[2]

መልክተኞቹ ከአዲስ አበባ በ1887 ዓ.ም. ግንቦት ወር ላይ ተነሥተው ፤ በሐረር በኩል አድርገው ፤ ጅቡቲ ገብተው ትንሽ እንደቆዩ በሰኔ ወር መዠመሪያ ላይ ከጅቡቲ ሜሳጀሪ ማሪቲም (ኢራባዲ) በሚባለው የፈረንሳይ መርከብ ተሳፍረው ፖርት ሳይድ ደረሱ ። ከዚያም ቺዛሬቪች ወደሚባለው የመስኮብ መርከብ ተዛውረው እ.ኤ.አ. በ29 ሰኔ ኦዲሴያ ሲደርሱ ፤ በዚያ ያለው አገረ ገዥ ፤ የሲቪልና የጦር ሹማምንቱን አስከትሎ ከፍ ያለ የክብር አቀባበል አደረገላቸው ። በሐምሌ 1 ቀን ከኦዲሴያ ተነሥተው ፤ በባቡር ተጉዘው ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት መናገሻ ከተማ ወደ ፒዮትሮቡርግ እስኪደርሱ

---

1 I Russi in Etiopia, C. Zaghi. PP. 109 - 110, 171.

2 I Russi in Etiopia, PP., 171 - 172.

በየመንገዱ ፣ በየከተማው የተደረገላቸው የጋለ አቀባበል ከፍ ያለ የወንድማማችነት መሆኑን በዘመኑ የነበሩት ጸሐፊዎች መዝግበውታል ።

ፒዮትሮቡርግ ከተማ ሲገቡ ፣ የከተማው ከንቲባ ራትኮቭ ራጐቭ የጦሩ አዛዥ ዤኔራል ቴምፌቭ ፣ የቀሩትም መኳንንትና ሹማምንት የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ፣ የከተማውን ሕዝብ አሰልፈው ተቀበሏቸው ። ቀጥሎም በቀጥታ የቅዱስ ጴጥሮስን ካቴድራል ተሳልመውና የሟቹን ንጉሥ መቃብር ጐብኝተው ፣ በመቃብሩ ላይ እንደ ደንቡ የተዘጋጀላቸውን ያበባ ጉንጉንንና ከአዲስ አበባ ይዘው የመጡትን የወርቅ ዘውድ አስቀመጡ ። ከዚያ የአውሮፓ ሆቴል ወደሚባለው ትልቅ ማረፊያ ወስደው እንደ የማዕረጋቸው ክፍል ሰጥተው አስቀመጧቸው ። ባሉበትም ሆቴል የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ፣ የግልም ሰዎች እየመጡ የወንድምነታቸውን ስሜት በፍቅርና በወዳጅነት መልክ ገለጡላቸው ። ከዚህ በኋላ በሐምሌ 7 ቀን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሉቫኖቭ ርስቶቭስኪ የሚባለው መስፍን ፣ ከዚያም አከታትለው የፍርድ ፣ ያገር ግዛት ፣ የገንዘብ ፣ የመገናኛ ፣ የጦር ሚኒስትሮችና የፈረንሳይ አምባሳደር እየተቀባበሉ ሲያነጋግሯቸው ሰነበቱ ።

በዚሁ ጊዜ ፣ የታላቁ የቅዱስ ሲኖዶስ መሪ ፓቤደኖሺቭ ኮንስታንቲፒትሮቪች የሚባሉት በቅድሚያ ወዳረፉበት ሆቴል ሔደው ከነፊታውራሪ ዳምጠው ጋር ተዋውቀው በወዳጅነት ሲጫወቱ ቆዩ ። ቀጥሎም ወደ መኖሪያ ቤታቸው መልከተኞቹን በሙሉ ወስደው ፣ ምሳ ጋብዘው ሲጨርሱ ባደረጉት ዲስኩር ለምኒልክ ምስጋና ከማቅረብ ጋር የሃይማኖት ወንድሞቻቸውን ኢትዮጵያውያንን በመቀበላቸው መደሰታቸውን ጠቅሰው ፣ "ኢትዮጵያ በልማት እያበበች ፣ በኃይል እየጠነከረች ፣ ሃይማኖቷንና አገሯን እንድትጠብቅ "[1] ያላቸውን የጋለ ምኞት ገልጸውላቸዋል ።

ይኸ ሁሉ ከሆነ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ኒኮላ መልክተኞቹን በቤተ መንግሥታቸው የሚቀበሉበት ቀን እ.ኤ.አ. ሐምሌ 13 ቀን 1895 እንዲሆን ተወሰነ ። ሹማምንቱ መልከተኞቹ ወዳረፉበት ሆቴል ሔደው በመዠመሪያ ለዋናው መልክተኛ ለፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ በስድስት ታላላቅ ነጫጭ ፈረሶች የሚሳብ በጣም ያጌጠ ወርቅማ ሠረገላ ቀረበላቸው ፤ ሁለተኛው በአራት ፈረስ የሚሳበው ሠረገላ ለአባ ገብረ እግዚአብሔር ፣ ሦስተኛው በሁለት ፈረሶች የሚሳበው ለቀኛዝማች ገነሜና ለልጅ በላቸው ፣ ከነርሱም ኋላ ኢትዮጵያን

I I Russi in Etiopia, C. Zaghi PP. 143 - 149.



የሚያውቁ ልዩ ልዩ የመስኮብ ሰዎችና ተራ ኢትዮጵያውያን ተቀምጠዋል ። ከነዚህም መካከል ለዚህ ግንኙነት በጣም የተጣጣረው ኮንት ሊዎንቴቭ ይገኛል ።

ጉዞው ካረፉበት አውሮፓ ሆቴል ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲያመራ ፣ ግራና ቀኝ የተሰለፈው ሕዝብ በሆታና በጭብጨባ እየተቀባበለ በመሸኘት ከቤተ መንግሥቱ በራፍ ደረሱ ። በዚያም የቤተ መንግሥቱ የፕሮቶኮል ሹምና ዋናው ጸሐፊ ከተቀበሏቸው በኋላ ፣ ወደ ቤተ መንግሥቱ ዘልቀው በቅድሚያ የጐበኙት የሟቹን የእስክንድር ሣልሳይን ባለቤት ፣ የንጉሠ ነገሥቱን እናት ማሪያን ቤዶሮቭናን ነው ። ከዚያ ንጉሠ ነገሥቱ ኒኮላ በአጃራሻቸው ሆነው ወደሚጠብቋቸው ተመርተው ሔደው ፣ እጅ ነሥተው ፣ ዋናው መልክተኛ ፊታውራሪ ዳምጠው ንግግር አደረጉ ። ፊታውራሪው በንግግራቸው አስፋፍተው የገለጹት ዐፄ ምኒልክ በደብዳቤያቸው ላይ ያመለከቱትን ሲሆን ፣ ለዚህ መልእክት የበላይ ሆነው የንጉሠ ነገሥታቸውን የወዳጅነት ደብዳቤ ለመስኮቡ ንጉሠ ነገሥት ፣ የእቴጌ ጣይቱን ደብዳቤ ለንግሥት አሌክሳንድራ ቢዶሮቭና ለማድረስ በመቻላቸው መደሰታቸውንና ምንም እንኳን ስለ ሣልሳይ አሌክሳንድር ሞት ቢያዝኑም ፣ ስለኒኮላ መንግሥ ምኒልክ የተሰማቸውን ደስታና መልካም ምኞት ገልጸዋል ።

በዚሁ ጊዜ ፣ ቀድሞ ለራሳቸው በወርቅና በአልማዝ ተጊጦ ለተላከላቸው ኒሻን አጸፋ ፣ ዐፄ ምኒልክ ለንጉሠ ነገሥት ኒኮላ የላኩትን በወርቅና በጌጣጌጥ አምሮ የተሠራውን ባንገት የሚጠለቀውን የሰሎሞን ኒሻን ከምስክር ወረቀቱ ጋር አስረከቡ ። በበኩላቸው መምህር ገብረ እግዚአብሔር የወርቁን መስቀልና አርባዕቱን ወንጌል ከቡራኬና ከመንፈሳዊ አነጋገር ጋር አቀረቡ ። በዚህ ጊዜ ሁሉ ኮንት ሊዎንቴቭና ጓደኞቹ ፣ ታላላቅ የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አልተለዩም ።

በዚህ ዓይነቱ አቀባበል ፣ በንዴት ሆዳቸው የበሸቀው የኢጣልያ ዋና ጉዳይ ፈጻሚ ሲኞር ሲልቬስትሬሊ ጀሴፔና ጓደኞቹ ናቸው ። የፈረንሳዩ ሚኒስትር ሞንቴቤሉላን ጉስታቭ ፣ ሉዊ ሐኖቶ ለሚባለው የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲጽፍ ፣ "ሲልቬስትሬ በኢትዮጵያውኑ ጉብኝትና በተደረገላቸው የጋለ አቀባበል ተበሳጭቶ ፣ ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ፣ አነጋገሩ ሁሉ አንድ የውጭ አገር ዲፕሎማት ካለው የለዘበ ዲፕሎማሲያዊ አነጋገር የወጣ ነበር"[1] ሲል እንደ ገለጸለት ተመዝግቧል ።

1. I Russi in Etiopia, C. Zaghi, P. 129.

ይኸው የኢጣልያ ጉዳይ ፈጻሚ ቀጠሮ ጠይቆ ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከልዑል ሉባኖቭ በተገናኘበት ቀን ፣ "ኢትዮጵያ በኢጣልያ ሥር ሆና ፣ ምኒልክ እንደሽፍታ የሚቆጠር ሆኖ ሳለ ፣ እናንተ የሱን መልክተኞች በዚህ ዓይነት የክብር አቀባበል መቀበላችሁ የማይገባ ነው ። ይኸንኑ ወቀሳዬን በጽሑፍ እገልጻለሁ" ብሎ ረዥም ንግግር በሚያወርድበት ጊዜ ፣ ሚኒስትሩ በዝምታና በጽሞና ሲመለከተውና ሲያዳምጠው ከቆየ በኋላ መደምደሚያውን ፣ "ኢትዮጵያ ነጻ መንግሥት መሆኗን ፣ ምኒልክም የነጻዪቱ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን እና ምናለን ። ቀድሞውንም ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ አለኝ የምትለውን የበላይ ጠባቂነት መብት አልተቀበልነውም ። ስለዚህም እንደዚህ ያለው የነጻ መንግሥት መሪ መልክተኞቹን ሲልክ በመልካምና በመሰለው መንገድ መቀበል የመስኮብ መንግሥት ትክክለኛ መብቱ ስለሆነ ፣ በዚህ ምክንያት የኢጣልያ መንግሥት ለሚያቀርበው ክስና ወቀሳ ደንበኛ መልሱን እንሰጣለን" ሲል መለሰለት ።

ከዚህ በኋላ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ለዚህ አጸፋውን እመልሳለሁ በሚል ስሜት ከአውሮፓውያን መንግሥታት ጋር የመስኮብ መንግሥት ያለውን የባህልና የንግድ ልውውጥ ለማሰናከል ተጣጣረ ። እንደዚሁም በኢትዮጵያ ስሜን ዤኔራል ባራቲዬሪ ከመንግሥቱ መመሪያ በመቀበል በፊት ካፄ ዮሐንስ ጋር ባለሟል ከነበሩትና አሁን በቅርታ በአክሱም ከተቀመጡት ከእጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር ግንኙነት አድርጎ ፣ እጨጌውንና ካህናቱን በገንዘብና በልዩ ልዩ ስጦታ በመሳብ ፣ በትግራይና በትግሬ ላሉት የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ፣ "ምኒልክ በሃይማኖት ከማይመስላቸው ከመስኮብ መንግሥትና ቤተ ክህነት ጋር ግንኙነት አድርገው የኖረውን የተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ሊለውጡ ነው" የሚል ስብከት በቃልም ፣ በጽሑፍም እያደረገ ማስበተን ዠመረ ። የዚህም የፕሮፓጋንዳ ጽሑፍ በኢጣልያ አገር እየተዘጋጀ በእስክንድርያም ፣ በኢየሩሳሌምም እየተበተነ ፣ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም የኢየሩሳሌም ገዳም መምህራንና መነኮሳት በንጉሣቸው በምኒልክ ላይ እንዲነሡ ያልተሞከረ ነገር የለም ። ዳሩ ግን ፕሮፓጋንዳው ብዙ መንገድ ሳይራመድ እየከሸፈ ሔደ ።

የሆነ ሆኖ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠውና ባልደረቦቻቸው በመስኮብ ከተማ ወዲያና ወዲህ እያሉ በጉብኝትና በግብዣ ሲዘዋወሩ ፣ ከየሚኒስትሮቹ በተለይ ከውጭ ጉዳይና ከጦር ሚኒስትሮቹ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ፣ የንግግሩን ውጤት ፣ ወደፊት የመስኮብ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመርዳት ያቀደውን ፣ የኢጣልያ ጉዳይ ፈጻሚና ጓደኞቹ ለማወቅ አጥብቀው ይጣጣሩ ነበር ። ከዚህ በፊት እንደ ጠቀስነው ፣ የኢጣልያው



ጉዳይ ፈጻሚና ባልደረቦቹ ከዮሴፍም ፣ ከረዳም ወሬ ለማግኘት ቢጣጣሩ አልሆንላቸውም ።

በፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ የሚመራው የመልእክት ጓድ አላላክ የፖለቲካ ፣ የሃይማኖት ፣ የወታደርነት መልክ ስለ ነበረው ስለ ፖለቲካው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጋር ካደረጉት ውይይት በቀር አብዛኛው የፊታውራሪ ዳምጠው ግንኙነት ያበከረው ከጦር ሚኒስትሩ ጋር ነበር ። አዴሳ በደረሱበት በመዠመሪያው ቀን ፊታውራሪው ባማረ ፈረስ ላይ ተቀምጠው ዐሥራ አምስት ሺ የሚሆነውን የወታደር ሰልፍ እየዞሩ በጐበኙበት ሰዓት ከፍተኛ አድናቆት ነበራቸው ። ከዚያም የመልእክቱ ጓድ ዐርባ ቀን ሙሉ በመስኮብ በቆየበት ጊዜ ከየጦር አለቆቹ ጋር በመገናኘት ተወያይተዋል ። በጉብኝት ፣ በሰልፍና በግብዣ ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ፣ ጋዜጦች ሁሉ የሁለቱን መንግሥታት ወዳጅነት ፣ የሁለቱን ሕዝብ ወንድማማችነት እያጐሉ ሲጽፉ ፣ "በነጻነት የቆየችውንና የከበረችውን ክርስቲያኒቱን ኢትዮጵያ በፍራንቼስኮ ክሪስፒ የሚመራው የኢጣልያ መንግሥት የውጫሌን ውል አመካኝቶ ውጊያ በመዠመሩ ወንጀለኛ ነው" እያሉ በጽሑፍ ሲነቅፉ ኢትዮጵያን ሲደግፉ ፣ በየስብሰባው ጉልማማውና በደማቅ ቅላት መልካቸው ያሸበረቀው ፊታውራሪ ዳምጠው ብቅ ባሉ ቁጥር የተሰበሰበው መኳንንትና መሳፍንት ከነሕዝቡ በደመቀ ሁኔታ ሲቀበላቸው ሰነበተ ።

በዚሁ ጊዜ ኮንት ሊዎንቴቭ በበኩሉ ፣ "ዳግማዊ ምኒልክ ዘራቸው ከሰሎሞንና ከንግሥት ሳባ የወረደ ፣ ብልህ ፣ ቸርና ደግ ንጉሥ ከመሆናቸው ጋር ባገራቸው የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማግባት የሚጣጣሩ ፣ ላገራቸው ጸጥታና ሰላም የሚፈልጉ ሲሆን ፣ በሌላው በኩል ያገራቸውን ነጻነት ለመከላከል ቆርጠው የተነሡና ስላገራቸው ነጻነት የመጨረሻ ደማቸውን ለማፍሰስ የቆረጡ ናቸው ። ሕዝቡም ኩሩ ተዋጊ ፣ ሃይማኖቱንና አገሩን ንጉሡን ወዳድ ነው" እያለ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ሰነበተ ።[1]

በዚህ ዓይነት ክብርና ደስታ ከሰነበቱ በኋላ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠውና ባልደረቦቻቸው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዳግማዊ ኒኮላ ለስንብት ቀርበው ፣ አንድ ራሱ ማኅደሩ በወርቅና መጨበጫው በአልማዝ ያጌጠ ጠመንጃና ልዩ ልዩ የወርቅ ፣ የአልማዝ ቀለበት እንደዚሁም በቅዱስ አሌክሳንድር ኒቭስኪ የተሠየመ በዕንቁና በአልማዝ የተንቆጠቆጠ ባንገት የሚጠለቅ ኒሻን ለምኒልክ ፣ ቀጥሎም መሸፈኛው

1. I Russi in Etiopia, C. Zaghi, pp. 156-158

በክር ሥራ ያጌጠ በውስጡ የሴት የመታጠቢያ ቤት ልዩ ልዩ ዕቃ ፥
አንድ ያንገት ድሪ ፥ በክንድ የሚደረግ አምባርና የገሮ ጉትቻ ለእ
ቴጌ ጣይቱ ፥ አንድ " ኤክስፕሬስ " የሚባል ጠመንጃና አንድ የአል
ማዝ ቀለበት ፥ አንድ ልዩ የኪስ ሰዓት ፥ አንድ በከበረ ድንጋይ ያጌጠ
ጐራዴ ለፊታውራሪ ዳምጠው ፥ ለራስ መኰንንም በቅድስት ሐና
የተሠየመ ባንገት የሚጠለቅ ባለ ኮርዶን ኒሻን ተላከ ። እንደዚሁም
ለቀሩት ተከታዮች እንደ የማዕረጋቸው ተሰጥቷል ። ሌሎችም መሳፍ
ንትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ለመላክተኞቹ ብቻ ሳይሆን ላፄ
ምኒልክና ለእቴጌ ጣይቱ አንዳንድ የመታሰቢያ ስጦታ በየስማቸው
ላኩ ።

ከዚህ በኋላ ፥ ፊታውራሪ ዳምጠውና ባልደረቦቻቸው ንጉሠ ነገ
ሥቱንና ንግሥቲቱን ሌሎችንም በደስታ ፥ በፍቅርና በናፍቆት ስሜት
ተሰናብተው በመጨረሻ ከጦር ሚኒስትሩ ስለርዳታ አንድ መቶ ሃምሳ
በርዳን ጠመንጃ ተቀብለው ወደ ኦዴሳ ተመለሱ ። አካሔዳቸው በቱርክ
ዋና ከተማ በስንጣንቡል (ኮንስታንቲኖፕል) በኩል ስለነበረ ፥ የቱርኩ
ሡልጣን የእልፍኝ አስከልካዩን አህመድ አሊ ባሻን ልኮ ከመርከባ
ቸው ላይ በማስመጣት በቤተ መንግሥቱ ግብዣ አደረገላቸው ። ከዚ
ያም ከሡልጣኑ ተሰናብተው በመርከብ ወደ እስክንድርያ (ግብፅ)
ከዚያ ወደ ፖርትሳይድ ተመልሰው በመጡበት ሚሳጀሪ ማሪቲም
በሚባለው የፈረንሳይ መርከብ ተሳፍረው በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ
ጅቡቲ ሲደርሱ ከራስ መኰንን የተላኩ ሰዎችና የፈረንሳይ ባለሥል
ጣኖች ተቀበሏቸው ።


ከዚህ በኋላ ፥ ወደ መስኮብ አገር ያደረሳቸው ሌምንቴሽ አሁንም
እስከ ጅቡቲ ካደረሳቸው በኋላ ፥ በፍቅር ተሰነባብቶ ወዳገሩ ሲመለስ
እነፊታውራሪ ዳምጠው በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከን
ጉሠ ነገሥታቸው ጋር በመገናኘት ኒሻኑንና ገጸ በረከቱን ለንጉሠ
ነገሥቱና ለእቴጌ ጣይቱ አስረከበው የሆነውን ሁሉ በቃልና በጽ
ሑፍ ሳይገልጹ አይቀሩም ። ዳሩ ግን ፥ የዚህን ጉዳይ የሚነግረን ምንም
ጽሑፍ የለም ። ከአዲስ አበባ እንሣሣቸውን የጠቀሱት ጸሐፌ ትእዛዝ
ገብረ ሥላሴ ፥ "...ወደ መስኮብ መንግሥት የተላኩት እነፊታው
ራሪ ዳምጠው በዕንቁ ፥ በአልማዝ የተሸለመ ለንጉሠ ነገሥት የሚ
ገባ መዠመሪያውን ኒሻን ይዘው መጡ "[1] በማለት ቀንጨብ አድር
ገው ዝርዝሩን አልፈውታል ።

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፥ ገጽ 225 ። በተረፈ ስለሌላው ዝርዝር ሁኔታ
ካርሎ ዛጊ የጻፈውን በሙሉ ማንበብ ያስፈልጋል ።



እነፊታውራሪ ዳምጠው ፥ አዲስ አበባ በመስከረም ወር 1888
ዓ.ም. እንደ ደረሱ ፥ ወዲያው ምንም ያህል የዕረፍት ጊዜ ሳያገኙ ለዓ
ድዋ ጦርነት የከተት ዓዋጅ ተደርጎ ንጉሠ ነገሥቱ ጦራቸውን አስ
ከትለው በጥቅምት ፪ ቀን ካዲስ አበባ ወደ ሰሜን ለዘመቻ ሲጓዙ
ፊታውራሪ ዳምጠውም የራሳቸውን ጦር ይዘው የዠግንነት አሟ
ሟት ወደሚጠብቃቸው ወደ ዓድዋ አብረው ዘመቱ ።



ፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ

መልካም ቤተሰቦች ከተባለው ከራስ ቢቶደድ መኰንን እንዳልካቸው መጽሐፍ



ኒኮላይ ሰርጌዬቪች ሌዎንቴቭ
ከቫቲካን ቤተ መጽሐፍ

# ክፍል ሦስት

## የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት

## ምዕራፍ ሐያ አምስት

### የክተት ዓዋጅ — የንጉሠ ነገሥቱ ጉዞ ወደ ትግሬ — ወታደራዊ ድርጅትና አቅዋም

ዶክተር ትራቬርሲና ኮሎኔል ፒያኖ ወዳገራቸው እንደ ተመለሱ ፣ ዠኔራል ባራቲዬሪ በሰሜን ማጥቃቱ ቢታወቅም ፣ ዳግማዊ ምኒልክ የውጫሌን ውል መፍረሱን ለየመንግሥታቱ ከማስተላለፍ በቀር በቶሎ የጦርነት ዓዋጅ አላወጁም ። ሁልጊዜም ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ያለው ጠብ እንደማያቋርጥና ጦርነትም እንደማይቀር በልባቸው ተገንዝበዋል ። በሰበብ በአስባብ በሚያገኙት አጋጣሚ እየተጠቀሙ ፣ መሠረታዊ ጥያቄያቸውንም ሳይለቁ ላይ ላዩን ፣ "ወዳጅነታችን ለምን ይቅር ፣ በከንቱስ ለምን የክርስቲያን ደም ይፍሰስ ፣" የሚል ደብዳቤ እየጻፉ ጊዜ ያራዝሙ ነበር ። ጊዜ ያራዘሙባቸው ምክንያቶች ሦስት ናቸው ።

ሀ/ ወደፊት ለሚያደርጉት ጦርነት በቂ የምግብ ስንቅና የጦር መሣሪያ በደንብ እስኪዘጋጅ ድረስ ፣

ለ/ ራስ መኰንን በ1881 ዓ.ም. ሮማን የጐበኙ ጊዜ የሐረርን ጉምሩክ ቀረጥ እንደ ማያዣ አድርገው ከኢጣልያ ባንክ የተበደሩት አራት ሚሊዮን ሊሬ (አንድ ሚሊዮን የማሪያ ቴሬዛ ብር) እስኪከፈል ፣

ሐ/ ሌላው አውራጃ ሁሉ ለማዕከላዊ መንግሥት ሲታመን ፣ በወላሞ ንጉሥ ጦና አስቸግሮ ስላመጣ እርሱ በዘመቻ ተገዶ እስኪገብርና ደቡባዊ ዠርባቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ ነው ።

ስለዚህ የኢጣልያን የወታደር ብዛትና ትጥቁን ፣ የጦር መሣሪያውን ብዛትና ዐይነት ፣ ራስ መኰንን ሮማን በጐበኙ ጊዜ ባይናቸው ያዩትን

በዝርዝር ባስረዱዋቸው መጠን ከእንደዚህ ያለው አውሮፓዊ ሥልጡንና ኃያል መንግሥት ጋር የሚደረገው የገሃድ ጦርነት በዋዛ እንደማይፈጸም ያውቃታል ። ዝግጁነትም ፣ ብዛትም ያላቸው የጦር መኳንንትና ወታደሮች ቢኖሩዋቸውም ፣ እነዚህኑ በዘመናዊ የጦር መሣሪያ ካላስታጠቁ ብዛትና ዝግጁነቱ ሁሉ ዋጋ ቢስ እንደሚሆን ከቅርቡ ከመቅደላው ጦርነት ስለሚገነዘቡት ፣ በዚህ ጊዜ አሳባቸው ያተኮረው በተቻለ መጠን በጥድፊያ መድፍ ፣ ጠመንጃና ጥይት ከመሰብሰቡ ላይ ነው ። ከቀድሞ ዠምሮ በእጃቸው የነበረ ጠመንጃና ጥይት ፣ በቅርቡም ከአሰብ የመጣላቸው ሁለት ሚሊዮን ጥይት እጃቸው ቢገባም ፣ ይኸም እንደማይበቃ ዐውቀውታል ። ከጀርመን አገር አንድ መቶ ሺ ጠመንጃ አዘው የነበረውን ፣ የጀርመን መንግሥት ከኢጣልያ ጋር ባለው የቃል ኪዳን ዝምድና ምክንያት እምቢታውን ስለገለጠ ጉዳዩ አሳሳቢ ሆነ ። በዚሁ ጊዜ የመሣሪያ ማግኛው ምንጭ ፈረንሳይና መስኮብ ብቻ ነበሩ ።

ስለዚህ ፣ ከወዳጆቻቸው ከመስኮብ ዘንድ በሌዎንቴቭ በኩል ፣ ከፈረንሳይ መንግሥት በሽፍነና በነአርኑ አማካይነት የተቻለውን ያህል ሰበሰቡ ። ስለ መሣሪያው ዝግጅት ነጋድራስ አፈወርቅ በጻፉት መጽሐፍ ከዚህ የሚከተለውን አስፍረው ይገኛል ።

> ዐጤ ምኒልክ . . . ነገራቸውን ሁሉ እያበጃጁ እያስናዱ ተጋፍቶ ቢመጣም እንገጥመዋለን ፣ ተጋፍቶ ባይመጣም ተደራጅተን ሰናበቃ አለፈቃዳችን የያዘውን አገር ግፋን ሔደን (ወደ ፊት ገፍተን) እናስለቅቃለን ይሉ ዠመር ። በዚሁ ቆርጠው ተቀምጠው ሳለ አንድ ቀን ከፈረንሳዊ የገዙት 30 ያህል የስምዎ (የስማቸው) ምልክት "ም" የተጣፈበት መልካም መድፍ ደርሶላቸው ደስ እያላቸው ሲአዩ ቆዩና በሐኪም ትራቬርሲ ፊት እንግዲህ የመጣው ይምጣ አይመጣም እንጂ ቢመጣ በዚህ እናሳየዋለን [1] አሉ . . .

ይኸን የተናገሩት ፣ ጣልያኖቹ ከራስ መንገሻ ጋር በኮዓቲትና በሰንዓፌ ከነቀኛዝማች ኃይለማርያም ጋር በደብረ ኃይላ ከመዋጋታቸው በፊት ትንሽ ጊዜ ቀደም ብሎ ነው ። ነገር ግን ፣ በማናቸውም ኢጣልያኖቹ እስከ መረብ ድረስ ከመግፋታቸው የተነሣ ለመዝመት አስበው ነበር ። በደቡብ ካሉት ጠቅላይ ግዛቶች ሐረርጌን ጨምሮ በማዕከላዊው መንግሥት ሥር ተጠቃለው ሳለ ባቅራቢያ ካሉት አውራጃዎች ፣ እላይ እንዳልነው ፣ የወላሞ ንጉሥ አፈንግጦ እነራስ መንገሻ አቲከምን ቢልኩ አልበገር አለ። እርሱንም ሳያሳምኑና ዠርባቸውን

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ — ገጽ 86 ።



ሳያስተካከሉ ወደፊት ዘልቀው ወደ ትግሬ መዝመቱም ቅርታ አሳድሮባቸዋል ።

በዚህ ምክንያት ራስ ሚካኤልን ፣ ራስ መንገሻ አቲከምን ፣ ጅማ አባ ጅፋርን ፣ ሊቀመኳስ አባተንና ሌሎችንም አስከትለው በኅዳር 7 ቀን 1887 ዓ.ም ካዲስ አበባ ተነሥተው በ27 ቀን ዳሞት ከጦና ከተማ ገቡ ። ነገር ግን ፣ በዚህ ጦርነት በከንቱ ለሚጠፋው ሳገሩና ለባላገሩ አዝነው ፣ "አገር ከጠፋ በኋላ ሲያቀኑት ያስቸግራል ። ገንዘብም በግድ ካልሆነ በቀር በፈቃድ የሰጡት አያልቅም ። አገርህን አታስጠፋ ፤ ግብርህን ይዘህ ግባ" ብለው በመጨረሻ የማስጠንቀቂያ ምክር ለጦና ቢልኩበት የእምቢታ ቃል መለሰ ።

ከዚህ በኋላ ወታደሩን በየመሪው በግራና በቀኝ ፣ በፊት ለፊትም ልከው ፣ ጦርነቱ ተዠመረ ። ውጊያው ወደ ማለቂያው ሲደርስ ጦና ከወላሞ ወደ ቦረዳ ሸሽቶ ነበር ። ወታደር እግር በግር ተከታትሎ ደርሶበት በጥይት ተመትቶ ተያዘ ። ጦርነቱ አልቆ አገሩ ጸጥ ሲል ፣ ወታደር የማረከውን ሰውና ከብት ፣ በተቻለ መጠን ለየባለቤቱ እንዲመልስ አዘዙ ። ለወላሞ ግዛትም ራሱን ጦናን መልሰው ሾመውና አደላድለው ሲጨርሱ ፣ እርሳቸው ወደ ከተማቸው በጥር 11 ቀን ተመልሰው ገቡ ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ጦርነቱን ለመካፈል መጥተው የነበሩት ፣ ጀጌ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በሰፈሩበት ሰዓት ተሰናብተው ፣ በቆጫና በገሙ በኩል አድርገው ፣ ከፋ ከግዛታቸው ገቡ ።[1]

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከወላሞ ሲመለሱ ፣ ከራስ መንገሻ ተልከው የመጡት ሹም አጋሜ ተሰፋዬ ፣ ራስ መንገሻ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ከኢጣልያኖች ጋር ሁለት ጊዜ ተዋግተው ስለ ተሸነፉ ፣ የትግሬን ግዛት ለቀው ወደ ራስ ወሌ ግዛት መግባታቸውን በዝርዝር ለንጉሠ ነገሥቱ አስረዱ ። ቀጥሎም አዲስ አበባ ገብተው እንደ ሰነበቱ ፣ በደብረ ኃይላ እነቀኛዝማች ኃይለማርያም ተዋግተው አሁንም ጣልያኖች ማሸነፋቸውን ሰሙ ። ከዚህ በኋላ ፣ የጣልያን ጦር ወደፊት እየገፋ አዲግራትንና መቀሌን በመያዝ መሽጎ ፣ ግንባር ቀደሙ ጦራቸው ወደ አላጌ መገሥገሡ ተሰማ ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ 218 - 220
Une Expedition-Avec le Negus Menelich, J.C.Vanderheym Chap. IV,PP. 107 - 161.

ቢሆንም ቀደም ብለን ያወሳነው፣ የኢጣልያ ብድር እንዲከፈል ሰው ሁሉ በቀንድ ከብት አንድ ብር (የቀንድ ብር ወይም የፈሰስ ብር) እንዲያዋጣ ቀደም ብሎ ትእዛዝ በያለበት ተላልፎ ነበር ። ገንዘቡ ተሰብስቦና በራስ መኰንን አማካይነት ተከፍሎ ፣ ስለ ዋስትና በኢጣልያኖች እጅ ተይዞ የነበረውን የሐረር ጉምሩክ በዚሁ ሰሞን አስለቀቁ ።

ጦናን ከአሳመኑና ይኸንንም አንድ ሚሊዮን ብር ከፍለው ከዕዳ ነጻ ሲሆኑ የጦርነት ዓዋጅ ገና አላሳወጁም ነበር ። ከወላሞ እንደተመለሱ በግንቦት ወር ወደ ወረይሉ ሔደው ዋግሹም ብሩን አስረው ልጃቸው ጓንጉልን ሾሙ ። የኢጣልያኖቹንም የወረራ ሁናቴ በቅርቡ ካረጋገጡ ወዲህ በሰኔ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ። ክረምቱን በሙሉ ሲዘጋጁ ከርመው ፣ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ መክረው ፣ ዘክረው ከጨረሱ በኋላ ፣ በመስከረም ወር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክተት ዐዋጅ በይፋ በነጋሪት ዐወጁ ።

> እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ ። እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ ። እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለኔ ሞት አላዝንም ። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም ።
>
> አሁንም አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል ። እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ የሰዉን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር ።
>
> አሁን ግን ፣ በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም ። ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም ። አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም ። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ ። ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ ለምሽትህ ለሃይማኖትህ ስትል በሐዘን እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ፣ ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም ። ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ ። [1]

በዛሬ አስተያየት ፣ ይህ የንጉሠ ነገሥቱ የክተት ዓዋጅ አንድ የበታች መኰንን ከፊቱ ላለው ወታደሩ በንግግር የሚያስጠነቅቀው ዓይነት ይመስላል እንጂ ፣ ካንድ ከበላይ የንጉሠ ነገሥት መሪ የተሰጠ ጠቅላላ የክተት ዓዋጅ አይመስልም ። "የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም ፣ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም" ሲሉ የቃል ዛቻ ይመስላል ።

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . .ገጽ 225 ።ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሳይጠረዝ በቀረው ታሪካዊ ጽሑፋቸው የዓዋጁን ቃል በጥቃቅን አባባል ለየት አድርገው አስፍረውታል ። ገጽ 187 ።



ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱና ወታደሩ አብረው የሚጓዙ ፣ አብረው የሚበሉ ፣ አብረው የሚሠሩና የኑሮአቸው ሕይወት ለክፉውም ለደጉም የተሳሰረ ስለሆነ እያንዳንዱ ወታደር ይህን የክተት ዐዋጅ በቀጥታ በነፍስ ወከፍ ለራሱ እንደ ነገሩት ያህል በመመልከት ትእዛዙን ወዶ አክብሮ ይቀበለዋል ። በአማላጅ በወዳጅ እድናለሁ ብሎ ተስፋ እንዳያደርግ ነገሩን መሐላ ያምድሞታል ። በዚህ ላይ ደግሞ በዐዋጁ ውስጥ የኢጣልያ ስም አልተጠቀሰም ። ይኸም በጊዜው ለጥንቃቄ ወይም ነገሩን ላለማባባስ በምክር የተደረገ ዘዴ ይመስላል ። የሆነ ሆኖ ይኸን ዐዋጅ በመስከረም ወር ካደረጉ በኋላ ፣ ላገር ጥበቃ አጐታቸውን ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴን ሾመው እርሳቸው በጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ካዲስ አበባ ወደ ዘመቻው ተጓዙ ።

የኢትዮጵያ ወታደር ፣ የኢጣልያ አጥቂነት እንደ ታወቀና የክተት ዐዋጅ ከታወጀ ወዲህ ፣ ለዚህ ለዓድዋ ጦርነት ቀረብ ያለው የጐጃም ፣ የቤጌምድር ፣ የወሎና የላስታው ከ300 እስከ 500 ኪሎ ሜትር ያህል ፣ የሸዋና የሐረር ፣ የባሌ ፣ የአሩሲ ፣ የከምባታ ፣ የሲዳሞ ፣ የጅማ ፣ የከፋ ፣ የወለጋና የኢሉባቦር ጦር ከ600 እስከ 1000 ወይም እስከ 1500 ኪሎ ሜትር ድረስ ርዝመት ያለውን አገር በእግሩ አቋርጦ ተጉዟል ። አብዛኛው አጭር ሱሪና ጥብቆ ለብሶ በዚያ ላይ ነጠላውን ደርቧል ። የሚራመደው በባዶ እግሩ ከደንጊያና ከእንጨት እንቅፋት ጋር እየታገለ ውስጥ እግሩን እሾህ በሙቀት ጊዜ ረምጫ እያቆሰለው ነው ።

ለራሱም ቆብ ስለሌለው የፀሐይ ሐሩር የሌሊት ቁር ይፈራረቅበታል ፤ ቢታመም ባገር ባህል መድኃኒት ከመጠቀም በቀር ደንበኛ ሕክምና አያገኝም ። በጉዞም ላይ እያለ ራሱን የባህሉን መድኃኒት እንደ ልብ ማግኘቱም ይቸግራል ። ከዐፄ ምኒልክ ጓዝ ጋር በከረጢት የተያዘ ቁስል ማድረቂያ ዮድና ዶፈር ፣ ለራስ ሕመም አስፒሪን እንዳለ ቢታወቅም ባቅራቢያ ላሉት ሹማምንትና ዘበኛ እንኳን ማድረሱ ያጠራጥራል ።

ተዋጊ ወታደር ፣ ስንቅ አቀባዩ ገባር ፣ ድንኳን ተካዩ ፤ አብዛኛውን ጊዜ በራሱ ወጭ ለስንቁ ያዘጋጀውን ጥራጥሬ እህል (ሽምብራ ፣ አተር ፣ ባቄላ) ፣ የተቆላ ወይም በእሳት በስሎ የተፈጨ የገብስና የስንዴ ዱቄት በየአረፈበት በውሃ ነክሮ አድበልብሎ የሚበላውን በሶ ባንድ ትከሻው መዋጊያ ጠመንጃውን ወይም ጦሩን በሌላ ትከሻው ተሸክሞ ይጓዛል ። ግማሹም ጠመንጃውን ራሱ ተሸክሞ ፣ ስንቁን በአህያ ላይ አድርጎ ፣ የመጓዝ ዕድል ያለው አለ ። የጉዞውን ድካም ለማዘናጋት ከወንዶቹ ውስጥ ሸለላና ቀረርቶ እያሰማ የሚጓዝ አለ ። ከሴቶቹም የሚያንጐራጉሩና አዋጊ ግጥም የሚገጥሙ ይገኛሉ ።

ማታ በሠፈር ከደረቅ መሬት ላይ ሣር አጭዶ ጕዝጕዞ ይጋደማል ። እንቅልፍም ሊወስደው ይችላል ። አህያ የሌለው እንደልቡ ሲተኛ ፣ ባለአህያው ግጦሽ ለአህያው መፈለጉና አህያውን አውሬ እንዳይበላበት የመጠበቁ ግዴታ ስለአለ ባለአህዮችና ባለአጋሰሶች በየፈረቃ የመተኛት ግዴታ አለባቸው ።

መኳንንትና ሹማምንት እንደየማዕረጋቸው ለብሰው ፣ በበቅሎ ተቀምጠው ፣ ባርኔጣ ደፍተው ፣ አንዳንዶቹም ሻሽ አስረው ፣ አሽከር አስከትለው ፣ ሲጓዙ ውለው ቀን ለምሳ ፣ ማታ ለራት ከቤታቸው ሲነሡ ያስያዙትን ቋንጣ ፣ ዳቦ ቆሎ ፣ ድርቆሽ ፣ ጭኮ ወይም ጥረሾ ይመገባሉ ። ጊዜያዊ መጠጥና ውሃ በእርኮትና በጐባበጠ ቀንድ የመጠጣት ፣ በድንኳን ውስጥ የመተኛት ዕድል አላቸው ። ከጉዞው በቀር በሠፈረበት ቦታ የጦርነቱ ጊዜ እየተራዘመ በሔደ መጠን ፣ የስንቅ ማለቅና ሌላውም ሁሉ ችግር ለነርሱም ቢሆን እየተባባሰ መሔዱ የማይቀር ነው ።

ሌላው ጭፍራ ፣ አሽከርና ገረድ በእግሩ ሲጓዝ እነርሱ በከብት ጀርባ ይጓዛሉ ። ሌላው እብርድ ላይ ሲተኛ እነርሱ በድንኳን ውስጥ ፣ ከምንጣፍ ላይ ብልኮና ጋቢ ለብሰው ይተኛሉ ። እንደዚህ ያለው ያኗኗር ልዩነት በኢጣልያኖቹም በኩል አለ ። ሆኖም ረዥሙን ጉዞ በየቀኑ እበቅሎ ላይ ሆኖ ዳገት መውጣቱ ፣ ቁልቁለት መውረዱ ፣ ሸለቆ ፣ ወንዛወንዝና ሰፋፊ ሜዳ ማቋረጡ ፣ ሁሉም ቢሆን ለሰውነት አድካሚና አሰልቺ ፣ ጭንና ባትን የሚያደነዝዝ ነው ።

ከነርሱ የበለጠ ግን ፣ እነርሱን በመከተል ጠመንጃና ጐራዴ ፣ እርኮትና ሌላም ዕቃ ተሸክሞ በጌታው በቅሎ ኋላ የሚኳትነው አሽከር ፣ በጀርባዋ የስንቁን አገልግል ወይም ሹሮና ድልህ በቅላቅል ተሸክማ የምታጓዘው ገረድ አሁን ካለንበት ዘመን ላይ ሆነን ስናጤነው ሁለቱም የነበረባቸው ድካም ከፍ ያለ ነው ። ከተወሰነው ሠፈር ቀን ለምሳ ፣ ሌሊት ለመኝታ ጌታውና ሌላው ጭፍራ ሲያርፍ ፣ አሽከር ድንኳን የመትከል ፣ እንጨትና ውሃ ፣ ሣር ለበቅሎ የመፈለግ ግዴታ አለበት ። ገረድም መብል የማዘጋጀቱ ጉዳይ ይጠብቃታል ። ጌትዮው በድንኳን ውስጥ ፣ በሥጋጃ ወይም በካሊም ፣ አለዚያም በቁርበት ላይ ሲተኛ አሽከርና ገረድ ቀን ለብሰው የዋሉትን እንደ ለበሱ ፣ እንደተራው ወታደር እጠራ ሜዳ ላይ የጌትዮውን ድንኳን ከበው ይተኛሉ ።

ከአዲስ አበባ ወይም ከሌላው ከተማ ተመርጣ የመጣችው የጭን ገረድ የምትባለው የጌታዋን መኝታ አነጣጥፋ ፣ እግር አጥባና ራት አብልታ ፣ እሷም የተራረፈውን በላልታ ከጌታዋ ጋር በድንኳን



ውስጥ የመተኛት መብት ይኖራታል ። ይኸን ሁኔታ ባለቤት ሴት ወይዘሮ የተስማሙበትና ያገር ባህል የፈቀደው ስለሆነ ፣ በመኝታም በመብልም የጭን ገረድ ከሌሎች የተሻለ ዕድል አላት ማለት ነው ።

በዚህ አያያዝ ፣ አሽከርና ገረድ የተጐዱ ፣ ጌትየው የተጠቀመና ድልወት ያገኘ ይመስላል ። ነገር ግን በጦርነቱ ወቅት ገረድና አሽከር ይልቁንም ገረዷ ወደኋላ ከጓዝ ጋር ትቆያለች ። የተሻለ ኑሮ ያገኘው የጦር መኰንን ከወታደሩ ጋር እጦርነቱ አፍላ ላይ ገብቶ የመዋጋት ግዴታ አለበት ። በመጨረሻም በዕድል ካልዳነ በቀር የመቁሰልና ጭራሹንም የመሞት አደጋ አለበት ።

የሆነ ሆኖ ፣ በዚህ ዐይነት የኋላ ቀርነት ችግር መካከል ወደፊት እንደምናነበው ፣ የኢትዮጵያ ወታደር ረዥሙን የወራት መንገድ በእግሩ ተጉዞ ፣ የራሱን ጥራጥሬ እህል በልቶ ፣ ንጹሕ ውሃ ተጐንጭቶ ከባሕር ማዶ በባቡርና በመርከብ ተሳፍሮ የመጣውን ድርጅቱ የተሟላውን ፣ በጦር ትምህርት ቤት የሠለጠነውና በማናቸውም ምቾት ያልተለየውን የፈረንጅ ወራሪ ተዋግቶ በማሸነፍ ፣ አገሪቱን ከባርነት ውርደት በማዳን ፣ ለሚመጣው ትውልድ አኩሪና አስመኪ ታሪክ አወረሰ ።

በርሱ አንጻር ፣ የሠለጠነውና መልካም ልብስ ለብሶ ፣ በጥሩ መብልና መጠጥ ሰውነቱን ገንብቶ ፣ ላገሩ ቅኝ አገር ለማውረስ በድንፋታና በእብሪት የመጣው የኢጣልያ ወታደር የመሸነፍን ወራዳ ጽዋ ቀምሶ ፣ ለወገኑ መጥፎ ዝናን ለዘላለም አተረፈ ። በድልወት የተቀናጣው ባለመለዮውና ባለጫማው የኢጣልያ ወታደር ለየካቲት 23 ቀን እጥቢያ በሌሊት ጉዞ ሲደናበር የእንዳ ኪዳነ ምሕረት ፣ የአባ ገሪማ የማርያም ሸዊቶ ዳገትና ቁልቁለት ፣ ሸለቆና ጉብታ ፣ ጠጠርና ደንጊያ ሲያዳክመው ፣ የኛው ወታደር ዱሮውን በለመደው አኗኗር ሁሉንም ችግር በጠቅላላው በመቋቋም ጠላቱን ተዋግቶ አሸነፈ ።

መቸም ቢሆን መማርም መሠልጠንም ተገቢ ነው ። ነገር ግን ራሱ ሠለጠንሁ ብሎ ፣ በድልወት ኖሮ ፣ ሌላውን መናቅ ራስን በተናቀው እጅ ያዋርዳል ። የምዕራቡም ፣ የምሥራቁም ሥልጡኑና ገናናው የሮማ የቄሣሮች መንግሥት የወደቀው ባልሠለጠኑና ባልተማሩ ፣ በሚንቋቸው ነገዶች እጅ ነው ። ንጉሡ ኡምቤርቶና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ከባለሥልጣኖቻቸው ጋር ይኸን ያባቶቻቸውን የሮማውያንን ያለፈ ታሪክ በክፍል እንደ ተማሩት አይጠረጠርም ። ይሁን እንጂ ፣ በዚህ ኢትዮጵያን ለመውረር በተነሡበት ዘመን በደንብ አላጤኑትም ። ነገር ግን ይኸን ያጤኑት ድል ከተመቱ በኋላ መሆኑ ነው ። የዚህም ትርጉሙ 'ኸብ ከሔደ ውሻ ጮኸ' እንደሚባለው መሆኑ ነው ።



DÉFILÉ DE LA CAVALERIE DEVANT MÉNÉLIK (PAGE 150).

የምኒልክ ጉዞ
ለቱር ዲሞንድ ከኤች አደን መጽሐፍ



የወላሞ ባላባት ጦና

ከአባ ማስያስ መጽሐፍ




ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ
ከሞሪስ ደኮፒ መጽሐፍ



በዚህ ዘመን ያንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ትጥቅ

ከግን ዴስም መጽሐፍ

የዓፄ ምኒልክና የሠራዊታቸው ጉዞ ወደ ሰሜን



# ምዕራፍ ሐያ ስድስት

## በራስ መኰንን አዝማችነት ግንባር ቀደም የሆነው ጦር አላጌ ስለመድረሱ—ራስ መኰንን ከጄኔራል ባራቲዬሪና ከማዦር ቶዜሊ ጋር የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተገነዘብነው ፣ የኢጣልያ መንግሥት መሠረታዊ አሳብ ቢቻል መላ ኢትዮጵያን ፣ ያም ቢቀር የሰሜኑን ክፍል በሙሉ ይዞ ከዚያም ሁኔታው እየታየ ወደፊት መግፋትና ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት መፍጠር ነው ። ለዚህ ዓላማ የሚያስፈልገው በጀት ዐሥራ አራት ሚሊዮን ሊሬ ግድም ተፈቅዷል ። ይኸውም በኢትዮጵያ ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የማርቴሬዛ ብር ይሆናል ። ወታደሩም በየጊዜው ከናፖሊ ወደብ እየተሳፈረ ፣ ምጥዋ ላይ እየተራገፈ ፣ አሥመራና አዲግራት ላይ እየተከማቸ በየመሥመሩ ይደለደላል ። ቀድሞ ከተያዘው ከሠራዬ ፣ ከሐማሴን ፣ ከአከለ ጉዛይ ፣ ከሐባብ ፣ ከቦጐስ ፣ ከከረን አውራጃዎችና አሁን በቅርቡ ከተያዘው ከእንደርታ ፣ ከአጋሜ ፣ ከተምቤን ፣ ከገረአልታ ፣ ከእንዳ መሆኔ የሚገኘው ያገር ተወላጅ በግድም በውድም እየተመለመለ በድርጅት ታጥቋል ። ሌላው ደግሞ የነራስ ስብሐት ፣ የነደጃች ሐጐስ ተፈሪ ፣ የነደጃች ዓሊ ፣ የነሼክ ጠልሃ ነጭ ለባሽ ባንዳ በየባላባቶቹ አማካይነት ጠመንጃ እየተቀበለ ዝግጅቱ በኢጣልያኖቹ በኩል በትጋትና በቅልጥፍና ይራመዳል ። በዚያው መሥመር የሰላውና ባለባቶቹን የመከፋፈሉ ጉዳይ በግልጽም በምስጢርም ይካሔዳል ።

ባለፉት የኮአቲት ፣ የሰንዓፌና የደብረ ኃይላ ጦርነቶች ፣ የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ራስ መንገሻን ሊያጠቁ የቻሉት ለጦርነት ባሠለጠኑት በዚህ ያገር ተወላጅ ጦር ከፍተኛ ድጋፍ መሆኑ አይጠረጠርም ። የኢጣልያ መንግሥት ላገሩ እንግዳ ቢሆንም ፣በሀብት ምጣኔና በቴክኒክ ከፍ ያለ የሠለጠነ መንግሥት ስለሆነ ፣ ሁሉንም ጉዳይ በየመስኩ በማዘጋጀት ያገር ተወላጁን ለጦርነት በማሠልጠን በሹመትና በገንዘብ ወሬ ነጋሪ ፣ አስረጅና መንገድ መሪ እየገዛ የወራሪነት ተግባሩን በደንብ ይመራል ።

ከወዲህም ባሼ ምኒልክ በኩል ዝግጅቱም ፣ ስለላውም እየተከናወነ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ከመረብና ከበለሳ ሙና ወዲህ የያዘውን

ወረዳ ሁሉ በሰላም እንዲለቅ አጥብቀው እንደጣሩ በትክክል ይታያሉ ። በዚህም በኩል ለጦርነት ዝግጅቱና ሰላም ፍለጋው ጐን ለጐን ይሔዳሉ ። በኢጣልያ በኩል የተፈለገው ደግሞ ፤ በጦርነት ወይም በሰላም አገር ማግኘት ብቻ ስለሆነ ፤ የሁለቱ መንግሥታት አሳብ በፍጹም የተለያየ በመሆኑ ፡ ሁለቱም ወደ ጦርነቱ መምጣት ግዴታቸው ሆነ ።

በኢትዮጵያ ባለፈው የሃምሳ ዓመት ታሪክ ውስጥ የሥልጣን መያዝ መሠረት የጦር ኃይል ነው ። ዐፄ ቴዎድሮስ ከመሳፍንቱ ፤ ዐፄ ዮሐንስ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዙፋን የወረሱት ፤ አሁንም ዐፄ ምኒልክ በንጉሠ ነገሥት ዙፋን የተቀመጡበት በጦር ኃይል ነው ። እውነት ነው ፤ ከነገሡ በኋላ ነጋሢው ሁሉን እንዳመሉ ሲያስተዳድረው ፤ የመስፍኑን ወይም የመኰንኑን ክብሩን ሲጠብቅለት ፤ በሹመትና በሽልማት ሲያሳድገው ፤ ለሕዝብ ትክክለኛ ፍርድ መስጠቱ ሲታይ ፤ ከየትም ክፍል ቢወለድ ፤ "ይኸስ ይገባዋል ፤ ሺ ዓመት ያንግሠው" የሚባል አለ ። ዐፄ ምኒልክ በዚህ በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ሁሉን እንዳመሉ በመያዝ ፤ ለሁሉ በተቻለ መጠን የሚገባውን በመስጠታቸው ፤ ለውጊያ ፤ ለቅጣት ፤ ለበቀል ሳይቸኩሉ ሁሉንም በትዕግሥት እያመዛዘኑ ስለሚሠሩ ይነስ ይብዛ በዚህ ጊዜ ባገሪቱ የሕብረት ስሜት ፈጥረው መጭውንና ከባዱን ጦርነት እንደ ምንም ሲወጡት ይታያል ።

ይኸውም ሆኖ ፤ የቅርብ ረዳታቸው ራስ መኰንን ኢጣልያን በጐብኙበት ሰዓት የእግረኛውን ፤ የመድፈኛውንና የመርከበኛውን ወታደር ትጥቁን ፤ የጦር መሣሪያውን ብዛትና ጥራት ባይናቸው ያዩትን በዝርዝር ለንጉሠ ነገሥቱ ማስረዳታቸው የማይቀር ነው ። ባንድ ወገን የፈረንጅን ጦር አንችለውም የሚል ጥርጣሬ ባፄ ምኒልክና በመኰንን ዘንድ ሊያድር ይችላል ። በሌላው ወገን ፤ " እኛ ወደፊት ገፍተን ከኢጣልያ ስንዋጋ ከኋላችን አገሌና አገሌ ሸፍተው ቢወጉንስ ? እነ እገሌ ተነጥለው ወደ ጠላት ቢደረቡስ ? በስንት ጣር ያገኘነውና ያቋቋምነው መንግሥት መልሶ ቢፈርስስ!" የሚል ሥጋት ሊያዋልላቸው ይችላል ። በዚህ አንጻር ደግሞ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከነገሡ ጀምሮ ያደራጁት የጦር ሠራዊትና በሹመት በማዕረግ ያሳደጉት የጦር አለቃ ብዛቱን ፤ ንቃቱን ፤ ታማኝነቱን ሲያዩት ይበራታሉ ። ከኢጣልያ በወዳጅነቱ ጊዜ የተቀበሉትና ከፈረንሣይ መንግሥት በንጹሕ ወቄት ወርቅና በዝሆን ጥርስ* የገዙት ጥሩ ጥሩ የጦር መሣሪያ

* አንድ ወቄት ወርቅ (በ1909 ዓ.ም.) ከ37—39 የማርያቴሬዛ ብር ሲሆን አንድ ፈረሱላ የዝሆን ጥርስ ከ180 እስከ 210 ብር ያወጣል ።



በእጃቸው መኖሩን ሲረዱና በዙሪያቸው ፤ ባገዛዝ ብቻ ሳይሆን በጋብቻና በወዳጅነት በፍቅር ገመድ ያሰሩዋቸውን የመኳንንትና የመሳፍንት ብዛትና ሕብረት ሲመለከቱ ልባቸው በኩራትና በአለኝታ መጽናናቱ የታወቀ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፤ ባላቸው ያስተዳደር ዘዴና አስተዋይነት ጐን ንቁና ብልህ የሆኑት ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ያላቸው የፖለቲካ ፤ የጦርና ያስተዳደር ልምድ ፤ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መተባበር ፤ በዝግኖችና ቁጥራቸው በበረከተ መሳፍንትና መኳንንት መከበባቸው ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ልብ በአለኝታ የተመላ ሳይሆን አልቀረም ።

ቢሆንም በቤተ መንግሥቱ በዚህ የጦርነት ዋዜማ ሦስት ክፍል ይታያል ። በአንደኛው ክፍል እንደ እቴጌ ጣይቱ ፤ እንደ ራስ ወሌ ፤ እንደ ደጃች በሻህ አቦዬ ፤ እንደ ፊታውራሪ ገበየሁ ፤ እንደ ሊቀ መኳስ አባተ ያሉት ፤ " ኧረ እንበለው የምን መለማመጥ " የሚሉ ናቸው ። በሁለተኛው ክፍል ከንጉሠ ነገሥቱ ዠምሮ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፤ ራስ መንገሻ አቲከም ፤ ራስ መኰንን ፤ ደጃች መሸሻ ወርቄ ፤ አፈ ንጉሥ ነሲቡ ፤ (አቶ) ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሁኔታውን በማመዛዘን ነገሩን በለዘብታና በዘዴ ይዘው ሰላማዊ መንገድ የሚፈልጉ ናቸው ። ሦስተኛ ፤ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፤ ራስ አሉላ ፤ ራስ ሐጐስ ባሁኑ ጊዜ የተወረረው አገር የትውልድ አገራቸው ስለሆነና የኢጣልያ መንግሥት ስለከዳቸውም ጦርነቱን አጥብቀው እንደሚፈልጉት ግልጥ ነው ።

ስለዚህ ፤ በጠቅላላ የሁሉም አሳብ ተመዛዝኖ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሚመራባቸው አሳቦች በሁለት ላይ በግልጽ እንደ ተመሠረቱ ይታያል ።

፩ኛ. በማናቸውም ረገድ በትዕግሥት በሰላም ኢጣልያኖችን ካገር ለማስወጣት መፈተን ፤

፪ኛ. የሰላሙ መንገድ በፍጹም የከሸፈ እንደሆነ ጠንክሮ መዋጋት ነው ።

የኢጣልያ መንግሥት ግን እላይ እንዳልነው ፤ እንደ እንግሊዝና እንደ ፈረንሣይ ፤ እንደ ጀርመን ፤ እንደ ቤልጅክ በግድ ቅኝ አገር ማግኘት አስፈላጊዬ ነው ብሎ በእንግሊዝ ፤ በአውስትሪያ ፤ በጀርመን ደጋፊነት ቆርጦ የተነሣ ነው ። ባለፉት በተደረጉት ጦርነቶች በቀላሉ ራስ መንገሻን ስለ አሸነፈ ፤ "በያለበት ያሉት መሳፍንት ባፄ ምኒልክ ውስጥ ሕብረት አድርገው ኢጣልያን ሊወጉ አይችሉም ። ቢዋጉም የአንድነትና ያገር ፍቅር ስሜት ስለሌላቸው ጦርነቱ ሲዠመር

ወዲያው ይፈርሳል ። ያዬ ምኒልክና የራስ መኰንን ሰላም ፈላጊነት ከፍርሃት የተነሣ ነው ” የሚል ግምት ስለ አደረሰበት ፣ እነሆ ከዋናው የጦር ሰፈሩ ከአሥመራ 300 ኪሎ ሜትር ፣ ከአዲግራት 200 ኪሎ ሜትር ግድም ዘልቆ እስከ አላጌ ከደረሰ በኋላ ፣ ቀጥሎም ከአላጌ 150 ኪሎ ሜትር አልፎ አሸንጌ ላይ ደረሰ ። ታዋቂው የጦር መኰንን ማዦር ቶዜሊ ብዙ ጦር ይዞ በመጀመሪያ እስከ አሸንጌ ድረስ የጦሩ ጫፍ ከደረሰ በኋላ ፣ ባሁኑ ጊዜ ከአለቆቹ ተመካክሮ ወደኋላው ቀለስ በማለት ለውጊያ ከሚመቸው አላጌ ጉብታ ከበሩ ላይ በደንብ መሽጎ ተቀምጧል ።

ማጆር ቶዜሊ ፣ የአራተኛው ያገር ተወላጅ ባታዮ ጦር አዝማች ሆኖ ከዚህ በፊት እንደ ተመለከትነው ፣ በሐላይ ደጃች ባሕታ ሐጎስን ተዋግቶ የገደለ ነው ። ከመግደሉም በላይ ሬሳቸው ለመቀጣጫ እንዳይቀበር መከልከሉ ይታወሳል ። ከዚያ በኮአቲት ፣ በሰንዓፌና በደብረ ኃይላው ጦርነት ለክፍሉ ዋና መሪ ሆኖ ተዋግቷል[1] ። በዚህ ምክንያት ቶዜሊ የራሱን የባታዮ ጦር ይዞ ብቻውን የንጉሡን ጦር ሊመልስ ይችላል ተብሎ ግምት የተጣለበት ከፍተኛና ዝግና የጦር መኰንን እንደሆነ ተገምቷል [2] ።

አሁንም ለጦርነት ምቹ የሆነውን ከፍታው እስከ 3013 ሜትር የሆነውን የአምባ አላጌን መተላለፊያ በደንብ መሽጎ ለጦርነት ይጠባበቃል ። በውስጡ የያዘው የጦር ኃይል ከዚህ እንደሚከተለው ነው ። ኤቤል ፣ ካኖቬቲ ፣ ፔርሲኮ ፣ ሪቺ ፣ ብሩዚ በሚባሉ ሻምበሎች የሚመራ

| | | |
|---|---|---|
| የነጭ ወታደር ፣ | 1350 | ባለጠመንጃ |
| የባንዳ ጦር ፣ | 300 | ” |
| የራስ ስብሐትና የደጃች ዓሊ ጦር | 350 | ” |
| የሸህ ጦልሃ ጦር | 350 | ” |
| በአንጌራ የሚመራ 4 መድፍ | | |
| በጠቅላላ | 4 መድፍና 2350 | ባለጠመንጃ |

እነዚህን እንደያዘ በአምባ አላጌ መሽጎ ሲጠባበቅ ንጉሠ ነገሥቱ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ መንቃነቃቸውን ፣ ከዚያ በራስ መኰንን የሚመራው ግንባር ቀደም ጦር ከደሴ ወደ አሸንጌ መጓዙን ፣ እርግጠኛውን ወሬ ከሰላዮቻቸው ባገኙ ጊዜ ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ ቶዜሊ ከነጦሩ ወደ መቀሌ ተመልሶ እንዲመሽግ ይልከበት ዘንድ ለጄኔራል አሪሞንዲ ጽፎለት ነበር ። ነገር ግን በጊዜ ማጠር ፣ በመንገዱ

1 Lettere e Diari, F. Lemmi, P.9.

2 L' Assedió di Macalle, V. Mantegazza, P. 327



ወጣ ገባነትና ርቀት የተነሣ ፣ ቶዜሊ ወደ መቀሌ ሳይመለስ እርዳታም ሳይደርስለት ቀድመው እነራስ መኰንን አላጌ ጥግ መድረሳቸውን ተመለከተ ።

አዲስ አበባ ላይ ባለፈው የተመለከትነው የክተት ዓዋጅ ከታወጀ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ተነሥተው ፣ በጊዳ በኩል አድርገው ፣ በጥቅምት 18 ቀን ወረይሉ ከተማ እንደገቡ ራስ ሚካኤልን ፣ ራስ ወሌን ፣ ራስ መንገሻ አቲከምን ፣ ራስ መኰንንን ፣ ራስ አሉላን ፣ ዋግሹም ጓንጉልን ፣ ደጃች ወልዴን ፣ ፊታውራሪ ገበየሁን ፣ ፊታውራሪ ተክሌን ፣ ሊቀ መኳስ አድነውን ፣ ቀኛዝማች ታፈሰን ፣ “ ቀድማችሁ ወደ አላጌ ዝመቱ ። የሚቀላችሁ እንደሆነ ውጉት ። የሚከብዳችሁ እንደሆነ ወደኔ ላኩብኝ ” ብለው አስቀድመው መላካቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሲያረጋግጡ[1] አንዳንድ ጽሑፍ ደግሞ ፣ “ እኔ እስክመጣ ድረስ ከባችሁ ተቀመጡ እንጂ አትዋጉ ” ብለው እንደነበረ ያመለክታል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ይህ ግንባር ቀደም ጦር በራስ መኰንን አበጋዝነት ከወረይሉ ተነሥቶ በመጓዝ ላይ እንዳለ ከደብረ ኃይላ ጦርነት የመጡት ራስ መንገሻ ከነጦራቸው በአሸንጌ ሲጠባበቁ ነበርና ከነራስ መኰንን ጋር ተገናኝተው ሁሉም ጉዟቸውን ወደ አላጌ ቀጠሉ ። ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተለው ፖለቲካ ኢጣልያኖችን በሰላም ለማስወጣት ስለሆነ ፣ ራስ መኰንን አላማጣ ላይ ሳሉ እ. ኤ. አ በኅዳር 26 ቀን 1885 ዓ. ም. ከዚህ የሚከተለውን ደብዳቤ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ላኩለት ። ያማርኛው ደብዳቤ ስለማይገኝ ትርጉሙን ከፈረንሳይኛ ወደ አማርኛ በቃል ስንመልሰው እንደዚህ የሚል ነው ።

ለታወቀው ወዳጄ ለጄኔራል ባራቲዬሪ የኤርትራና የአካባቢው አገረ ገዥ ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

የተላከ ከራስ መኰንን የሐረርና የዙሪያው አገር ሁሉ ገዥ ። የኔን ጤንነት ማወቅ የፈለጉ እንደሆነ እስካሁን ድረስ ደህና ነኝ ። ሐረር የነበርሁ ጊዜ ለኛም ለናንተም መንግሥት የሚበጀውን ከፌልተር ጋር ተነጋግረን ነበር ። አሁንም ደም በከንቱ ሳይፈስ ጉዳዩን ሁለታችን በግል ተነጋግረን ብንፈጽመው መልካም ነው ። ግርማዊነታቸው እኔን ወደ ትግሬ ሲልኩ ከሁሉ በፊት ከእርስዎ ጋር ተነጋግሬ ለመጨረስ ነው ። የሚበጀውን በቶሎ እንዲልኩብኝ ተስፋ አለኝ ። ሙሴ ፌልተር እንደሌለም ፈልገው ካለበት ያስጠሩት ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 230—231 ።

ይህን ደብዳቤ ከአላማጣ ከራስ መኰንን የተላኩት ሰዎች አንላዕ ድረስ ወስደው ፣ ለቶዜሊ አደረሱ ። ቶዘሊ ለገኔራል አሪሞንዲ ከሰጠው በኋላ ፣ እርሱ ደግሞ የደብዳቤውን አጭር አሳብ በቴሌግራም አዲግራት ለሚገኘው አለቃው ለገኔራል ባራቲዬሪ አስታውቆ እንደዚህ የሚል መልስ መጣለት ።

ከራስ መኰንን ጋር ንግግር ለመጀመር ፈቃዱ መሆኑን ፌልተርንም ከዘይላ አስጠርቼ እንደማስታውቀው የምንገናኝበትን ቦታ ራስ መኰንን እንዲያስታውቀኝ ፣ እስከዚያ የሁለታችንም ጦር ወደፊት ሳይሔድ በያለበት እንዲቆም ተዋጉ ብዬ እንዳላዝ የራስ መኰንንም ጦር የጦር ማጥቃት ነገር እንዳይፈጽም ለራስ መኰንን አስታውቅ ።

ይኸን የመሰለውን አሳብ ለገኔራል አሪሞንዲ አስታወቀ ። እንደዚሁም ፣ " የምንገናኝበትን ሁኔታና ሥፍራ እየተነጋገርህ ቆይ " ብሎ ለማዦር ቶዜሊ ትእዛዝ አስተላለፎ ፣ ጉዳዩንም ሮማ ላሉት አለቆቹ ካደረሰ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ደብዳቤ በቀጥታ ለራስ መኰንን ጻፈላቸው ።

. . . ሰላምና ጤና ለርስዎ ይሁን በሙሉ ጤንነት ስለ መገኘትዎ ደስ ብሎኛል ። እኔም ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁንና ደህና ነኝ ። ድልን ባገኝ እንኳን ጦርነት ተደርጎ የክርስቲያን ደም መፍሰሱ ለኔ በጣም ያሳዝነኛል ። ሁለታችን ተገናኝተን ደም የሚፈስበትን መንገድ ብናስወግድ በጣም ደስ ይለኛል ። ንጉሣችን ኡምቤርቶ ምኞታቸው ይኸው ነው ። ስለዚህም ከርሳቸው ሙሉ ሥልጣን ተቀብያለሁ ። እርስዎም ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ሙሉ ሥልጣን ተቀብለው እንደሚመጡ እምናለሁ ።

ስለዚህም የምንገናኝበትን ዝርዝር ጉዳይ እንዲያዘጋጅ ለማዦር ቶዜሊ ልኬበታለሁ ። ከርስዎም በኩል አንድ ሰው ተወክሎ ወደ ማዦር ቶዜሊ እንዲላክ ፤ ሙሴ ፌልተርም ከርስዎ ጋር ያደረገውን ንግግር ገልጾልኛል ። ወዳጆችም ስለሆናችሁ ከዘይላ ተፈልጎ እንዲመጣ ልኬያለሁ ። ስለ ሀገርዎ ምንም ፍርሃት አይሰማዎት ። እግዚአብሔር ለርስዎና ለመላዋ ኢትዮጵያ ጤንነት እንዲሰጥ እመኛለሁ [1] ።

ራስ መኰንን የጻፉለት እ.ኤ.አ. ኅዳር 26 ቀን ሲሆን ፣ እርሱ የመለሰው ከስምንት ቀን በኋላ በታኅሣሥ 3 ቀን ቢሆንም መልሱ በፍጹም ሊደርሳቸው አልቻለም ። በዚህ ዐይነት ከባራቲዬሪ ጋር የመጻጻፉ ጉዳይ ውጤት አልሰጠም ። የተፈለገው ፌልተርም በጊዜው አልተገኘም ። ስለዚህ ያን ሁሉ ሠራዊት ይዘው እንደዚሁ መቆየት ስለአልቻሉ ፣ እዚያው አጠገባቸው ለሚገኘው ለማዦር ቶዜሊ መጻፍ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፈው ላኩለት ።

1 Memoire d'Afrique , Baratieri, P. 263.



"የመጣሁት ጦርነት ለማድረግ ነው ያስከተልሁትን ጦር እንደዚሁ ሳሰናብተው አልችልም ። የባራቲዬሪ ወዳጅነት ስለያዘኝ የሰላም እማካይነት ለማድረግ ፈልጌ ነበር ። ከገኔራል ምንም መልስ ስለአልመጣልኝ ንጉሡም ከአሸንጌ ወዲህ ስለ ተጠጉና እኔም መንገዱን ይዤ ከቆምሁ መተላለፊያ አያገኙም ።"

ቶዜሊም ለዚህ ደብዳቤ ቀጥሎ ያለውን በድንፋታ የተሞላ መልስ ሰጠ ።

የባራቲዬሪን መልስ ጠይቀኸኛል ደብዳቤህን ልኬዋለሁ ። በታኅሣሥ 2 ለጻፍከው በ4 ታኅሣሥ መልሼልሃለሁ ። ወደፊት መጓዝህ ለሰላም ከአለብኸው ጋር ይጋጫል ። ወደፊት መራመድ ጦርነት ፍለጋ ነው ። ከዚህም ጦርነት የሚከተለውን ማንም መጥና ሊያውቀው አይችልም ። ለመሔድ መነሣት የሰው ችሎቱ ነው ፣ የመድረሱ ነገር ግን በእግዚአብሔር እጅ ነው ። በመቅደላና በሰሐጢ የሁለት ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዕድል ተወስኗል ። ሦስተኛው ንጉሠ ነገሥት ከሰሎሞን ዙፋን ይወጣ ዘንድ ኢጣልያ ለመርዳት ብትደስትም ፣ ከሰባት ዓመት በፊት የሠራችውን መልሳ ለማፍረስ ችሎት አላት ። [1]

ዋናው መሪ ባራቲዬሪ ፣ ለራስ መኰንን በርስዎታ ሲጽፍ ቶዜሊ አንባቢ እንደ ተመለከተው በአንተታ ነው የጻፈው ። የአጻጻፍ ሥነ ሥርዓት አለማወቅ ይሁን ወይንም በንቀት አለዚያም በትርጓሜ ስሕተት አይታወቅም ። አጻጻፉ ፍጹም ድንፋታና ትምክህትን የተመላ ስለሆነ በንቀትም ሊሆን ይችላል ። ሁለቱ ነገሥታት ዐፄ ቴዎድሮስና ዐፄ ዮሐንስ ሕይወታቸው በመቅደላና በመተማ እንዳለፈ ፣ የሦስተኛውን ንጉሠ ነገሥት የምኒልክን ሕይወት እኛው የገነባነውን መልሰን እናፈርሰዋለን ባይ ነው ። መተማ እላለሁ ብሎ በስሕተት ሰሐጢ ብሏል ። " ከሰባት ዓመት በፊት ኢጣልያ የሠራችውን መልሳ ለማፍረስ ችሎት አላት " ብሎ የሚጠቅሰው ፣ ኢጣልያ በሰላሙ ጊዜ ለዐፄ ምኒልክ ያቀበለችውን የጦር መሣሪያ እርዳታ መጥቀሱ ነው ወይም መሣሪያ አቀብለን ያደራጀነውን የምኒልክን መንግሥት እኛው እናፈርሰዋለን ለማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ የሰላሙ ነገር ከዚሁ ላይ ስለቆመ ይኸን ደብዳቤ በታኅሣሥ ፪ ቀን ጽፎ እንደላከ በ፭ኛው ቀን ጦርነቱ ተደርጎ አልኸኛውና ደፋሩ ቶዜሊ የምኒልክን መንግሥት አፈርሳለሁ ሲል የራሱን ሕይወት አጣ ።

1 Adua, E. Bellavita, PP 243 - 244.
ደብዳቤዎቹ የተተረጐሙት ከኢጣልያንኛው ጽሑፍ መሆኑን እመለከታለሁ ።



ራስ መኰንን ወ/ሚካኤል በዓድዋ ጦርነት ጊዜ
ከሞንታዶኤ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሐያ ሰባት

## የአምባ አላጌ ጦርነትና ድሉ

ራስ መኰንንና ማዦር ቶዜሊ ፣ እነዚያን ደብዳቤዎች ከተለዋወጡ በኋላ ፣ ራስ መኰንን ከበው መጠባበቅን እንጂ ፣ በቶሎ በጦር ማጥቃቱን የፈለጉ አይመስልም ። ምናልባት እርሳቸው ቶዜሊ ስድስት ራሶች ያሉበትን ጦር ደፍሮ በመውጋት ፈንታ ጦሩን ይዞ ወደ አዲግራት ይመለሳል የሚል ግምት አድሮባቸው ይሆናል ።

ነገር ግን ፣ ቶዜሊ ባንድ ወገን ያለበት ምሽግ ለመመከት ምቹ መሆኑን ፤ በሌላ ወገን "የኢትዮጵያውያን ጦር ምንም ቁጥሩ ቢበዛ የድርጅቱ ክንውንና የመሣሪያው ጥራት ከኛ ያነሰ ነው" የሚል የንቀት ግምት ስለ አደረበት ፣ ከዚህ ሁሉ ጋር ከዚህ በፊት ባደረጋቸው ጦርነቶች እየቀናው ዝብዱው በነጮችም ፣ በጥቁሮቹም ዘንድ ደምቆ የታወቀለትና በዚህም የሳቮያ ኦርድር ሚሊቴር ኒሻን ተሸልሞ ስለ ነበረ ፣ ባሁኑ ጦርነት ሌላ ዝብዱ ሠርቶ ሌላ ሽልማት በመመኘት ጦርነቱን ራሱ ዐውቆ እንደ ፈለገው አይጠረጠርም ። በዚህም ላይ ዕድሜው ዐርባ ዓመት የአፍላነትና የሙሉ ሰውነት ጊዜ ነበረ ። ይህ የአፍለኛነት ዕድሜ በኢጣልያዊ ግንፍል ደም ላይ ሲጨመር ፣ በሁሉም መጋጋልና መደንፋት በዚህ ዘመን ያለ የኢጣልያ ጦር መኰንን ዐይነተኛ ሥዕል ነው ። ስለዚህ በየተራራው ዙሪያ የኢትዮጵያ ጦር እንደ ሠፈረ ከዚህ በፊት ያወሳናቸውን የጦር ሹማምንት ከዚህ እንደሚከተለው አሰልፎ ለመዋጋት ወሰነ ።

አንደኛ ፣ የራስ ስብሐትና የደጃች ዓሊ ጦር ግንባር ቀደም ሆኖ ፣ ከኋላው በቀኝ በኩል የካፒቴን ኤሲል ክፍል ጦር እየደገፈው የመጀመሪያውንና የታችኛውን መስመር ይዞ እንዲዋጋ፤ ይኸም ያገር ተወላጅ የሆነውን አስቀድሞ በማዋጋት የነጩን ጦር ለመቆጠብ መሆኑ ይታወቃል ። ራስ ስብሐት በራስ መንገሻ ትእዛዝ ከታሰሩበት ፣ ከአምባ ሰላማ ፣ አሪሞንዲ ካስፈታቸው በኋላ ባሁኑ ጊዜ በግድም በውድም የኢጣልያኖቹ መሣሪያ ሆነዋል ማለት ነው ።

ሁለተኛ ፣ ከኤሲል ክፍል በስተቀኝና በመካከል ከአላጌ መንገድ ጋር የሚያገናኘውን ሥፍራ ይዞ የካፒቴን ካኖቬቲ ክፍል ጦር ፈሳሹን ወንዝ ተከትሎ ፤

ሦስተኛ ፡ የካፒቴን አንጌራ ጦር በኋላው በካፒቴን ፔርሲኮ ጦር እየተደገፈ በቀኝ በኩል ከአምባው ባንደኛው ዘቅዛቃ ሥፍራ ፤

አራተኛ ፡ የሼህ ጠልሃና የቲኔንቲ ቮልፒቼሊ ጦር የተወሰነ ባንዳ ጨምሮ በቀኝ በኩል ያለውን የቶጉራንና የሙጃን መተላለፊያ መንገድ በመያዝ ፤

አምስተኛ ፡ የካፒቴን ሪቺ ፡ የካፒቴን ብሩዚ እና የካፒቴን ፓጀላ ጦር ከኋላ ደጀን እንዲሆን አሰልፎ እ. ኤ. አ. በታኅሣሥ 7 ቀን 1895 ዓ.ም. (ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም.) ጦርነቱ ተጀመረ ።

በኢጣልያኖቹ ጽሑፍ ፡ የጦርነቱ ከፋች ራስ ወሌ መሆናቸውን ያመለክታል ። በኛ በኩል ግን ፡ የጦርነቱ ጀማሪ ፊታውራሪ ገበየሁ መሆናቸው በብዙ ሰነድ የተደገፈ ነው ። እርሳቸውም ባንድ ወገን ከዚህ በፊት በዶጋሊ ጦርነት ራስ አሉላ እንዳሉት ፡ ለጌታዬ ላፄ ምኒልክ ድግስ እንጂ ፡ የጦር መስተንግዶ እንዲጠብቃቸው አላደርግም በማለት ፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቶዜሊ ጦር ፊት ለፊት መድፍም እየተኰሰ እያላገጠም ስለ አበሳጫቸው ፡ ከጠቅላይ አዣዥ ከራስ መኰንን ትእዛዝ ሳይጠብቁ ጦርነቱን ከፈቱ ። እንደ ርሳቸው ጀግንነት የሚስማቸው ቀኛዝማች ታፈሰና ፊታውራሪ ተክሌ ተከታትለው ሔደው ውጊያውን አማሙቀው ቀጠሉ ።

በዚህ ጊዜ ፡ ራሶቹ ሁሉም በየድንኳናቸው ስለነበሩ የተኩሱን ድምፅ በመስማት የጦር መሣሪያቸውን ታጥቀው ከየድንኳናቸው ወጥተው ወደ ጦርነቱ ሲያመሩ ፡ ሹም አጋሜ ተስፋዬ የአላጌን ምሽግና አቀማመጥ የሚያውቁት ወደ ራሶቹ ቀርበው ፡ "የአላጌ በር እንኳን ጠመንጃና መድፍ ተጠምዶበት በደንጊያ እንኳን አንድ ሰው ሊከላከል ይቻላልና አልጋውን እንዳታፈርሱት በምኒልክ አምላክ ወደየድንኳናችሁ ግቡ" ብለው ተማጥነዋቸው ነበር ። ራሶቹ ግን ፡ እርስ በርሳቸው ተመካከረው ፡ "እኛ እዚህ ተቀምጠን የንጉሡን አሽከር ፊታውራሪ ገበየሁን ዝም ብለን እናስገድለዋለን" ተባብለው ወደ ጦርነቱ ቦታ ሔደው ገጠሙ ። ፊታውራሪ ገበየሁም ምንም እንኳን ሰምኑን ታመው ቢሰነብቱ በበቅሎ ሆነው ዘንጋቸውን ይዘው ፡ "እይዞህ ጥይትም ያለቀብህ በጐራዴ በለው" እያሉ ወታደሩን እያደፋፈሩ ማዋጋታቸውን ከራስ መንገሻ ዮሐንስ መላከተኛ የሰሙትን ማስታወሻ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አስቀርተውልናል ።[1]

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . .ገጽ 240—245 ።



ስለዚህ ፊታውራሪ ገበየሁ ፡ ወደ ከፈቱት የጦርነት ቦታ ራሶቹ ደርሰው በቀኝ በኩል የራስ ወሌ ጦር በራስ ስብሐትና በካፒቴን ካኖቪቲ የሚመራውን ፡ በመካከል የራስ መኰንንና የራስ ሚካኤል ጦር የኤሴልንና የፔርሴኮን ጦር ፡ በስተጀርባ የራስ መንገሻና የራስ አሉላ ጦር ከሼክ ጠልሃና ከአንጌራ ጦር ጋር ውጊያ ገጠሙ ። በራስ ወሌ ግንባር ያለው በራስ ስብሐት የሚመራው ጦር ተዳክሞ ወደ ኋላው ተመልሶ ከሚደግፈው ከኤሴል ጦር ጋር ተደባልቆ በመመከት ተዋጋ ። ራስ መኰንን ቀደም ብለው ከካፒቴን ካኖቪቲ ጦር ጋር ሲዋጉ ወዲያው ለርዳታ የራስ ሚካኤል ጦር ደርሶ ሲያጠቃ ፡ በዚህ ግንባር ያለው የኢጣልያ ጦር ምንም በርትቶ ቢከራከር አልሆነለትም ። ከአምባ አላጌ ምሽግ ጀርባ በምዕራብ በኩል የዘመቱት እነ ራስ አሉላም በበኩላቸው ሲያጠቁ ፡ የኢጣልያ ጦር እስከ ረዥም ጊዜ ድረስ ሊመክት አልቻለምና በቅድሚያ የሼክ ጠልሃ ጦር ሽሽት ጀመረ ።

ዋናው አዝማች ማዦር ቶዜሊ ፡ ወዲያና ወዲህ እያለ ጦሩን ሲያዋጋ ፡ የጦሩ ግንባር ሰፊ መሆኑን በመመልከት ፡ በየአለበት የአለውም ጦር የመከበብ አደጋ እንደ ገጠመው ተረዳ ። የጦሩን ግንባር ለማጥበብና ኃይሉን ለመሰብሰብና ለማዋጋት ከሞከረ በኋላ ፡ የሁሉም መዳከም ስለ ተቃረበ ፡ ተጠባባቂውንም ጦር ጨምሮ ሪቺ ፡ ኤሴል ፡ ካኖቪቲ በመጨረሻ ኃይላቸው እንዲዋጉ አዘዛቸው ። እነርሱም እንደ ታዘዙት ሲዋጉ ከመካከላቸው ካፒቴን ሪቺ ተመትቶ ወደቀ ።

በዚሁ መካከል ፡ አስቀድሞ እርዳታ እንዲመጣለት መቀሌ ለጄኔራል አሪሞንዲ ልኮ ነበርና መጣ አልመጣም እያለ ወዲያና ወዲህ እየተንቆራጠጠ ሳለ ፡ ውጊያው ጧት የጀመረ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ከቀጠለ በኋላ የኢጣልያ ጦር ሽሽት ጀመረ ። ቶዜሊ ሁሉም ጦር ወደኋላው ተመልሶ ፡ ከተረፈው ተጠባባቂ ጦር ጋር ሆኖ በመጨረሻ ኃይል እንዲዋጉ አዘዘ ። የመጨረሻው ጦርነት በሚደረግበት ላይ ብዙ እልቂት ደርሶ ፡ በዚሁ ጦርነት ብሩዚና ሙላዛኒ እየተመቱ ወደቁ ። የሙቶ አለቃ ስካላ ከነሕይወቱ ተማረከ ። ካፒቴን አንጌራም ክፉኛ ቆሰለ ። ከመድፍ ተኳሾች ውስጥ የሱዳን ተወላጆች ነበሩና አበሾቹ ከሚማርኳቸው ብለው መድፎቻቸውን እንደ ተጫኑ ከነበቅሎቻቸው እየገፉ ገደል ሰደዷቸው ።

ከዚህ በኋላ ፡ ወታደሩ ምሽጉን እየለቀቀ በቶጐራ መንገድ አድርጎ በያለበት እየተዘበራረቀ ሸሸ ። ማዦር ቶዜሊም ፊቱን በሐዘንና በንዴት እንዳጨመደደ ወደታች ሲወርድ ፡ መንገዱን የራስ አሉላ ሰዎች ዞረው እንደ ያዙበት ተመለከተ ።በዚያን ጊዜ አንዳንዶቹ ፡ እንደ ሌሎቹ ራሱን እንዲያድን ቢመክሩት ፡ "ያደረጉትን ያድርጉኝ" ብሎ

ወደ ጠላቶቹ ፊቱን እንደ መለሰ ወዲያው ከደረቱ ላይ ተመትቶ ወደቀ ። በወቅቱም "አላጌ እበሩ ላይ ሲወድቅ ማገሮር ፣ እንደ ግራኝ ሁሉ በሰባት አረር" (ጥይት) ተብሏል ።

በዚህ ዐይነት ፣ አለቅዬው ተመትቶ ሲወድቅ በኮዓቲት ፣ በስንዓፌ ፣ በደብረ ኃይላ ራስ መንገሻ ዮሐንስንና ጦራቸውን በያለበት ሲያሳድድ የኖረው ያራተኛው ባታዮ ጦር በዚህ ዓይነት ፍርስርሱ ወጣ ። የቆሰለውም ፣ ደህናውም ፣ ነጩም ያገር ተወላጁም በየግንባሩ ወደ መቀሌ አቅጣጫ ይሸሽ ጀመር ። [1]

በመጀመሪያ ላይ እንደ ተመለከትነው ፣ ጦርነቱ በጠቅላይ አዛዥ በራስ መኰንን ትእዛዝ ሳይሆን በአበጋዙ በፊታውራሪ ገበየሁ ስለተከፈተ ፣ ምንም እንኳን ድሉ የኢትዮጵያውያን ሆኖ ራሳቸውም በደንብ የተካፈሉት ቢሆን ፣ የጦርነቱ ጉዳይ በድል አድራጊነት ከተደመደመና የመጀመሪያውን የጦር ኃይላቸውን ከአሳዩ በኋላ ፣ ራስ መኰንን ጦርነቱን ያለትእዛዝ የጀመሩትን ፊታውራሪ ገበየሁንና ቀኛዝማች ታፈሰን አሰሩዋቸው ። የአምባላጌን የድል የምስራች ወሎ ግዛት ውስጥ ለሚገኙት ላፄ ምኒልክ ለመንገር በደብዳቤና በቃል አሽከራቸውን የላኩ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ናቸው ።

ደብዳቤውም እንደዚህ የሚል ነው ።

> ይድረስ ከሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መድኃኔዓለም ጤና ይስጥልኝ ብዬ እጅ እነሣለሁ ። ልጅዎ ራስ መንገሻ ። ጃንሆይ ጦርነቱ አልታሰበም ነበር ። ፊታውራሪ ገበየሁ ሔዶ ገጠመው ። እኔም በጀርባው መኳንንቱም በግንባር ገቡበት ። ከመኳንንቱ ሠራዊቱ ፣ ከሠራዊቱ መኳንንቱ እንደዚህ ያለ ተዋጊ ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም ። ይህ ሁሉ የሆነ በምኒልክ ሀብት ነው ። ፈረንጅ እንኳን መድፍና ወጨፎ ይዞ የአላጂ (አላጌ) አምባ ሲሰበር ፣ ከጥንት ባባቶቻችን በደንጊያ ይመለስ ነበር ። ከዚህ በፊት ተደርጎ የማያውቅ ዛሬ በምኒልክ ሀብት ተደረገ ። እንግዲህም የምኒልክ ሀብት ይጠብቀናል ። በ10 ወ 108ወ8ቱ (1888) ዓ.ም. እመ 4ቱ ለታኅሣሥ ተጻፈ ። ማኅተም ራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ 2

የጦር የበላይ አዛዡ ራስ መኰንን እያሉ ፣ ራስ መንገሻ የጦርነቱን የድል ወሬ ለመግለጽ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ የላኩበት

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 239 - 241, Italia ed Etiopia, Conti - Rossini, PP. 197 - 208. Lettere e Diari F.Lemmi , PP. 9-20.

2 ከፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከምንጆን ቪዳዬ ዶሲዬ ፣ ቁ.82



ምክንያት ለአንባቢም ለጸሐፊም ግር ሳያል አይቀርም ። ምክንያቱን ስንመረምር ምንም እንኳን ራስ መኰንን የጠቅላላው የጦር አበጋዝ ቢሆኑ ፣ ራስ መንገሻ ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ የዐፄ ዮሐንስ ልጅ በመሆናቸው ፣ በክብርም በማዕረግም ከራስ መኰንን በዚያን ሰዓት ከፍ ብለው ስለሚታዩ ፣ በዚህም ላይ ጦርነቱ የተደረገበት የአምባአላጌ ሠፍራ በራስ መንገሻ ግዛት ውስጥ ስለሆነ ፣ የበላይነት መብት ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብለው እንደሆነ አይታወቅም ። ይሁን እንጂ መላከተኛው ፣ የድሉን ብሥራት ላፄ ምኒልክ ይነግር ዘንድ በቃል የላኩት ራሶቹ በኅብረት ይመስላል ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ከአዲስ አበባ ተጉዘው ወረይሉ (ወሎ) እንደ ደረሱ ፣ ከዚያ በኅዳር 23 ቀን ውጫሌ ባሻ ጮፌ ፣ ከዚያ በመርሳና በጭራ ወንዝ ፣ በአላ ወንዝና በጉሊማ አድርገው ሆርማት ላይ በሠፈሩበት ጊዜ የአላጌን ጦርነት ሰሙ ። በታኅሣሥ 1 ቀን ከሆርማት በማይ ሽምበቆ ፣ በቢትሞ አድርገው ፣ አላማጣ ደርሰው ድንኳን ተተከሎ ሰፈር ሆነ ። በአላማጣ እንደ ሰፈሩ ይኸን ደብዳቤ የያዘው ፣ በቃልም የተላከው ፣ የራስ መንገሻ መላከተኛ ወደፊት ቀድሞ በየተራራው ላይ የሚጓዘውን ወታደር እያቋረጠ ፣ እየተንደረደረ ሲሮጥ የሚጓዘው ሰው ባየው ጊዜ ፣ "ከወዴት መጣህ እባክህ ወሬውን ንገረን" ቢሉት ፣ 'እኔ ከራሶቹ ዘንድ ነው የመጣሁት ፣ አላጌ ላይ የዘለቀው ጦር ኢጣልያኑም አለቀ ፣ መድፉም ነፍጡም ተማረከ" ብሎ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር በግሥጋሴ ደረሰ ። ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት ድንኳን ገብቶ ፤

> "ኢጣልያኑ አላጌን አምባውን ይዞ መድፉን አልቦ ነፍጡን ሰልፎ ተቀምጦ ነበር ። ፊታውራሪ ገበየሁ ወደፊት ቀድሞ ሲጓዝ ፣ ፊት የቀደመው የርሱ ጦር ከኢጣልያው ዘበኛ ጋር ተገናኝቶ ተታኮሰ ። ፊታውራሪ ገበየሁም ከሹማምንቱ ጋር እንዲህ አለ ። እንግዲህ ይህ ጦር አምሮብን ሳለ ለጌታችን አልጋ መሞት ይገባናል ...እንዲህም ተባብለው ጭፍራው አንድ ጊዜ ገባበት ። አምስቱን ክቢ እንደሻረው ተኩሱ ከነራስ መኰንን ሰፈር ተሰማ ... እነሱም ከየድንኳናቸው ታጥቀው ሲወጡ ... ሹም አጋሚ ተሰፋዬ ... አይሆንም ብሎ አግጠናቸው ... ራሶቹ ከዚህ ተቀምጠን የጃንሆይን አሽከር ገበየሁን እናስገድላለን ብለው እየተሰለፉ ሔዱ ። ሠፍራውም እንኳን ለከብት ለእግረኛም ቢሆን እጅግ የከፋ ገደል ነበር ። ስዉ ግን ፣ የመድፉንም የነፍጡንም ተኩስ ቁም ነገር አላለው ። እጅ ለጅ ተያይዞ ዕፁብ ድንቅ ተብሎ የተመሰገነ ውጊያ ተዋግቶ ድል አድርጎ ፈጀው ። ....ነገር ግን ፣ ፊታውራሪ ገበየሁንና ቀኛዝማች ታፈሰን ሳይታዘዙ ስለተዋጉ አስረናቸዋል ብለዋል ራሶቹ ።"

ሲል ለንጉሠ ነገሥቱ መንገሩን የጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ያረጋግጣል ።

ከዚሁ አያይዞ ፥ ዐፄ ምኒልክ መልክተኛውን ሸልመው ፥ “እኔም መጣሁ ። እግዚአብሔርም ሁልጊዜ ቀኙን ለኛ ያድርገው” ብለው መልሰው እንደ ሰደዱት ፥ በዚያም ሰሞን ልጁም ፥ ዐዋቂውም “ገበየሁ ገበየሁ “እያለ እንዳነሣው ፥ “ጐበዝ አየሁ” የሚል ሥያሜም እንዳወጣለት የጸሐፊ ትእዛዙ ጽሑፍ ያመለክታል ።[1] በዚህም ጊዜ —‘ ከነፍጥ ጐበዝ ፥ አየሁ (የጠመንጃ ስም) ከአሽከር ገበየሁ’ ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።

የአላጌ ጦርነት በንጉሠ ነገሥቱም ፥ በራስ መኰንንም ዘንድ እንዳልተፈለገና ንጉሠ ነገሥቱ የአላጌን የጦርነት ወሬ አዲስ አበባ ላሉት በአሳብም ፥ በምክርም ፥ የጦር መሣሪያም በማቀበል ፥ ለሚረዱዋቸው ፈረንሳዮች በላኩት ደብዳቤ ላይ ገልጸውታል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፥ ካዲስ አበባ በዐዋጅ ሠራዊታቸውን ሰብስበው የሔዱት ለጦርነት መሆኑ ራሱ የከተቱ ዐዋጅ በግልጽ ያስረዳል ። ነገር ግን ፥ በዚህ ዘመን ምዕራባውያን የእስያንና የአፍሪካን ዓለም ተከፋፍለው የያዙበት ፥ ጠባቸው የሚያስፈራ ፥ ሥልጣኔያቸው የሚጠቅም መሆኑን በደንብ ስለ ተረዱት ፥ በተቻለ መጠን “አጥቂ” መስሎ አለመታየትን ዋና ዓላማ አድርገው ይዘውታል ። በአዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገር ወዳጆቻቸውም የሚመክሩዋቸው ይኸንኑ ነው ። ስለ ኢጣልያ ንጉሥና ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች በጻፉ ቁጥር ንጉሠ ነገሥቱም ፥ ራስ መኰንንም በደብዳቤያቸው ውስጥ ደጋግመው የሚጠቅሷቸው ዐረፍተ ነገሮች አንደኛው ፥ “ጉዳያችንን በሰላምና በወዳጅነት እንጨርስ” ሁለተኛው ፥ “የክርስቲያን ደም በከንቱ አይፍሰስ” የሚሉ ናቸው ።

የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ግን ፥ ይኸን አቋም የፍርሃት አድርገውት እነዐፄ ምኒልክ እንደሚመኙት የያዙትን ወረዳ ሁሉ በሰላም ለመልቀቅ አልፈለጉም ። በራሳቸው ጉልበትና በሥልጣኔያቸው በመመካት ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሌላው የአፍሪካ ሕዝብ ሁሉ በመናቅና በማኮሰስ ፥ እንደገና ከያዙት እያለፉ አዲስ ወረዳ በመያዝ ፥ ለኢጣልያ የቅኝ አገር መፍጠርን በበኩላቸው ዓላማ አድርገው ይዘውታል ። እስከ አላጌም የደረሱት በዚሁ ዓላማ መሆኑን ባለፈው አመልክተናል ።

ስለዚህ ፥ ዳግማዊ ምኒልክ መቀሌ ከገቡ በኋላ ፥ የአላጌን ድል አዲስ አበባ ላሉት ፈረንጆች ሲጽፉ አድራሻውን ለሙሴ ሞንዶን

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፥ ገጽ 241 ።



ቪዳዬ አድርገውለታል ። ምክንያቱም ሞንዶን በዚህ ጊዜ “ለታ” ለሚባለው ለፈረንሳይ ጋዜጣ ወኪልና ለንጉሠ ነገሥቱም ወዳጅ ስለ ነበረ ነው ። ጣልያኖቹ ኢትዮጵያንና አስተዳደሩን እያጥላሉና እረመኔ እያስመሰሉ በመጻፍ ወረራቸውን “የሚገባ ነው” ለማስኘት ፥ በአውሮፓ ወሬያቸውን በጋዜጣ ሲነዙ ፥ እርሱ ከአዲስ አበባ እየጻፈ በመላክ የጣልያኖቹን ፕሮፓጋንዳ የሚያስተባብል ፥ ዐፄ ምኒልክን በማሞገስ ከልብ የሚደግፍና አማርኛም የተማረ ነበር ።

ከንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈለትን ደብዳቤ እንደሚከተለው እንመልከት ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን ። እንዴት ሰንብተሃል ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። ከናንተ ከተለያየሁ ኢጣልያኖችን እጅግ አልገፉም ብዬ ነገሩን በዝግታ ይዤው ነበር ። በዝግታ መያዜ ግን ፥ የክርስቲያን ደም ሳይፈስ በመካከሉ ድንገት እነዚያን የሚያስታግሥ ምክር ከአውሮፓ ይመጣል ብዬ ነበር ። ኋላ ግን ነገሩን አስተውዬ ባየው ከቶ እኔ የፈራሁ እነሱ የበረቱ መሰሏቸው አሸንጌ ድረስ በር ለመያዝ መጡ ። የኔም ሠራዊት አስቀድሜ የሰደድኳቸው መኳንንት ሁሉ ሳይደርሱ የኢጣልያ ወታደር የፊተኛውን ጦር አዘላስቅ አይቶ ተመልሶ አላጌ ላይ በሩን ይዞ ሰፈረ ። የኔም ጦር ተከትሎ ከአላጌ ወዲህ አይባ ላይ ሰፈረ ። ከዚህ በኋላ ሰፈሩን እያዩ ጣልያኖች መተኮስ ጀመሩ ። የኔም ወታደር አላስችል ቢላቸው ካለቆቻቸው ትእዛዝ ሳያገኙ ወጥተው ጦርነት ገጥመው በኅዳር 28 ቀን ድል አድርገው ፈጁት ። የፊተኛው ጦር ዐሥራ ሁለት አለቆች ይዞ የመጣ ማጆር ቶዜሊ ነበር ። ከርሱ ስምንት ሞተዋል ፤ ሁለቱ ተማረኩ ። ዥኔራል ባራቲዬሪ * ለርዳታ መጥቶ እመንገድ ሲደርስ ድል ያደረገው የኛ አባራሪ ጦር ቢደርስበት ጥቂት ራሱን ሆኖ ከዚያ ሸሽቶ መቀሌ ከርዱ ገብቶ የኛ ጦር ከቦት ተቀምጧል ። አሁንም ደስ ብሎኛል ደስ ይበልህ ። ሁሉንም እንድታውቀው ራስ መንገሻ የሰደደልኝን ደብዳቤ ሰድጄልሀለሁ ። ደስታውንም ላንተ መላኬ የሁሉም ሽማግሌ ነህና አዲስ አበባ ላሉት ፈረንጆች ሁሉ እንድትነግራቸው ይሁን ። ለቀሩት ፈረንጆች ሁሉ አለመላኬ ደብዳቤ ችኮላ ቢሆንብኝ ነውና ለሁሉም አንተ ንገርልኝ የራስ መንገሻን ደብዳቤ ከራስ ዳርጌ ተቀበል ።

በታኅሣሥ በ6 ቀን በአሸንጌ ሰፈር በ፲888 ዓ. ም. ተጻፈ ።[1]

* ባራቲዬሪ ያሉት አሪሞንዲ ለማለት ነው ። ቶዜሊን ለመርዳት መጥቶ በሽሽት የተመለሰው አሪሞንዲ እንጂ ፥ ዋንዬው ባራቲዬሪ አይደለም ። ምናልባት ወሬ ነጋሪያቸው አሪሞንዲ በማለት ፈንታ ባራቲዬሪ ብሏቸው ይሆናል ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቤት .. ከሞንዶን ዶሲዬ ፥ ቁ.82

ዳግማዊ ምኒልክ ፡ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ራስ መንገሻ ዮሐንስ የጻፉላቸውን ደብዳቤ በራስ ዳርጌ አማካይነት ለሞንዶን ቪዳዬ መላካቸው ፣ ምናልባት በዚህ ጊዜ ኢጣልያኖቹና ወገኖቻቸው “እነንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ እነራስ ሚካኤል ንጉሠ ነገሥቱን ከድተዋል ። ራስ መንገሻም ከድተው ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር እየተጻጻፉ ለጣልያን ሊገቡ ነው ” የሚባል ወሬ ይነፍስ ስለነበር ይሆናል ። ይልቁንም ራስ መንገሻ ፡ ምንም ራሳቸው ከኢጣልያኖቹ ጋር በኮአቲትና በሰንዓፌ ቢዋጉ አሁንም ለሚቀጥለው ጦርነት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቢሰለፉ ፣ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፡ የዙፋን ወራሽነቱ መቅረት እያደር እየቆጫቸው ውስጡን በኅዳር 23 ቀን 1887 ዓ.ም. ለኢጣልያ ንጉሥ ከጻፉ ወዲህ በነሐሴ 23 ቀን 1887 ዓ.ም. ደግሞ ለንግሥት ቪክቶሪያ ፣ “ መንግሥቴን ተቀምቼያለሁና እርዱኝ ” የሚል የጥያቄ ደብዳቤ ጽፈው ኖሮ ፡ በአላጌ ጦርነት ጊዜ መላክተኛው ካይሮ ደርሶ ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች መነጋገሩ በውጭ አገር ጋዜጣ ተጽፎ ነበር ።

ምናልባት ፣ የዚህኑ ወሬ ሞንዶን ቪዳዬ ከፈረንሳይኛ ጋዜጣ ላይ አንብቦ የራስ መንገሻን አለመታመን ላፄ ምኒልክ ጽፎላቸው እርሳቸው ደግሞ ለዚሁ የራስ መንገሻን መታመን ከደብዳቤያቸው ላይ እንዲረዳው ልከውለት ይሆናል ። ዳሩ ግን ፣ ራስ መንገሻ ባለፈው ዓመት ሁለት ጊዜ ከኢጣልያ ጦር ጋር ተዋግተው ያን የመሰለ የመሸነፍ አደጋ ደርሶባቸዋል ። ያንን ቁጭት ለመወጣት በጦርነት ከነራስ መኰንን ጋር ከመሰለፋቸው ከአራት ወራት በፊት ለንግሥት ቪክቶሪያ መጻፋቸው ፣ በእውነትም ኢትዮጵያውያን አንድነት የላቸውም ያሰኛል ። በወቅቱም የእንግሊዝ መንግሥት በምንም ዐይነት እርዳታ ለማድረግ እንደማይችል የታወቀ ነው ።

የአላጌ ጦርነት የተከናወነው ፣ ብዛቱ በተለያየ ወታደሮች መካከል መሆኑ አይጠረጠርም ። የኢትዮጵያውያኑ ቁጥር ከኢጣልያኖቹ ጸሐፊዎች በተሰጠው ግምት ከሃምሳ ሺ በላይ ባለጠመንጃ ሲሆን ፣ የኢጣልያኖቹ ከዚህ በፊት እንደ ተመለከትነው ሦስት ሺ አይሞላም ። ነገር ግን ፣ በደንበኛ አካዳሚካዊ የጦር ትምህርት የተዘጋጀ ወታደርና ይኸን ባላገኘ ወታደር ፣ እንደዚሁም ምሽግ ይዞ በሚመከትና ከውጭ በሚያጠቃ መካከል የተደረገ ጦርነት ስለሆነ ፣ የተዋጊ የቁጥር ልዩነት የሚጫነው በመጠኑ ነው ። ጥሩ የመሣሪያ ትጥቅ ያለው አንድ መቶ ወታደር እንደ አላጌ ያለውን ምሽግ በቅድሚያ ከያዘ መቶ ሺ ጦር ሊመልስ ይችላል ። እነሹም አጋሜ ተሰፋዬና ራሳቸው ራስ መንገሻም በቃልም ፣ በደብዳቤም የገለጹት ይኸንኑ ነው ።



የሆነ ሆኖ ፡ የአላጌ ጦርነትና ድሉ ለኢጣልያ መንግሥት ትልቅ የማስጠንቀቂያ ደወል ነበር ። ኢጣልያኖቹ ግን ፣ ይኸን የደወል ድምፅ ሰምተው በመማር ፡ ጉዳዩንም ዐፄ ምኒልክ እንደ ተመኙት በትዕግሥት ወደ ሰላም በማቅናት ፈንታ ፣ አውሮፓዊ ክብራቸው ባንድ ባልሠለጠነ አፍሪካዊ ጦር እንደ ተነካ በመቁጠር ፣ በኢጣልያም ፣ በኤርትራም ያሉት ሁሉ ከቀድሞው የበለጠ አበክረው በመናደድ የሚበቀሉበትን ጊዜና ሥፍራ ይመርጡ ዠመር ። አዳዲስ ጦርም ከኢጣልያ አገር ወደ ኤርትራ የሚመጣው ፍጥነቱ ከዚህ በፊት ከነበረው ይበልጥ ተቀላጠፈ ። ቢሆንም ከኮዓቲትና ከደብረ ኃይላ ጦርነት ድል በኋላ ፣ ይህ የአላጌ ሽንፈት ኤርትራ ባሉት የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ዘንድ ፣ “በፍጹም የማንበገርና የማንደፈር ነን” የሚለው ልባዊ የትምክህት እምነት አጠራጣሪ ሆነ ። በአላጌ ውጊያ ኢጣልያኖች አስገድደው ባሰለፉት የኤርትራ ፣ የደንከል ፣ የራያና የአዘቦ ፣ የሐባብና የቦጐስ ፣ የከረንና የሱዳን ተወላጅ ዘንድ ነገሩ የተገላቢጦሽ እየሆነ ሔደ ። በጦርነቱ የተካፈሉት ላልተካፈሉት ያፄ ምኒልክን ጦር አወጋግ እያደነቁና እያጋነኑ አወሩ ። ከአላጌ ጦርነት በፊት በነበሩት የባንዳ ወታደሮችና በቅርብ በተመለመሉት ባገር ተወላጆች ዘንድ ፣ “ጣልያንን ማን ይችለዋል ” የሚል እምነት አድሮ ነበር ። አሁን ግን ፣ በተለይ ጦርነቱን ተካፍለው የሸሹትና ለሌሎቹ ያወሩት ፣ ያለቆቹን የነገበየሁ አባ ጐራን ፣ የነታፈሰ አባ ትንታግን አመራርና የወታደሩን ድፍረትና ጀግንነት በዝርዝር ሲተርኩት ፣ በፊት የነበራቸውን እምነት ከመሠረቱ አናጋው ። በዚህ ምክንያት ፣ በአላጌ አካባቢ ያሉ የእንዳ መሆኔ ፣ የአበርጋሌ ፣ የእንደርታ ፣ የዋጅራት ፣ የሰለዋና የገራልታ ሕዝብ በየወረዳው መመሥረትና ማስተዳደር ፣ ሹም ሽር ማድረግ የጀመሩትን ኢጣልያኖች እየተዉ ፣ ብዙ የትግሬ መኳንንትና ሹማምንት ከነጭፍራቸውና ከነመሣሪያቸው እንዲያውም አንዳንዶቹ ጠላትን እየወጉ ወደ ወገናቸው በመደባለቅ የኢትዮጵያን ጐራ አጸኑት ።

የኢጣልያ ጠቅላይ አዛዥ ነገሩን ሰምቶ ፣ እንደነመቶ አለቃ ጋምቢ የመሳሰሉትን ሹማምንት እየላከ አንዳንዶቹን ቢያስጠብቃቸውም ፣ ሁሉም በየጊዜው እየመጡ ለራስ መኰንን ይገቡ ጀመር ። እነዚህም የትልቁ ራስ አርአያ ልጆች ደጃች ተድላ አባ ጉበን ፣ ልጅ አብርሃ ፣* ደጃች ገብረ ሚካኤል ፣ ሹም ደራ መንገሻ ፣ ደጃች ብሩ ናቸው ።

* ደጃች ደብብ ካሤ ዮሐንስ ተጣልተው ከኢጣልያኖቹ ጋር በነበሩበት ሰዓት ታናሽ ወንድማቸውን አብርሃን ለኢጣልያኖቹ ሰጥተዋቸው ነበርና ጣልያኖቹ ቶሪኖ ወስደው አስተምረው መልሰው አምጥተው መሣሪያ አድርገዋቸው ነበር ።ከዓድዋ በኋላ ደጃዝማች ተብለው ትግሬን (እንደርታን) በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ከዋግሹም አባተ መዋጋታቸው በልጅ ኢያሱም ጊዜ ያገር ግዛት ሚኒስትር መሆናቸው ወደፊት ይገለጣል ።

ራስ መኰንንም ፣ የገቡላቸውን ሁሉ ፈቃደኞች የሆኑትን ለራስ መንገሻ ዮሐንስ አስረከቡዋቸው ። ወደዚህ እየከዱ የሚመጡትን ሹማምንት ለማገድ መጥቶ የነበረውን ቲኔንቲ ጋምቢን ቀደም ብለው የገቡት ደጃች ተድላ አባ ጉበን ማርከው ይዘው ከርሳቸው ጋር እስረኛ ሆኖ አገር ላገር ከዞረ በኋላ፣ በመጨረሻ ደጃዝማቹ ለራስ መኰንን አስረከቡትና በአላጌ ጦርነት ላይ ከተማረኩት ከሌተና ስካላና ከሁለት ዝቅተኛ መኰንኖች (ኮፓራሎች) ጋር ተደባልቆ በራስ መኰንን ሠፈር ብዙ ጊዜ ቆይቷል ።[1]

በኢትዮጵያ በኩል ግን ፣ ምንም እንኳን የወታደሩ ድፍረት ፣ የመሳፍንቱ ኅብረት በጣም ቢያስደስታቸውም ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ልባቸው በኩራትና በትምክህት አልተሞላም ። በተለይ አዲስ አበባ ፈረንጆች ፊት የጦርነቱንም ደረጃ ዝቅ በማድረግ በነፊታውራሪ ገበየሁና በነቀኛዝማች ታፈሰ ወደ መላከክ እያዘነበሉ ፣ ነገሩ እንዳይባባስ ያላቸውን የልስላሴ ፖለቲካ በጽሑፍም በተግባርም ያሳያሉ ። ራስ መኰንንም የተከተሉት ይኸንኑ አርአያ ነው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ኅዳር 28 ቀን በተደረገው ጦርነት ማገርር ቶዜሊ ፣ ካፒቴን ካኖቬቲ ፣ ካፒቴን አንጌራ ፣ ካፒቴን ፔርሴኮና ሌሎቹም ሹማምንት በድምሩ አምስት ካፒቴኖች ፣ ዐሥር የመቶ አለቆችና ሁለት ምክትል የመቶ አለቆች በጦርነቱ ላይ ሞተዋል ። ራስ መኰንን ከጦርነቱ በኋላ የነዚህን ሬሣ ከያለበት አስነሥተው ራሳቸው በሰልፍ ቆመው ፣ እዚያው አላጌ አጠገብ በሚገኘው ቤተ ማርያም በሚባለው ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀበሩዋቸው ።[2]

ከዚህ በፊት እንዳነበብነው ማገርር ቶዜሊ ፣ አምና 1887 ዓ. ም. ደጃች ባሕታ ሐጐስ ፣ ከራስ መንገሻና ካፄ ምኒልክ ጋር ተላልከው ፣ ቴኔንቴ ሳንጉይኔቲን አስረው የሸፈቱ ጊዜ ፣ አሁን በአላጌ ያለቀውን ጦሩን አስከትሎ ፣ በሐላይ ወግቶ ከገደላቸው በኋላ ሬሳቸውን በሜዳ ጥሎ ለመቀጣጫ በማለት አላስቀበረም ነበር ። አሁን ራስ መኰንን እርሱንና ወገኖቹን በክብር ሲያስቀብሩ ፣ የደጃች ባሕታ ሐጐስ ወንድሞች እነአዝማች ሠንጋል በዚያው ነበሩና ፣ "የኛን ወንድም ያላስቀበረው ቶዜሊ ለምን ይቀበራል" ብለው ተከራከሩ ። የዚህን ጉዳይና ሌላም የአላጌን የጦር ወሬ ጨማምረው በስፍራው የነበሩት

1 Italia ed Etiopia . . . PP. 209-214; Memoire d' Afrique - O Baratieri PP. 282-285 .

2 Adua, Bellavita, PP. 236 - 237 . La Prima Guerra d' Africa -R Bataglia - PP 644 - 646



አስተርጓሚው ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሠ ነገሥቱ ከጻፉት ሰፋ አድርገው ለዚያው ለሞንዶን ጽፈውለታል ።

ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን ከዚህ ቀደም ያላጌን ጦርነት የምሥራች ጃንሆይ የላኩብዎት ጊዜ የጦርነቱን ሁኔታ ውጊያቸውን ሳልከብዎት የቀረሁት ፣ ከመንግሥት ቤት የሚወጣው ደብዳቤ የተተካከለ ወሬ መሆን ይገባዋልና ይኸውና ዛሬ ጨርሼ እልክብዎታለሁ ። ከዚህ ቀደም ጃንሆይ ሳይልኩ ራስ መንገሻ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ጋር እርቅ ለማድረግ ጀምረው ነበር በእርቁም ሲመላለሱ የነበሩ አባ እናንያ የሚባሉ ኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ መነኩሴ ፣ ሊቄ ወልደ ኢየሱስና ግራዝማች ሳዶር ናቸው ።[1]

በመጨረሻው ግን ዐፄ ምኒልክ ፣ ለጦርነት ሲመጡ እናንተ ለእርቅ አልመጣችሁም ሰላዮች ናችሁ ብሎ አሰራቸው ። ከዚህ በኋላ ሞት ይገባችኋል ብሎ ሊያስደበድባቸው ሳለ ፣ ሌዑተና አስካላ የሚባል ከሹሞቹ መካከል ተነሥቶ መልክተኛ ወጊድ ይባላል እንጂ ይሞታልን ብሎ ከሞት አተረፋቸው ። ሞት ቢቀርላቸው እስራት አይቀርላቸውም ብሎ አስሮ ምጥዋ ሰደዳቸው ። ይህም ሌዑተና አስካላ ዛሬ አላጌ ላይ የተማረከው የመድፈኞች አለቃ ነው ። ጃንሆይም የየጁን መሬት ጨርሰው በታኅሣሥ በ4 ቀን አላማጣ ከሚባል አቀበት ከግርጌው የዋግሹም ግዛት ክፍል የሚሆን ሰፍረው ሳሉ ያላጌን ጦርነት ድል የማድረግ የምሥራች መጣላቸው ።

ከዚህ በኋላ ፣ የምሥራቹን ወደናንተ ልከው አሸንጌ ላይ ወጥተው ሰፈሩ ። ከዚህም ላይ የፊታውራሪው ጦር ድል ማድረግ ለመጨረሻው ድል የምሥራች ምልክት ነውና ሠራዊቱ ሁሉ ተሰልፎ ግባት ቢተኩስ በዱር በገደል የነበረ ወደ ኢጣልያንም ተጠግቶ የነበረ ሸፍታ ሁሉ መግባት ጀመረ ። ያላጌም ጦርነት ፊትም በደብዳቤ ያገኘነው ከተዋጋውም ከሠራዊቱ አፍ ያገኘነው ይህ ነው ። ጄኔራል ባራቲዬሪ ምጥዋ ሳለ ከሸዋ ጦር መጣብን ብለው ቢልኩበት ፣ ዓድዋም የነበረውን አዲግራትም የነበረውን ጦር አንድ ላይ ጠቅላችሁ ወደፊት ቀድማችሁ ከማገርር ቶዜሊ ጋር ያላጌን በር ያዙ ብሎ ላከ ። ማገርር ቶዜሊም ጦሩን ጠቅሎ ያላጌን በር ይዞ ምሽግ መሸገ ። ጄኔራል ባራቲዬሪም አምባ ነው ። መንገዱም እንኳን ያራት ራሶች ጦር አንድነት ሆኖ ለመሔድና ያንድ ፊታውራሪ ጦር ለማስገንዘ እጅግ ያስጨንቃል ብሎ ነው ይኸን ያደረገው በኅዳር በ27 ቀን የፊታውራሪ ገበየሁ ጦር ከአላጌ ወዲህ ዳቦር (ደቦር) ከሚባል ሜዳ ሰፈረ ። የቀሩትም ራሶች ወደ ኋላ ሰፍረው ነበር ። በ28 ቅዳሜ ጧት በፊታውራሪ ሰፈር ላይ ማገርር ቶዜሊ መድፍ መተኰስ ጀመረ ። የጃንሆይ ሠራዊት ግን ሰንበትን ለማክበር ያንለት ለመዋጋት ፈቃድ አልነበረውም ። ነገር ግን

1 ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ግራዝማች ሳዶር ናኩራ እንደታሠሩ ሞቱ ። ሁለቱ ካህናት መ.ያገ ሆኖ በቆየው በማገርር ቶማስ ሳልሳ ተለውጠው ተለቀዋል ። Italia ed Etiopia ገጽ 205 ፣ የማስታወሻ ቁጥር 3 ። በዚህ ጽሑፍ ላይ ሌተና አስካላ የሚሉት በደብዳቤያቸው እንደ ገለጹት በአምባላጌ ሲዋጋ የተማረከው ደንበኛ ስሙ Scala ነው ።

> ጠላት ከተነሣ ወዲያ ጊዜ መስጠት የሞኝ ሥራ ነው ብለው የኋለኛው ጦር ሳይደርስ ፊት የነበረው የፊታውራሪዎች ጦር እጅግ የሚያስጨንቀውን ዳገት በእግርና በፈረስ ወጥቶ የጦሩን ገዳም (ከምችቱን) አፈረሰው ። መድፉም ተያዘ ማጆር ቶዜሊም ከባልንጀሮቹ ጋር ከዚያው ሞተ ። ከማጆር ቶዜሊ ጋር የሞቱ ጣልያኖች ከ30 ይበልጣሉ ። 3 ፈረንጆች ግን ተማረኩ ። ከተማረኩት ከሦስቱ ኢጣልያኖች አንዱ ሊዩተና አስካላ የሚባል የመድፈኛ አለቃ ነው ። ይህ ጦርነት ሲደረግ የኛ ወታደሮች የሸሸው ጦር እንዳያመልጣቸው በዳገትና በቁልቁለቱ ፊሣውን እየረገጡ እስከ ማታ ድረስ ጋለቡበት ።
>
> ጄኔራል አሪሞንዲ የሚባለው ግን ፣ ከኰሎኔል ጋሊያኖ ጋር ኮረብታ ወዲያ ሰፍረው ሳለ ፣ የጦርነቱን የመድፉን የጠመንጃውን ተኩስ በሰሙ ጊዜ ለመርዳት ሲነሱ የኛ ጦር የሸሸውን ሲያባርር ከሰፈሩበት ደረሰባቸው ። ዕቃውን ትቶ መድፉን ብቻ ጭኖ ሸሸ ። የኛም ሰው ተከትሎ ብዙ ሰው ፈጀበት ። ጨለማ ገላገላቸው ። ኰሎኔል ጋልያኖ መቀሌ ከእርድ ገብቶ አደረ ። የተማረኩት መድፎች አራት ናቸው ። የተማረከው ዕቃ ግን የይሩ ባሩድ የዱቄቱ የብሩ ጠበንጃውም ባሳገር ማረከው እስካሁን ይለቀማል ። ይኸን ያህል ጠበንጃና መድፍ ሲተኮስ አላጌ ላይ የወደቁ የኛ ወታደሮች 276 ሞቱ 349 ቆሰሉ ። ማጆር ቶዜሊን ተከትሎ የሔደ ባሻ ባዙቅና የትግሬ ጦር አንድም አላመለጠም። ደጃች ባሕታ በሞተ ጊዜ ጣልያኖቹ አይቀበር ብለው ከልክለው ነበር። ዛሬም አላጌ ላይ የሞቱትን ጣልያኖች ራስ መኰንን ሳስቀብራቸው ቢሉ የደጃዝማች ባሕታ ወንድሞች አይቀበሩብን ብለው ለራስ መኰንን ቢሙሁ ፣ ይህ የክርስቲያን ሥራ አይደለም እነዚያ ቢከፉ እንደነዚያ እንከፋም ብለው አስቀበሯቸው ። ከዚህ በኋላ የጃንሆይ ሠራዊት የመቀሌን እርድ ከቦ ተቀመጠ ። እርሱ ግን የእርቅ ነገር እየተላላከ ሌት ሌት ካቡን እየካበ እርድን አጠነከረ . . . [1]

እላይ በግራዝማች ዮሴፍ ጽሑፍ እንደ ተገለጸው ፣ ጄኔራል አሪሞን
ለማጆር ቶዜሊ ድጋፍ ለመሆን አንድ ሺ አምስት መቶ ጦር ይዞ
ሌሊቱን ሁሉ ወደ አላጌ ለመድረስ ሲገሠግሥ አድሮ በአራት ሰዓ
ላይ አፍጐል ደረሰ ። ከዚያም በሩቅ የአላጌን ተራራ የጥይት ጭ
አጥቁሮት ተመለከተ ። ከዚያ ተነቃንቆ በዐሥር ሰዓት አዲአራ
ጉብታ ላይ ሰፍሮ ሳለ ፣ ቶዜሊን በሕይወት እንዳለ ቆጥሮ ከዚህ የ
ከተለውን ደብዳቤ ጻፈለት ።

> . . . እዚህ የደረስሁት ባራት (10) ሰዓት ነው ። ከምሽት በፊት ከዚህ ተነስቼ ወደ ማይ መዝጊ ሳልጠጋ አልቀርም ። የጠላት ጦር በርከቶ እንደሆነ ወደኋላህ እንድትመለስ ጠቅላይ ገዥው በጥብቅ ያዘዘውን ልኬብሃለሁ ። ያንተ ጦር ወደኋላ መለስ ቢል ከኛ ጦር ጋር ተገናኝቶ ከዚያው የሁሉም ጦር ተጠቃሎ ከአገረ ገዥው (ባራቲዬሪ) ጋር መቀሌ ላይ ይጠቃለላል ። ጥይትና ዱቄት የያዙት የብሌክን (ያገር ተወላጅ ሹም) ሰዎች በቴኔንቲ ኪያሪኒ መሪነት መጥተዋል ።

አሪሞንዲ ይኸን ለቶዜሊ ጽፎ ሳለ ደብዳቤው አላጌ ሳይደርስ ፣ በዐሥር ሰዓት ተኩል ላይ ፣ ከጦርነቱ ቦታ የሚሸሹትን የኢጣልያኖችና የባንዳ ወታደሮችን የሚያባርሩት የነራስ መኰንን ወታደሮች ደርሰው ተኩስ ከፈቱበት ። ዝርዝር ወሬውንም ፣ ከሞት የተረፉት ሦስት መቶ ባንዳዎች ከሦስት የኢጣልያ መኰንንኖች ጋር ደርሰው ነገሩት ። ከአላጌ የሸሹት ራስ ስብሐት ጄኔራል አሪሞንዲን ባገኙት ጊዜ ፣ "ከስድስት ሳምንት በፊት በጠላት ላይ ተጠንቀቁ፣ ከኛ በቁጥር ይበልጣልና ለምን ሠራዊቱን ባንድነት አትሰበስቡም ብዬ ላገረ ገዥው ለባራቲዬሪ ነግሬው ነበር ። ያለዚያ (ቢሰማኝ ኖሮ) ይኸ ሁሉ እልቂት አይደርስብንም ነበር"[1] ብለው ብስጭትና ቁጣ ጭምር ነገሩት ።

ከዚህ በኋላ ፣ አባራሪዎቹ መተኮሳቸውን ሲቀጥሉ የጄኔራል አሪሞንዲ ፈረስ ተመትቶ ሞተ ። ቢሆንም የኦዶኔ ክፍል ወታደሮች ጠንክር ብለው ስለመከቱ ፣ አደጋ ላይ የተገኘው ጄኔራል አሪሞንዴና ወታደሩ የመሸሻ ጊዜ አግኝቶ ፣ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ከሩብ ላይ ተዟሩ ጋብ ስላለ ፣ ጊዜውንም ምሽት ስለ ተከተለው ፣ በራሪዎቹ የአፍጐልን ሜዳ አቋርጠው ከሌሊቱ በዐሥር ሰዓት መቀሌ ገቡ ።

በአላጌው ጦርነት ፣ በጠቅላላው ከኢጣልያኖቹ ወገን ሁለት ሺ ወታደር ማለቁን ጠቅላይ አዛዡ ባራቲዬሪ በጻፈው መጽሐፍ አረጋግጧል ። ስለዚህ ከዘመተው ጠቅላላ ጦር የተረፈው ሦስት መቶ ሃምሳ ግድም ብቻ ነው ማለት ነው ። በኛ በኩል በግራዝማች ዮሴፍ ደብዳቤ ላይ እንደ ተገለጸው ፣ የሞቱት ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ፣ የቆሰሉት ሦስት መቶ ዐርባ ዘጠኝ ናቸው ።

---

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ዶሲዬ ፣ ቁ.82

1 Italia ed Etiopia . . P. 212

# ምዕራፍ ሐያ ስምንት

## የዳግማዊ ምኒልክና የሠራዊታቸው መቀሌ መግባት—የኢትዮጵያ ድርጅትና የጦር ኃይል

ባለፈው እንደ ተመለከትነው ፥ ዳግማዊ ምኒልክ በየመንገዱ ሰፈር
እያደረጉ ከየአለበት በየአለቃው እየተሰለፈ ለጦርነት የሚመጣውን ተቀ
ብለዋል ። ባንዳንድ ሰፈርም ስለ ደስታ ግባት እያስተኰሱ የሸፈቱ እስ
ገብተዋል ። ብዙ ሠራዊት ብዙ ባለበቅሎና ፈረሰኛ ለማስተላለፍ
የሚያስቸግረውን ውድማ መንገድ ሲያስጠርጉ ፥ አባጣ ጐባጣውን
ሲያስደለድሉ ፥ ጫካውን ሲያስመነጥሩ ፥ በየአደሩበት ድግስ እየተደ
ገሰ ሰንጋ እየታረደ ግብር እየተበላ ተጉዘው ከአዲስ አበባ በተነሡ
በሦስተኛው ወር መጀመሪያ ላይ በታኅሣሥ 5 ቀን ወፍላ ፥ በ8 አሸ
ንጌ ፥ በ11/1888 ደምባልአ ደረሱ ። እዚህም በደረሱ ጊዜ ቀድመው
የአላጌን ጦር የደመሰሱት እነ ራስ መኰንን በሰፈሩበት ሥፍራ በሽታ
ገብቶ ፥ ብዙ ፈረስና በቅሎ ሞቶ መንገድ አላስሔድ ስላለ ፥ ከአሸንጌ
በታኅሣሥ 23 ቀን ተጉዘው የቀድሞውን ጐዳና ፥ ወደ እንጣሎ የሚ
ሔደውን ሰቀው ፥ በቀኝ በኩል አልፈው መሐን ሕዝባ ከደረሱ በኋላ
መንገድና ስንቅ ለማዘጋጀት እዚሁ ላይ ሰፈሩ ።

በመሐን ሕዝባ ላይ ሳሉ ፥ ወደ ኋላ ዘግይተው የነበሩት ንጉሥ
ተክለ ሃይማኖት ጦራቸውን አስከትለው ፥ ከጐጃም ተነሥተው ፥ በቤ
ጌምድር አድርገው ፥ በታኅሣሥ 15 ቀን ደርሰው ከንጉሠ ነገሥቱ
ተገናኙ ። ከዚያ ንጉሠ ነገሥቱ በ19 ከመሐን ሕዝባ አልፈው በ22
እንዳ መሆኔ ፥ ከዚያ በ23 ዋጀራት ገቡ ። ይኸም ስፍራ ባንድ ወገን
የአላጌ ጦርነት ለት ብዙ ጣልያንና ባንዳ ያለቀበት ስለነበረ ፥ የሬ
ሳው ሽታ ከማስቸገሩ በቀር መንገዱ ውድማ የበዛበት ስለሆነ ፥ በሦ
ስትና በአራት መስመር በየጫካው ውስጥ መንገድ እየተከፈተ ሲሠራ
ጕድጓዳው ሲሞላ ሰነበተ ። ከመንገዱ መጥፎነትና ጠምዛዛነት የተ
ነሣ እንዱን የወንዝ ውሃ ሠላሳ ስምንት ጊዜ ማለፋቸውን ጸሐፊ ትእ
ዛዝ ገብረ ሥላሴ የጻፉት ማስታወሻ ያረጋግጣል ።

ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱና ሠራዊቱ ፥ በብዙ ችግር ጠባቡን መንገድ
በታኅሣሥ 24 እና 25 ቀን አልፈው በ26 ቀን ጨለቆት ሰፍረው

ሳሉ ፣ ወደፊት ቀድመው የነበሩት ራስ ሚካኤል ፣ ራስ ወሌ ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ፣ ራስ መኰንን ፣ ራስ አሉላና ደጃች ወልዴ ወደኋላቸው ተመልሰው ፣ ጨለቆት መጥተው ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ነሥተው ተገናኙ ። አላጌ ላይ የተማረከውንም መድፍ አስረክበው ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ለጣልያን እንደሆነ የያዝነው የኛው ይበቃናል" ብለው ከአላጌ የተማረከው መድፍ ወደ አዲስ አበባ ተላከ ።

በዚሁ በጨለቆት በታኅሣሥ 28 ቀን የልደትን በዓል (ገናን) አከብረው ፣ በ29 ከጨለቆት ተጉዘው መቀሌ ሰፈሩ ። በዚህም ቀን ስሜንን የእቴጌ ጣይቱን አገር የሚገዙት የእኅታቸው የወይዘሮ ደስታ ልጅ ደጃች ገሠሠ ስለነበሩ ፣ ከስሜን 500 በግ ብዙ ቅቤ ይዘው ገቡ ።[1]

በዚያን ዘመን ፣ በኛ በኩል የጦርነቱን ታሪክ መዘርዘር ፣ ማናቸውንም የተደረገውን በጽሑፍ ማስቀረት ስለ አልተለመደና ወደ ጊዜያችን የተላለፈ ባለመኖሩ ፣ በዓድዋ የተዋጋውን ትክክለኛውን የወታደሩንና የሹማምንቱን ፣ የጦረኛውንና የነፍጠኛውን ፣ የመድፈኛውን ቁጥር ለይተን አናውቅም ። ኢጣልያኖች በያለበት ሰላዮቻቸውን አሠራጭተው በሰበሰቡትና በዕርቅ እያመካኙ ሹማምንቱ እነማገር ሳልሳና እነቲኔንቲ ፓርቲኒ ከንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር በነበሩበት ጊዜ በግምት የሰጡት የወታደር ቁጥር በብዛትና በማነስ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

| | ሲያንስ | ሲበዛ |
|---|---|---|
| የዳግማዊ ምኒልክ | 34,000 | 38,000 |
| የእቴጌ ጣይቱ | 5000 | 6000 |
| የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት | 5000 | 6000 |
| የራስ ሚካኤል | 14,000 | 15,000 |
| የራስ መኰንን | 15,000 | 16,000 |
| የራስ ቢትወደድ መንገሻ | 5000 | 6000 |
| የራስ ወሌ | 6000 | 7000 |
| የራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ የራስ የአሉላንና የራስ ሐጐስን ጨምረው | 3000 | 4000 |
| የዋግሹም ጓንጉል | 10,000 | 11,000 |
| የፊታውራሪ ገበየሁ | 13,000 | 14,000 |
| ድ ም ር | 110,000 | 123,000[2] |

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ገጽ 239—244 ።
2 La Giornata di Adua - R.Mazzucconi, P. 202.



በጣም አሳንሰው የሚያቀርቡት ደግሞ ፣ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ። ይኸንንም ያቀረበው በሰላይነት የተያዘው መሐንዲሱ ካፑቺ ነው ።

| | | |
|---|---|---|
| ራስ መኰንን | 8000 | |
| ራስ ሚካኤል | 8000 | |
| ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት | 5000 | |
| ራስ መንገሻ ዮሐንስ | 5000 | |
| ራስ ወሌ ብጡል | 5000 | |
| ራስ መንገሻ አቲከም | 3000 | |
| ዋግሹም ጓንጉል | 2000 | |
| ያፄ ምኒልክ ዘበኞች (የልፍኝ) | 3000 | |
| የእቴጌ ጣይቱ ጦር የደጃች ገሠሠ ጭምር | 4000 | |
| የዕቃ ቤት የጠጅና የሥጋ ቤት | 1500 | |
| የንጉሠ ነገሥቱ ዕውቅ የሆነው ጦር ባቶ (በፊታውራሪ) ሀብተ ጊዮርጊስ የሚታዘዘው | 3000 | |
| በበጅሮንድ ባልቻ የሚታዘዘው | 3000 | |
| በሊቀ መኳስ አባተ የሚታዘዘው | 2000 | |
| ራስ ወልደ ጊዮርጊስ | 5000 | አውሳ የዘመቱት |
| ደጃዝማች ተሰማ ናደው | 5000 | |
| ራስ ዳርጌ | 3000 | አዲስ አበባ ለጥበቃ የቀሩት |
| ደጃች ሉል ሰገድ | 3000 | |
| ድ ም ር | 68,500 | |

አዲስ አበባ የቀሩትና አውሳ የዘመቱት 16,000 ሲቀነስ በሰሜን የዘመተው 52,500 ጦር መሆኑ ነው ። በምርኮኛነት አዲስ አበባ ከርሞ በኋላ በእርቅ ወደ አገሩ የተመለሰው ጄኔራል አልቤርቶኒ ሌላ የበዛ ዝርዝር ይሰጥና ሲያንስ 111,000 ሲበዛ 122,000 ያደርገዋል ። ከዓድዋ ድል በኋላ ለዕርቅ ወዳፄ ምኒልክ የተመላለሰው ማገር ሳልሳ ደግሞ 130,000 ተዋጊ ፣ ከ60 እስከ 70 ሺ አሽከርና ገረድ ያደርጋል ። እነዚህ እንደዚህ ከፍ ያለ ቁጥር የሚያቀርቡት እንደዚህ ባይበረክትኖሮ በዋዛ አንሸነፍም ነበር ብለው ለመግደርደር ፣ ያቀረቡት ይመስላል ። እንደ ክሎሺት እንደ ግለይሸን ያሉት ከ150,000 እስከ 200,000 አድርሰውታል ።[1]

1 Italia ed Etiopia - Conti - Rossini, PP. 340-342, Gli Italiani in Africa Orientale A. Del Boca., PP. 651 - 652.

በዚህ ዐይነት ፣ ሁሉም የተለያየ ቁጥር ቢሰጥም ፣ በመካከለኛና በሚመስል ቁጥር 100,000 ግድም ባለጠመንጃ ይኖራል ብሎ ለማስብ ይቻላል ። ንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥነት ዘመን ጀምሮ ፣ ከጠቡ በፊት ከኢጣልያ መንግሥት በግዥ ካገኙት በቀር ፣ በወዳጆቻቸው የውጭ አገር ሰዎች በእንጂኔር ኢልግ ፣ በሽፍነ ፣ በሶለዩ ፣ በላባሉ ፣ በሪምቦ ፣ በባራል ፣ በሳቩሬ ፣ በብሬሞ ፣ በቦሬሊ ፣ በቢኖ አማካይነት በየጊዜው በግዥ የሰበሰቡት ተጠራቅሞ ፣ ባሁኑ ጊዜ በእጃቸው 189,000 ልዩ ልዩ ጠመንጃ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ዐርባ አራት ሺ ጥይቶች ዐርባ ስድስት መድፎች ፣ አራት መትረየሶች እንደ ነበሩዋቸው የሚያረጋግጡ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ያፄ ምኒልክን የጦር ኃይል ከዚህ የሚያስበልጡም የሚያሳንሱም አሉ ።[1]

እነዚህ ሁሉ የተለያዩ መሳፍንትና መኳንንት ፣ በተለይ በየአውራጃው ትክለኛ መሳፍንት ወይም ባለጉልት የሆኑት እነንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ እነራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ እነራስ ሚካኤል ፣ "እንደምን ላፄ ምኒልክ አበሩላቸው" በማለት ያልተደነቀና ያልተገረመ የለም ። በተለይ ጣልያኖቹ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው የካቲት 23 ቀን ዋናውን ጦርነት እስከ ጀመሩ ድረስ ፣ እነዚህ እላይ የተጠቀሱት ባፄ ምኒልክ ላይ ሸፍተው በየአገራቸው ይቀራሉ ወይም ከጦር ሰፈር እንዋጋም ብለው ተመልሰው ወደ አገራቸው ይገባሉ የሚሉና ጐጃሚው ፣ ትግሬው ፣ ወሎዬው ፣ ከሸዌው ጋር አይዋደድምና እነዚህ ሁሉ ተስማምተው በኅብረት ጣልያንን አይወጉም ብለው የሚያምኑ ነበሩ።

ማንቴጋዛ የሚባለው ፣ "ወዳፄ ምኒልክ በዕርቅ ምክንያት አንድ ወኪል እንልክ የነበረው ፣ ጊዜ ለማግኘት ወይም አንድ ራስ ንጉሡን እንዲከዳ ለመገፋፋት ብቻ ነበር"[2] ብሏል ። ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ከዓድዋ በኋላ ባዘጋጀው መጽሐፉ ፣ "ራሶቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ምኒልክ በኛ ላይ ለማሰለፍ ዐወቀበት"[3] ብሏል ። በኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት ስመ ጥሩ የሆነው ኮንቲ ሮሲኒ ደግሞ ፣ "ምኒልክ ታላላቆቹ አለቆች እንዲከተሉት ለማስገደድ ያደረገው ከንውን አስደናቂ ነው" ይልና ከዚያ እልፍ ብሎ ፣ "አበሻን በሙሉ በጐኑ አሰልፎ ለማዋጋት በመሰብሰብ ረገድ ምኒልክ አንድ ተአምራት ፈጽሟል . . . ይኸን የመሰለውን ያውም ከዚህ ያነሰውን ያንድነት ታሪክ ለመፈለግ ከአህመድ ወልደ ኢብራሂም ጋር ወደ ተደረገው ጦርነት መሔድ አለብን[4] . . ." ብሏል ። ወደ ግራኝ ጦርነት ማለቱ ነው ።

1 La Giornata di Adua, R. Mazzucconi, PP. 202 - 203, Chronology of Menelik II-C.P. Rossenfield PP.160 - 162
2 L' Assedio di Maccalle, V. Mantegazza, P. 325.
3 Memoire d' Afrique, O. Barratieri, p. 351.
4 Italia ed Etiopia, Conti - Rossini, Gli Italiani in Africa, Del Boca, P.252.





ደጃዝማች ባልቻ
ከሞሪስ ደኮፒ

በዚህ ዐይነት ፡ ሁሉም የተለያየ ቁጥር ቢሰጥም ፡ በመካከለኛና በሚመስል ቁጥር 100,000 ግድም ባለጠመንጃ ይኖራል ብሎ ለማሰብ ይቻላል ። ንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥነት ዘመን ጀምሮ ፡ ከጠበፊት ከኢጣልያ መንግሥት በግዥ ካገኙት በቀር ፡ በወዳጆቻቸው የውጭ አገር ሰዎች በእንጂኔር ኢልግ ፡ በሽፍነ ፡ በሶለዬ ፡ በላባሉ ፡ በሪምቦ ፡ በባራል ፡ በሳቩሬ ፡ በብሬሞ ፡ በቦሬሊ ፡ በቢኖ አማካይነት በየጊዜው በግዥ የሰበሰቡት ተጠራቅሞ ፡ ባሁኑ ጊዜ በእጃቸው 189,000 ልዩ ልዩ ጠመንጃ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ዐርባ አራት ሺ ጥይቶች ዐርባ ስድስት መድፎች ፡ አራት መትረየሶች እንደ ነበሩዋቸው የሚያረጋግጡ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ያፄ ምኒልክን የጦር ኃይል ከዚህ የሚያስበልጡም የሚያሳንሱም አሉ ።[1]

እነዚህ ሁሉ የተለያዩ መሳፍንትና መኳንንት ፡ በተለይ በየአውራጃው ትክለኛ መሳፍንት ወይም ባለጉልት የሆኑት እንንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፡ እነራስ መንገሻ ዮሐንስ ፡ እነራስ ሚካኤል ፡ "እንደምን ላፄ ምኒልክ አበሩላቸው" በማለት ያልተደነቀና ያልተገረመ የለም ። በተለይ ጣልያኖቹ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው የካቲት 23 ቀን ዋናውን ጦርነት እስከ ጀመሩ ድረስ ፡ እነዚህ እላይ የተጠቀሱት ባፄ ምኒልክ ላይ ሸፍተው በየአገራቸው ይቀራሉ ወይም ከጦር ሰፈር እንዋጋም ብለው ተመልሰው ወደ አገራቸው ይገባሉ የሚሉና ጐጃሜው ፡ ትግሬው ፡ ወሎዬው ፡ ከሸዌው ጋር አይዋደድምና እነዚህ ሁሉ ተስማምተው በኅብረት ጣልያንን አይወጉም ብለው የሚያምኑ ነበሩ።

ማንቴጋዛ የሚባለው ፡ "ወዳፄ ምኒልክ በዕርቅ ምክንያት አንድ ወኪል እንልክ የነበረው ፡ ጊዜ ለማግኘት ወይም አንድ ራስ ንጉሡን እንዲከዳ ለመገፋፋት ብቻ ነበር"[2] ብሏል ። ዋናው አዝማች ገኔራል ባራቲዬሪ ከዓድዋ በኋላ ባዘጋጀው መጽሐፉ ፡ "ራሶቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ምኒልክ በኛ ላይ ለማሰለፍ ሀወቀበት"[3] ብሏል ። በኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት ስመ ጥሩ የሆነው ኮንቲ ሮሲኒ ደግሞ ፡ "ምኒልክ ታላላቆቹ አለቆች እንዲከተሉት ለማስገደድ ያደረገው ክንውን እስደናቂ ነው" ይልና ከዚያ እልፍ ብሎ ፡ "አበሻን በሙሉ በጐኑ አሰልፎ ለማዋጋት በመሰብሰብ ረገድ ምኒልክ አንድ ተአምራት ፈጽሟል . . . ይኸን የመሰለውን ያውም ከዚህ ያነሰውን ያንድነት ታሪክ ለመፈለግ ከአህመድ ወልደ ኢብራሂም ጋር ወደ ተደረገው ጦርነት መሔድ አለብን[4] . . ." ብሏል ። ወደ ግራኝ ጦርነት ማለቱ ነው ።

---


1 La Giornata di Adua, R. Mazzucconi, PP. 202 - 203, Chronology of Menelik II-C.P. Rossenfield PP.160 - 162
2 L' Assedio di Maccalle, V. Mantegazza, P. 325 .
3 Memoire d' Afrique, O. Barratieri , p. 351.
4 Italia ed Etiopia, Conti - Rossini, Gli Italiani in Africa, Del Boca, P.252.





ደጃዝማች ባልቻ

ከሞሪስ ደኮፔ



ራስ አባተ ቧ ያለው
ከአናራቶሪ

# ምዕራፍ ሐያ ዘጠኝ

## የመቀሌ ምሽግና ማገር ጋልያኖ - ከኢጣሊያ አገር የሚላከው ጦርና በምክር ቤት የተደረገ ክርክር

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ የአላጌን ውድቀት ራሱ ማስታወቅ ግዴታው ስለ ነበረ ፣ ይኸንኑ ላለቆቹ ካስታወቀ ወዲህ አሁንም ከአሸንጌ ወደ መቀሌ የሚያመሩትን የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ብዛት እየዘረዘረ ፣ አዲስ የጦር ወታደር እንዲጨመርለት እየደጋገመ ከመጠየቁ በፊት በኮዓቲት ፣ በሰንዓፌና በደብረ ኃይላ ጦርነት ጊዜ የተደነቀውንና የተከበረውን ያህል ፣ አሁን ደግሞ ከየአለቆቹ ወቀሳ አዘል ትእዛዝ ይደርሰው ጀመር ። በቀጥታ የሚጻጻፉቸው አለቆችም አንደኛ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ሞቼኒና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ናቸው ። ከርሱ ወገን ፣ "የንጉሡ ጦር ብዙ ስለሆነ እርዳታ ላኩልኝ" ሲል እነርሱ ደግሞ ዓይነትና መጠን መወሰን አለብህ ይሉታል ። "መልካም የ14 ባታዮ ጦርና 5 (ባትሪ) የመድፈኛ ጦር" ይላክልኝ ብሎ ሲመልስ ፣ "የለም ኢትዮጵያን በሙሉ የመያዝ ዓላማ የለንምና የያዝነውን ቅኝ አገር ለማጥበቅ ይኸን ያህል ጦር ይበዛል ። ስለዚህ የዘጠኝ ባታዮ ጦርና ሦስት የመድፈኛ ክፍል ይበቃሃል" በመባባል ክርክራቸውን በቴሌግራም ይመላለሱ ነበር ።* በፊት በኮዓቲቱ በደብረ ኃይላው ጦርነት ይወዳደሱ የነበሩት አሁን የአላጌ መሸነፍ ከተሰማ ጀምሮ የክሪስፒና የባራቲዬሪ የፖለቲካ ቡድኖች በምክር ቤትም በየጋዜጣውም ወቀሳና ንትርክ በዝቶባቸው ነበር ። ቶስካኔሊ የሚባለው የምክር ቤት አባል በረዥም ንግግሩ ውስጥ ፣ "አበሾች ገና ከመወለዳቸው ጦረኞች ናቸውና ጦርነቱ በፍጹም ይቅርብን" ያለውን ጠቅላይ ሚኒስትሩና ወገኖቹ ሊገነዘቡለት አልቻሉም ።

---

* አንድ ባታዮ ጦር በውስጡ 25 የጦር መኰንን 800 ወታደር ያለው ይሆንና 27 የመትረየስነት ጠባይ ያለው ጠመንጃ 6 ቀላል መትረደየስ 8 ከባድ መትረየስ 6 ሞርቲዮ (አጫጭር መድፍ) ባለ 81 የሆነ 3 መድፍ ታንክ የሚያፈርስ ። አንድ ባትሪ ደግሞ በውስጡ 4 መድፍ ያለው ነው ። ይኸም እንደ አገሩና እንደ ዘመኑ የቁጥሩ መጠን ይለያያል ። የኢጣልያ አንድ ባታዮ ባለ 700 ወታደር ነው ።

1 L' Assedio d' Maccalle, Vico Mante - gazza, PP. 77- 85.

ስለዚህ ራሱ ክሪስፒ ባንደኛው ቴሌግራም ፡ "ጊዜው ላንተም
ለሁላችንም አደገኛ ነው ። የጠየቅኸውን ልከንልሃል ፤ ከጠየቅኸውም
በላይ እንልክልሃለን ። አለማሰብና አለመጠንቀቅ መከራ ያመጣ እንደ
ሆነ በዚህ እኛ ምንም ጥፋት የለብንም" ብሎ ከላከለት በኋላ ቀጥሎ
በዚያው ሰሞን ደግሞ ፡ "መንግሥት በሰውም በመሣሪያም የጠየቅኸ
ውን ልኮልሃል ። አገሪቱ አንድ ሌላ ድል ትጠብቃለች ፤ እኔም ራሴ እጠ
ብቃለሁ ። ይኸም ድል አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ያበሻን ጉዳይ የሚደመ
ድም መሆን አለበት ። በምታደርገው ተጠንቀቅ ፤ የራስህና የኢጣልያ
ኖች ክብር ያለበት ነገር ነው ።"[1]

የዚህም ቀጥተኛ ትርጉሜው ፡ የአውሮፓዊውና የሠለጠነችው የኢ
ጣልያ ጦር ባልሠለጠነችው አፍሪካዊቷ በኢትዮጵያ ጦር መሸነፉ
ያንተም ፡ የኢጣልያም ክብር ተነክቷልና ይኸን የአላጌን መሸነፍ የሚ
ያስረሳ ኢትዮጵያም ሁለተኛ እንዳታንሰራራ የሚያደርግ አንድ ጊዜ
ለዘለቄታ የሚሆን ጦርነት አድርገህ በድል አድራጊነት ስማችንን
አድስህ ለኢጣልያንም ቅኝ አገር አውርሳት ነው ። በዚህም ላይ
ኢትዮጵያን እንደ ማናቸውም የጥቁር አገር ስለሚቆጥራት ፡ በአፍሪካና
በእስያም ከዚህ በፊት እንዳልነው እንግሊዞችና ፈረንሣዮች ፡ ጀርመ
ኖችና ቤልዥኮች አብዛኛውን ጊዜ ቅኝ አገሮቻቸውን ሁሉ በቀላል
ጦርነት ስለያዙ ፡ የኢጣልያ መሪዎችም ኢትዮጵያን የሚመለከቷት በዚሁ
ዓይነት ነው ። በዚህ ስሜት አያሌ መማክርት የአላጌው ውድቀት ክብራ
ቸውን እንደነካ በመቁጠር ይኸንኑ በእጥፍ ለመበቀል የሁሉም ምኞት
ነው ። በዚህም ጐን እላይ እንዳልነው የነክሪስፒ የፖለቲካ ባላጋራዎች
ሥልጣን ለመያዝ ሲሉ የመንግሥቱን አስተዳደርና የጦሩንም አመራር
በምክር ቤትና በጋዜጣ ይነቅፉታል ። የአላጌንም ውድቀት ለአባባላ
ቸው በቂ ምስክር አድርገው በማቅረብ ሥልጣን ለመረከብ ይሟገታሉ ።

የሆነ ሆኖ ፡ ጄኔራል ባራቲዬሪ የጠየቀው የእርዳታ ጦር አላጌ
ንም ለመበቀልና በኢትዮጵያ ለመስፋፋት ከኢጣልያ አገር ተሰብስቦ
በናፖሊ ወደብ ሲሣፈር ሲል ፡ በሹማምንቱና በወታደሩ መንፈስ ታላቅ
ደስታ ነበር ። ከመሳፍንቱ ጀምሮ ሁሉም እኔ ልሒድ እኔን ስደ
ዱኝ እያለ የመከላከያ ሚኒስትሩን በደጅ ጥናት የሚያዋክበው ብዙ
ነበር ። ከሲቪል ሳይቀር ብዙዎቹ አማላጅ እየላኩ የተመለመሉ አሉ ።
የየዘማቹ ቤተሰብና ነዋሪው ሰው ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ የሚጠብቀውን
የመሸነፍ አደጋ ሳይገነዘብ ዘማቾቹን በዘፈን ፡ በደስታ ፡ በትልቅ በዓል

1 LA Prima Guerra D' Africa - Bataglia PP - 282 - 284



ለመሸኘት ሁሉም ለየራሱ ኮሚቴ አበጅቶ ለየወታደሩ ሲጃራ ፡ መጠ
ጥና ልዩ ልዩ ስጦታ እየተሰበሰበ ለዘማቹ ይታደል ነበር ። ወደ ናፖሊ
ወደብ ከመድረሳቸው በፊት ወታደሩን ያሳፈረው ባቡር በሚቆምበት
ጣቢያ ሕዝቡ እየተሰበሰበ በደስታና በሆታ ይሸኛቸው ነበር ። የየባታ
ዮው ጦር በየክፍሉ ሆኖ ወታደሩ ከመርከብ ላይ ሊሣፈር አቅራቢያ
በዘማቹና በቤተሰቡ መካከል የበረከተ ሁካታ ፡ የስንብት መሳሳም
ሲደረግ ፡ ሥነ ሥርዓቱ ሁሉ ተዘበራርቆ ስለ ነበርና ሹማምንቱ ሥር
ዓት ለማስከበር ሲሞክሩ በዚህ ሥፍራ ቆሞ ይኸን ትርዒት በደስታ
ይመለከት የነበረው አድሚራል ኮርሲ ፡ "አንድ ጊዜ ተውዋቸው
የፈለጉትን ያድርጉ" የሚል ቃል ሲወረውር ፡ በዚያ የቆመው ቤተ
ሰቡ ሁሉ ጭብጨባውን በደስታ ገለጠ ።

የዓድዋ ጦርነት ከመደረጉ በፊት ፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 29 ቀን
ወደ ኢትዮጵያ የሚዘምቱት ወታደሮች ከናፖሊ ወደብ በተነሡ
በት ቀን ንጉሡ ራሱ ተገኝቶ ሸኝቷቸዋል ። ከመነሣታቸው በፊት
ባደረገላቸው ዲስኩር ፡ "መኳንንት ምክትል መኳንንትና ወታደሮች
ሆይ! የራሴን የወታደርነትና ያገሪቱን ሰላምታ እኔው ራሴ ላቀርብላ
ችሁ ፈለግሁ ። በወንድሞቻችን ደም የተቀደሰችውና የምትሔዱባት
አገር ለናንተ እንግዳ አይደለችም ። በርሷም ላይ የኛ ድል አድራጊነ
ትና የመሥዋዕትነት ሙያውና ዋጋው ፡ ማስታወሻው ገና በት
ኩሱ እንዳለ ታገኙታላችሁ ። እነዚህንም ምሳሌዎች እናንተም ትርኢ
ከሩባቸዋላችሁ ። ወታደሮች ሆይ ! የኢጣልያንን ምኞት ለወታደር
ጓደኞቻችሁ እንድታደርሱ ባንዲራዋን ለመከላከል የሁሉም ልጀቿ
እሽቅድምድም ነው " የሚል የማበረታቻ ቃል ይገኝበታል ።[1]

በዚህ ዓይነት ፡ የኢጣልያ ወታደር በፊትም የተላኩት አሁንም
ከአላጌ ጦርነት ወዲህ በጥርና በየካቲት ወር ከኢጣልያ አገር የተሣ
ፈሩት ሁሉ በጠቅላላው ኤርትራም ከገቡ በኋላ ፡ ሁሉም መኰ
ንኖችና ወታደሮች ጦርነት የጠማቸውና ድል ማድረግ የናፈቃቸው
በድል አድራጊነታቸውም የተረጋገጡ ነበሩ ። ይሁን እንጂ ፡ የአላ
ጌን ጦርነት የተካፈሉትና በሽሽት ወደ መቀሌ የተመለሱት ብቻ
ከኋላ ያለውንም የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ወሬ በመስማት ስለኢትዮ
ጵያ ጦር ያላቸውን አስተያየት ሳይለውጡ ይኸውም ማለት ሳያሠ
ጋቸው አይቀርም ።

ጄኔራል አሪሞንዲ ፡ ፈረሱ በአባራሪዎቹ ኢትዮጵያውያን ተመትቶ
ከሞተበት በኋላ በሌላ ፈረስ ሆኖ በሽሽት ከነጭፍራው መቀሌ ገብቶ

1 Francesco Crispi, La Prima Guerra d' Africa, P. 407

ዋናው የነራስ መኰንን ጦር መቀሌ ከመድረሱ አስቀድሞ በፊቱ ሦስት ጉዳዮች ተደቅነዋል ።

፩ኛ የመቀሌን ምሽግ አፈራርሶ የራሱን ጦር ጠቅሎ ወደ ዋናው ጦር ሰፈር ወደ አዲግራት መዛወር ፤

፪ኛ ወይም ያንድ ክፍል ጦር እዚሁ ከመቀሌ ምሽግ እንዲከላከል ትቶ እርሱ የቀረውን ጦር ይዞ ወደ አዲግራት መሔድ፤

፫ኛ ሁሉንም ጦር እንደያዘ እዚሁ መቀሌ ቀርቶ ወደፊት የሚጓዘውን የኢትዮጵያን ጦር መመከት ነው ።

ነገር ግን ፤ ዤኔራል አሪሞንዲ ምሽጉ ምንም በደምብ የተመሸገና የሦስት ወር ስንቅ የያዘም ቢሆን ፤ "ለብዙ ሠራዊት ሥፍራውም ስንቁም አይበቃም" በሚል አሳብ ይዋልል ነበር ። ጉዳዩን በውስጡ ካሉት ሻለቆች ከነጋልያኖ ከነአሚልዮ ጋር ሌሊቱን ተመካከረበት ። አንዳንዶቹ ፤ "ምሽጉን አፍርሰን ጠቅለን መሔድ የአገራችንን ክብር ይነካል" ስለአሉ ፤ ጋልያኖ "እኔ የራሴን የባታዮ ጦር ይዤ እዚሁ ለመከላከልና ሕይወቴንም ቢሆን ላገሬ ክብር ለመሠዋት ቆርጫለሁ" ብሎ ተናገረ ። በዚሁ ተወስኖ ለጋልያኖ 21 የጦር መኰንኖች ፤ 176 የነጭ ፤ 1150 ያገር ተወላጅ ወታደሮች ፤ አንድ የመድፈኛ ክፍል ተሰጠውና ቀረ ። አሪሞንዲም የቀረውን ጦር ይዞ ሲነጋ ራስ መኰንን ከመድረሳቸው በፊት በችኮላ አለቃው ወዳለበት ወደ አዲግራት ፍርሃት ባለበት ግሥጋሤ ሔደ ። የዚህን ጉዞ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ፤ "አሪሞንዲ የሦስቱን ቀን ጉዞ ባንድ ሌሊት አቋረጠው" ሲሉ ተችተዋል ።[1]

ጋልያኖ ፤ ጦርነት የጠማውና የኢትዮጵያን ጦር ይንቅ እንደነበረ በግል ከወዳጆቹ ጋር የተጻጻፋቸው ደብዳቤዎች ያመለክታሉ ። የአላጌ ጦርነት ከመደረጉ ከአንድ ወር በፊት በዚሁ በመቀሌ የነርሱው አገር ተወላጅ ናሬቲ በሠራው ባዬ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ተቀምጦ ሳለ ሊቤሪና ለሚባለው ኢጣልያ አገር ላለው ወዳጁ እንደዚህ የሚል ደብዳቤ ጽፎ ነበር ።

በጣም የተወደድሽው ሊቤሪና

የዛሬ ሐያ ዓመት አንድ ናሬቲ የሚባል የኢብሬያ አናጢ ሠርቶት በነበረ ባዬ ዮሐንስ አዳራሽ ዙፋን ላይ ተዝናንቼ በመዘርጋት በመልካም ጤንነት የምገኝ መሆኔን ለመግለጽ እነዚህን ጥቂት መስመሮች እልክልሻለሁ ።

ከሦስት ቀን ጀምሮ የአራተኛው ባታዮ ጦር የጀመረውን ይኸን ምሽግ ለማስጨረስ የኔ ወታደሮች እንዲያግዙ እዚሁ ላይ ቆይቻለሁ ። ሥራውም እልቆ መልካም መከላከያ ሆኗል ። . . . ነገ ከዤኔራል አሪሞንዲ ጋር አዲግራት እንሔዳለን. . . መንገዳ በመሸሹ ምክንያት የተቋረጠው ጦርነት የቆመ አይመስለኝም ።

. . . ምኒልክም አንድ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግን አያውቅበትም ። ዛሬ ጦርነት ይፈልጋል በማግሥቱ አይፈልግም በዚህ መካከል እኛ አየር ላይ ተንጠልጥለን ቀረን . . . በሮማ የኛ ድል አድራጊነት ይጠበቃል. . .1

መቀሌ ከአዲግራት 115 ኪሎ ሜትር ፡ ከዓድዋ 120 ፤ ከአምባ አላጌ 74 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ የእንደርታ ከተማ ነው ። ዐፄ ዮሐንስ መቀሌን ዋና ከተማ አድርገው እስካሁን ያለውን ቤተ መንግሥት አሠርተው አድምቀውት ነበር ። አሁን ጋልያኖ መሽጐ የተቀመጠበት ቦታ ዐፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸውካሠሩት ቤተ መንግሥት ወደ ደቡብ ምሥራቅ አለፍ ብሎ የእንዳ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ካለበት ከፍተኛ ቦታ ላይ ነው ። ከፍታው ከባሕር የመቀሌ 2062 ሜትር ሲሆን ፤ የእንዳ ኢየሱስ 2240 ሜትር ነው ። ከዓመት በፊት ከደብረ ኃይላው ጦርነት በኋላ ዤኔራል ባራቲዬሪ መቀሌ የገባለት ግማሹ ሕዝብ ካህናቱም ጭምር በውድም ፤ በግድም ተሰልፈው የተቀበሉት ጊዜ ፤ የመቀሌ ከተማ ለአላጌና ለአሸንጌ ፤ ለአዲግራትና ለአሥመራ አማካይ በመሆኑ የእንዳ ኢየሱስ ጉብታ ጠላትን ለመከላከል የሚያመች መሆኑን ተመልክቶ ሟቹ ቶዜሊ የምሽጉን ሥራ እንዲጨርስ አዞት ነበር ። ከዚያም ቶዜሊ ወደፊት ወደ አላጌ የዘመተ ጊዜ የምሽጉን ሥራ ይኸው ጋልያኖ ከአሪሞንዲ ጋር እየተስማማ ወደ ፍጻሜ አድርሶታል ። የእንዳ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንም ለምሽጉ ሥራ እንቅፋት ስለሆነ ፤ ታቦቱን አስወጥቶ በቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ላይ ራሱ የኢጣልያ ባንዲራ ተሰቅሎበት በውስጥና በበራፉ መድፍና ጠበንጃ ተጠምዶበታል ።[2]

በራስ መኰንን የሚመራው ጦር በኅዳር 28 ቀን የአላጌን ምሽግ ከደመሰሰ በኋላ ፤ ከዚያም ለእርዳታ የመጣውን የዤኔራል አሪሞንዲን ጦር ወደ መቀሌ እያባረረ የአላጌ ጦርነት በተደረገ በሦስተኛው ቀን ወደ መቀሌ ምሽግ አቅራቢያ ደረሰ ። እንደደረሰም የራስ መኰንን አሳብ ሁልጊዜ በሰላም መንገድ ኢጣልያንን ከአገር አስወጣለሁ የሚል ተስፋ ስለሆነ ፤ በሚጓዙበት ጊዜ እርሳቸው

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 241-242

1 Lettere e Diari, F. Lemmi, PP. 62-63.
2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 245

ለጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ “እንደ የሚታመን ሁነኛ ሰው የኛን አሳብ ለመንግሥታችሁ ሊያቀርብ የሚችል ላከልኝ” ብለው አንድ ደብዳቤ ላኩበት ። እርሱም ለዚህ ጉዳይ የተመረጠውን መኰንን ይዞ የሚሔድ ሰው ይላኩልኝ ብሏቸው ለዚሁ ብላታ እንግዳ ተሰማ የሚባሉትን መርጠው ላኩለት ።[1]

ከዚህ በኋላ ፣ ኡምቤርቶ ፓርቲኒ የሚባለውን መርጦ ፣ ከርሱም ጋር ሙንጣዝ ሐመድ የሚባለውን ላስተርጓሚነት ፣ ሌላ ደግሞ ተራ ወታደር ላጃቢነት ልኮአቸው በታኅሣሥ 18 ቀን 1895 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ራስ መኰንን ሰፈር ደረሱ ። እርሳቸውም መልክተኛውን በደንብ ተቀብለው ስለ አነጋገሩት በጣም ደስ አለው ።

ምንም እንኳ ፣ ራስ መኰንን ዕርቁን አጥብቀው ከልብ የሚፈልጉት ቢሆን ፣ ኢጣልያኖች ደግሞ የዚህን የእርቅ ንግግር ጊዜ የሚጠቀሙበት ምሽግ ለማጠንከሪያ ፣ በዕርቁ ሰበብ በራሶቹና በሠራዊቱ መካከል ወዲያና ወዲህ በማለት ሲያጋጥማቸው የመኳንንቱን ስሜት ለማወቂያ ፣ የመሣሪያውንና የወታደሩን ቁጥር ለመገንዘቢያ ፣ የየአለቃውንና የወታደሩን ሥነ ሥርዓት አጠባበቅና የሞራሉን ደረጃ ለመገመቻ ነው ። ቲኔንቲ ፓርቲኒ ከምርኮኛው ከቲኔንቲ ስካላ ጋር እንዲጫወትና አብሮ እንዲያድር የተፈቀደለትን ጊዜ ለዚህ ለስለላና ስውይይት ነው ያደረገው ። እንደ እውነቱ ራስ መኰንን በዚህ በጦርነት ሰዓት መልክተኛው ከምርኮኛው ጋር ተገናኝቶ እንዲሰነብት መፍቀዳቸው የሚገባ ባይሆንም ፣ የራሳቸው አስተሳሰብ ምን እንደ ነበረ ለመገመት ያዳግታል ።

ራስ መኰንን ለጠቅላይ ገዥው አንድ ደብዳቤ ፣ በሐረር ሳሉ ለሚያውቁትና ስለዕርቁ ጉዳይም አነጋግረውት ለነበረው ለፒዬትሮ ፌልተር ሌላ ደብዳቤ ቲኔንቲ ፓርቲኒን አሲይዘው ላኩት ። እርሱም እነዚህን ደብዳቤዎች ይዞ መቀሌ ምሽግ ደርሶ ከዚያ ወደ አዲግራት ሔዶ ለጄኔራል ባራቲዬሪ አስረከበ ። ባራቲዬሪም በጉዳዩ ሮማ ካሉት ባለሥልጣኖች ጋር በቴሌግራም ሲነጋገርበት ሰንብቶ ወደፊት እንደሞናነበው ፣ ይኸው ፌልተር ካለበት ተፈልጎ ወደ መቀሌ እንዲሔድና ከራስ መኰንን ጋር እንዲነጋገር ተወሰነ ።

ቢሆንም ፣ ፓርቲኒ አዲግራት በነበረበት ጊዜ ባራቲዬሪ ሮማ ካሉት አለቆቹ ጋር በቴሌግራም በሚወያይበት ሰዓት ከነርሱም ግልጽ ትእዛዝ ሳይመጣለት ጉዳዩ በማነህ ማነህ እየተወዛገበ ጊዜው

1 Italia ed Etiopia .. Conti -Rossini, P. 239.



ስለተራዘመ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ወደ መቀሌ የሚደርሱበት ቀን ስለተቃረበ ፣ ራስ መኰንን እንደዚሁ መጠበቅ ጉዳዩና ሁኔታው ስለ አሠጋቸው ፣ ለዚሁ በመቀሌ መሽጎ ለተቀመጠው ለማዦር ጋልያኖ ከዚህ የሚከተለውን ቁርጠኛ ደብዳቤ ጻፉለት ።

> እኔ ባንተ የሚታዘዘውን ትንሽ ምሽግ ስመውጋት አልመጣሁም ። እኛ ብዙ ስለሆንን ያንተን መድፎች ምንም አንፈራም ። አላጌን ልታስታውስ ይገባል ። በከንቱ ደም እናፍስስ ። እኔ እስከ ምጥዋ ድረስ ሸኚ ልስጥህ ። ጓዝህንም ሁሉ እዚያው ድረስ ልልክልህ እችላለሁ ።

እርሱም በበኩሉ ለዚህ መልስ ፣ “ከስፍራዬ አልነቃነቅም ፤ ጓዜንና ምሽጉን መውሰድ የፈለግህ እንደሆነ ናና ውሰድ ። በመድፍ በትር እቀበልሃለሁ” የሚል ቁርጠኛ መልስ ላከባቸው ። የጋልያኖ መልስ በአላጌ ጦርነት ቀዜማ ቶዜሊ ከመለሰው የድፍረት መልስ ጋር ተመሳሳይ ነው ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ያኛው በውጊያ ሲሞት ይኸኛው ባፄ ምኒልክ ፈቃድ ነፍሱን አድኖ ለጊዜው ከወገኖቹ ተደባልቋል ።

ራስ መኰንን ፣ ማይ መዝጊ ሆነው ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ ጽፈውት የነበረው ደብዳቤ ፣ “የአላጌው ጦርነት የተደረገው ያለኔ ፈቃድ ነው ። መጥፎ ነገር ነው የሆነው ። አሁንም የባሰውን ለማስወገድ አንድ ታማኝ ሰው ተደርጎ ጉዳዩን በሰላም እንጨርስ” የሚል ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ በዚሁ ምዕራፍ በመጀመሪያው ገጾች ላይ እንደተመለከትነው ፣ የኢጣልያ መንግሥት የአላጌን ውርደት በሌላ በማያዳግም ድል መመለስ ስለፈለገ ፣ ከዚህም ድል በኋላ ሰፊ ግዛት ማግኘት ዋናና ከሥር የተነሣበት ዓላማ ስለሆነ ካፄ ምኒልክም ፣ ከራስ መኰንንም የሚሰነዘረው የሰላም ፍላጐት የጦር አለቆቹ ካለው የበለጠ ለመዘጋጂያ ፣ ጦር ለማደራጃያ ፣ ምሽጐችን ለማጠንከሪያ ከማድረግ በቀር ሰላሙን በምንም ዓይነት አልፈለጉትም ። ዕርቅና ሰላም ቢፈልጉም የሁለቱ መንግሥታት ሰላም አፈላለግ መንገዱ በፍጹም የተራራቀ ነው ። የኛ መሪዎች ሰላም ፍለጋ የተያዘውን አገር ለማስለቀቅ ሲሆን የኢጣልያኖቹ ደግሞ ፣ “የኛ ባንዲራ መውለብለብ እስከ ጀመረበት እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ያለውን አገር እንደ ያዝን የውጫሌውልም እንዳለ ረግቶ መኖር አለበት” የሚል ነው ። ልዩነቱ በሌላ ታላቅ ጦርነትና ድል አድራጊነት ካልተፈታ ሌላ መፍትሔ የለውም።

እንደዚህ ያለውን ቁርጠኛ ሐሳብ የሆነውን ጉዳይ ከጦርነትና ከኃይል ሥራ በቀር የሚገላግለው መንገድ ስለሌለ ፣ ሁለቱም ወገኖች

1 L Assedio di Meccalle .. ,PP. 301 -341.

ባንደበታቸው ሰላምን እያወሩ ፣ "ደም በከንቱ አይፍሰስ" እየተባባሉ ላዩን ሳይሆን ውስጡን ተዋውቀው ሁለቱም ፣ በእርቅና በሰላም ፍለጋው ጊዜ እየተጠቀሙ የጦር ሠራዊታቸውን ያደራጃሉ ።

በዚሁ ጊዜ ፣ የኢትዮጵያን ሁኔታ በውቃለሁ የሚለው 12 ዓመታት ያህል ባዬ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ልዩ መልክተኛ ሆኖ የተቀመጠውና በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ የተነሣ ከንጉሠ ነገሥቱም ከእቴጌ ጣይቱም ተጣልቶ ወዳገሩ የተመለሰው አንቶኔሊ በሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትርነት ተሾሞ ነበር ። ነገር ግን ፣ ከሚኒስትሩ ከሲኞር ብላን ጋር ስለ አልተስማማ ፣ ወደ አርጀንቲን ተልኮ በቦኔስ አይሬስ የኢጣልያ ሚኒስትር ሆኖ ተቀምጧል ።

ከዚያም ሳለ ፣ ከአምባ አላጌ ጦርነት ወዲህ በደብዳቤም በቴሌግራምም ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ክሪስፒ ልዩ ልዩ ምክር ከመላክ አልተቆጠበም ። እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ 12 ቀን 1895 ዓ. ም. በላከው ቴሌግራም የሰጠው ምክር ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

> በልዩ ጥንቃቄና በረጋ መንፈስ ድሉ እርግጠኛ እንዲሆን ሸዎችን በትግሬ አገር ማዳከም ። አዲግራትን ትቶ አሥመራንና ከሰላን መከላከል ። ራስ ስብሐትን መጠርጠር ። በሐረር ላይ ህማች ወታደር መላክ ጠቃሚ ነው ። ከዮሐንስ ለመገላገል በምኒልክ ለመጠቀም ያደረግነውን አሁንም ከጉጃሙ ንጉሥ ማድረግ ። በድፍረቴ ይቅርታ ። አንቶኔሊ.[1]

ውስጥ ዐወቅ የሆነው አንቶኔሊ ሮማም ፣ አዲስ አበባም የነበረ ጊዜ የምኒልክን ኃይልና ድርጅት በቅርብ ከማወቅ የተነሣ በምጥዋና በአሥመራ ያሉት አገረ ገዥና የጦር አለቆች ተመቸን ብለው ወደፊት እየቀደሙ አገር መውረራቸውን አልተስማማበትም ነበር ። አሁንም በዚህ ቴሌግራሙ ምንም እንኳን የኢጣልያ ወታደር መቀሌንም አዲግራትም ደርሶ መመሽጉን ባይዘነጋውም ፣ የርሱ አስተያየት የኢጣልያ ጦር ከምዕራብ በከሰላ ፣ ከምሥራቅ በአሥመራ በደንብ መሽጐ በተረፈ ግራና ቀኝ እየተነኮሱ በመውጋት ፣ ጠላትንም ከግራና ቀኝ በማስነሣት ፣ የሸዋ ጦር በትግሬ አገር ተዳክሞ ወዳገሩ እንዲመለስና ከዚያ በኋላ ሁኔታው እየተመዛዘነ የመስፋፋቱ ጉዳይ እንዲቀጥል ነው ። ምክሩ በመጠኑ አደገኛ እንደነበረ የታወቀ ነው ። የዚህ ዐይነቱ ዓላማ በመቶ ሺ የሚቆጠር ሠራዊት ላስከተሉት ንጉሠ ነገሥት በትግሬ ለረዥም ጊዜ በሚቆዩበት ሰዓት ፣ በስንቅ ማለቅና በሌላውም ችግር ውስጥ እንዲገቡ አስቦ ነው ።

ነገር ግን ፣ በማናቸውም ረገድ ኢጣልያኖቹ የአላጌን መሸነፍ እንደ ውርደት ስለ ቆጠሩት ፣ ለዚህ በቀል አንድ የድል ብድር

1 La Prime Guerra d' Africa, Crispi, 394



በቶሎ ካልመለስን ብለው ጦርነቱን በትጋት ከማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ ። በቅርብም በሩቅም ያለ መከር ከዚህ ዓላማ ሊመልሳቸው አልቻለም ። የአላጌ ጦርነት ውጤት እንደ ተሰማ በሮማ ምክር ቤቱ ተከፍቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ የሚደረገውን ጦርነት በደንብ ለመምራት ፣ የአላጌውንም ብድር በደንብ ለመመለስ የሚያስችል ሐያ ሚሊዮን ሊሬ በጀት እንዲፈቀድለት ጠየቀ ። የቅኝ አገር ወረራን ከሚቃወሙት መማክርት ዓይነተኛው ኢምብሪያኒ የሚባለው በዚሁ ጉዳይ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር የጋለ ክርክር አደረጉበት ። "ይኸ ሐያ ሚሊዮን ከወዴት ይመጣል... በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ ፣ ሌላ ሐያ ሚሊዮን መጠየቃችሁ አይቀርም . . . ክሪስፒ ሐበሻን የቁማር ግዛት ለማድረግ ሲፈልግ ነገሩን የጨዋታ ነገር አድርጎታል ። ሌላ መሸነፍ እንደሚደርስብን አስታውሱ . . . ." ብሎ በድፍረት ሲናገር ፣ ከቀኝ ክፍል ታላቅ የታቃውሞ ሁካታ ደረሰበት ። እነጋገሩ ጓደኞቹን እነካቫሎቲንና እነዲሩዲኒን ሲያስደስት ፣ የቀኝ ክፍሎችን የበለጠ ያናደዳቸው ፣ "ከአላጌ መሸነፍ በኋላ ካላረፋችሁ ሌላ መሸነፍ ይደርስባችኋል" ሲል በድፍረት የሰነዘረው ቃል ነው ።[1]

ስለዚህ ፣ በዚህ ጊዜ ከሥልጣን ላይ ያሉት የነክሪስፒ ወገኖች በውጭውም ፣ በምክር ቤቱም ውስጥ ስለ በረከቱ የጦርነቱ ጉዳይ ከመቀጠል አላቋረጡም ። የብልሁ የምክር ቤት አባል የኢምብሪያኒ ትንቢትም ወደፊት እንደምናነበው በትክክል ይደርሳል ።

1 Abissinia - Ed. Scarfoglio. PP. 183 - 184.

# ምዕራፍ ሠላሳ

## የንጉሠ ነገሥቱ ጦር አሰፋፈር — በመቀሌ ምሽግ የመጀመሪያው ጦርነት

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በታኅሣሥ 28 ቀን የገናን በዓል በጨለቆት ካሳለፉና በ29 መቀሌ ደርሰው ከነራስ መኰንን ጋር ከተገናኙ በኋላ ፣ ከመቀሌ ከእንዳ ኢየሱስ ምሽግ የተተኮሰ የመድፍ ጥይት ከማይደርስበት ሥፍራ ሰፈሩ ። በመቀሌ ምሽግና እርሳቸው በሰፈሩበት ሥፍራ መካከል 6500 ሜትር ስለሆነ ፣ በዚያን ጊዜ በኢጣልያኖቹ እጅ ያለው የመድፍ ጥይት የሚሔየደው ፫ ኪሎ ሜትር 850 ሜትር ብቻ ስለሆነ ፣ የሰፈሩ ጉዳይ በጥናት እንደ ተደረገ ያስታውቃል ። እንዲያውም በዚህ ጊዜ ከፈረንሳይ አገር ተገዝቶ የመጣውና በኢትዮጵያውያኑ እጅ ያለው የመድፍ ጥይት እስከ 4500 ሜትር ድረስ ሔዶ ስለሚመታ ፣ የመድፉ ዓይነት ከኢጣልያኖቹ የኢትዮጵያውያኑ ይሻላል ማለት ነው ።[1]

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ በመቀሌ እንደ ደረሱ ምሽጉን ባንድ የጦር ክፍል አስከብበው እርሳቸው ግን መቀሌን አልፈው 110 ኪሎ ሜትር ድረስ ተጉዘው ዋናው የኢጣልያ ጦር ተከማችቶ ወደሚገኝበት ወደ አዲግራት ሔደው ለማጥቃት ሊሞክሩ ይችሉ ነበር ። ነገር ግን በአላጌ እንደሆነው ይኸንንም በመቀሌ የመሸገውን ጦር በሙሉ እየጠረግሁ እልፋለሁ በሚል ስሜት ፣ "እነዚህን ጣልያኖች ከጉድጓዳቸው* ሳላስወጣ ወደ ግራም ወደ ቀኝም አልል" ብለው በዚያው ሰፈሩ ።

እንደዚሁም ጀኔራል ባራቲዬሪ የአላጌን መሸነፍ ከውርደት ቆጥሮ አዲስ የድል ብድር እመልሳለሁ እያለ በሚመኝበት ጊዜ ፣ የገዛ ጦሩ መቀሌ ላይ ተከቦ ሲጨነቅ ከአዲግራት ገሥግሶ በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራውን ጦር ለመግጠም ጉልበቱን አልተማመነውም ። በዚህ ምክንያት ጋልያኖ ፎክሮ ፣ "በመቀሌ ቀርቼ ያገሬን ባንዲራ እከላከላለሁ

1 Italia ed Etiopia, Conti - Rossini,P. 248; The Campaign of Adwa and the Rise of Menelik, G.F.H.Berkeley, Chap. Vl, PP. 178 -216

* ከምሽጋቸው ለማለት ነው ።

እንዳለው ዕድሉ ያውጣው” ብሎ ባራቲዬሪ አዚያው አዲግራት ምሽጉን እያጠነካከረ ተቀመጠ ።

ስለዚህ ፣ ዐፄ ምኒልክ ጦራቸው መቀሌ ደርሶ ሰፈሩን ተከፋፍሎ ከያዘ በኋላ ፣ በምሽጉ ዙሪያ ራቅ እያለ ከዚህ እንደሚከተለው ሰፈረ ። ከምሽጉ በምዕራብ በኩል በደብሪ የሸዋ ጦር ፣ በምሥራቅ በኩል የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የራስ መንገሻ ዮሐንስ ጦር ፣ በጋምቤሳ በኩል የራስ መንገሻ አቲከም ፣ የራስ ወሌ ፣ የደጃች ወልዴ ጦር ፣ ወደ ጨለቆት በሚወስደው መንገድ ላይ የንጉሡ ነገሥቱ ፣ የራስ መኰንንና የፊታውራሪ ገበየሁ ጦር ፣ ጦሩ በዚህ ዐይነት ከሰፈረ በኋላ ፣ ስለ ጦርነቱ አጀማመርና አመራር በስፍራው የነበሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሚከተለውን ጽፈዋል ።

ድንኳን በሚተከልበትና ጭነት በሚራገፍበት ጊዜ አንድ በቅሎ ፈርጥጦ ወደ ኢጣልያኖቹ ሰፈር ሮጠ ። አንድ ሰው ሊመልሰው ሲሮጥ ባዩ ጊዜ ኢጣልያኖቹ የመድፍ ተኩስ ዠመሩ ። ኢጣልያኖቹ አብዝተው መተኰሳቸውን ንጉሠ ነገሥቱ በተመለከቱ ጊዜ ፣ ሊቀ መኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን ሒዱ እናንተም ተኩሱባቸው ብለው አዘዙና የምሽቱ ጊዜ በመድፍ ተኩስ አለፈ ። ወደ ማታ ንጉሡ እንደገና ሊቀ መኳስ አባተንና በጅሮንድ ባልቻን ጠርተው ፣ “እነዚህን ኢጣልያኖች ከጉድጓዳቸው ሳላስወጣ ወደግራም ወደቀኝም አልሔድም ፤ እናንተም የጠላት መድፍ ጥይት የማይደርስበትን ሥፍራ መርጣችሁ ከዚያ ሆናችሁ ምሽጉን በመድፍ ምቱት ” ።

ብለው አዘዙዋቸው ።

ካሉ በኋላ ፣ ሊቀ መኳስ አባተ ጦራቸውን ይዘው በምሽጉ በስተግራ የኢጣልያኖቹን ቃፊር ጠባቂ አባርረው ምሽግ አበጅተው ፣ መድፍና መትረየሳቸውን እንደ ጠመዱ ፣ በጅሮንድ ባልቻም በስተቀኝ በኩል እንደዚሁ ሌሊቱን ተገን (ምሽግ) ሠርተው መድፍና መትረየሳቸውን ጠመዱ ። ኢጣልያኖቹም የኢትዮጵያኖቹን መጠጋት ባወቁ ጊዜ የመድፍና የጠመንጃ ተኩስ አበረከቱ ። አነጣጥሮ በመተኰስ የተመሰገኑት ሊቀ መኳስ አባተም ፣ በሩቅ በሚያሳየው መነጽራቸው ታቦቱን አውጥተው የያዙትን የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተመልከተው አስተካክለው ቢተኩሱ ፣ የመድፉ ጥይት በመስኮት ገብቶ ያንዱን መድፍ እግር ሰባበረው ፤ ኢጣልያኖቹም ከተበላሸው መድፋቸው ላይ ጭስ መነሣቱን ባዩ ጊዜ እየተኰሱ የመድፍ ጥይት ሊቀ መኳስ አባተና በጅሮንድ ባልቻ ባሉበት ቦታ ላይ እንደ በረዶ አወረዱባቸው ። ነገር ግን አንድም ሰው አልቆሰለም ። . . .በዚህ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፣ ከድንኳናቸው ወደ ላይ ካለው ከፍተኛ ስፍራ ላይ ሆነው የመድፉን ውጊያ በመነጽር ሲመለከቱ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የቀሩት መኳንንትም እንደ ርሳቸው ያዩ እንደነበረ ጸሐፊው ዘርዝረውታል ።



ከዚሁ አያይዘው ፣ እቴጌ ጣይቱም የድንኳናቸውን መጋረጃ ገልጠው ሲመለከቱ ፣ በእርሳቸው አጠገብ አዛዥ ዘአማኑኤል ቆመው ስለነበረ እቴጌይቱ ወደርሳቸው ፊታቸውን አዙረው ፣ “ሒድና ከሊቀ መኳስ አባተ እየተመካከርህ ምንጩን ለመያዝ ትችል እንደሆን ሞክር” ብለው አዘዙዋቸው ። እሳቸውም ሒደው እንደ ታዘዙት ከሊቀ መኳስ አባተ ጋር ቢነጋገሩ ሊቀ መኳሱ ፣ “የምንጩ ሥፍራ ጥልቅና ወደ ኢጣልያኖቹ ምሽግ የቀረበ ነው ። በምንጩና በምሽጋቸው መካከል አንድ መቶ ሃምሳ ክንድ የሚሆን እርቀት አለ ። ቢሆንም መተላለፊያውን በመድፍ ሳስጠብቅ ቆይቼ ፣ ሌሊት ሲሆን ወታደር ልኬ ምንጩን አስይዛለሁ” ብለው መለሱላቸው ። አዛዥ ዘአማኑኤል ይኸን መልስ ከሊቀ መኳስ አባተ ተቀብለው ለእቴጌይቱ ቢነግሩዋቸው ፣ በጣም ደስ እንደ አላቸውና ነገሩንም ለዐፄ ምኒልክ እንደአመለከቷቸው ፣ ንጉሡም “መልካም ነው” ብለው ስለመለሱ እቴጌ ለወታደሮቻቸው ፣

እስካሁን ድረስ እምሽጉ ውስጥ ገብተን ለመዋጋት ደስታችን ነውትሉ ነበር ። ነገር ግን ወደ ምሽጉ ገብቶ ለመዋጋት እንደዚህ ለበዛችሁት ጦር የምሽጉ መንገድ ጠባብ ስለሆነ ፣ ከኢጣልያኖቹ መድፍና ጥይት የበለጠ እርስ በርሳችሁ ትገዳደላላችሁ ። ስለዚህ ሒዳችሁ ጣልያኖቹ ውሀ እንዳይቀዱ ምንጩን ጠብቁ እናንተም እስካሁን እምሽግ ገብተን እንዋጋለን የምትሉት የሚዳን ጦርነት እንደማትፈሩ ተስፋ አለኝ ። በዚህ ጦርነት ተዋግተው ለተረፉት ደስ የሚያሰኝ የክብር ሽልማት እሰጣቸዋለሁ ፤ ለሞቱትም ተዝካራቸውን አውጣላቸዋለሁ ፤ ልጆቻቸውንም አሳድግላቸዋለሁ ፤ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን ”

ብለው እንዳሰናበቷቸው ዘርዝረዋል ።

እቴጌይቱ በዚህ ንግግር ካሰናበቱዋቸው በኋላ ፣ ወታደሮቹ የጦር መሣሪያቸውን በደንብ አዘጋጅተው እንደ ተቆጣ ነብር መስለው ከቀኑ በ11ኛው ሰዓት ወደ ምንጩ ተንዙ ። እቴጌም ሌሊቱን ሙሉ ፣ “አምላኬ ሆይ አታሳፍረኝ እርዳኝ” እያሉ ሲጸልዩ ሲያዝኑ አደሩ ። 11 ሰዓት ሲሆን አላይ እንደ ተባለው ፣ ገብረ ጊዮርጊስ ድልነሤና ሸዋዬ የሚባሉት አሽከሮች ተነሥተው በነርሱ ውስጥ ለየአንዳንዳቸው የሚታዘዝ ሦስት መቶ ባለጠመንጃ ወታደር ይዘው ወደ ምንጩ ከሔዱ በኋላ የሚተኩሱበትን ምሽግ እንደ አበጁ ጸሐፌ ትእዛዝ በደንብ አብራርተውታል ።

ከዚህም አያይዘው ፣ ኢጣልያኖቹ ምንጩ ወደ ምሽጉ በመቅረቡ ምክንያት አበሾች መጥተው ይይዙታል ብለው እንደ አላሰቡ ፣ ነገር ግን ባወቁ ጊዜ ሐሙስ ከማታው በሦስት ሰዓት መድፋቸውን እየገጐተቱ ወጥተው ባለጠመንጃዎች ጭምር ምንጩን በሚጠብቁት

ላይ በድንገት ደርሰው ውጊያ እንደ ገጠሙዋቸው ፤ ጠባቂዎቹም ጠንከረው ከመዋጋታቸው የተነሣ ጣልያኖቹ ወደ መጡበት መመለስ ግድ እንደ ሆነባቸው ፤ በማግሥቱ ሊቀ መኳስ አባተ ከበጅሮንድ ባልቻ ጋር ተስማምተው ጣልያኖቹ ያሉበትንና መድፋቸውን የጠመዱበትን በመነጽር ተመልክተው በመድፍ መቱት ። ጣልያኖቹ ጓዛቸውን መድፍ ወደማይደርስበት ቦታ እንደ አዛወሩ ፤ ሊቀ መኳስ አባተ በምሽግ ያሉትን በጥብቅ እየጠበቁ ፤ ወዲያና ወዲህ ሲሉ በመድፍና በመትረየስ እየመቱ ጣልያኖቹ ምሽጉን እስኪለቁ ድረስ ሳይተኙና ከመሣሪያቸው ሳይለዩ ሰነበቱ ። በዚህ ሳምንት ሊቀ መኳስ አባተ የሠሩትን ማንም ሊሠራው እንደማይችል ፤ እቴጌ ጣይቱም በየቀኑ ከሌሊቱ ከዘጠኝ እስከ ዐሥር ሰዓት ድረስ ውሃውን ለሚጠብቁ ወታደሮች ብዙ መጠጥ የያዘ ቀንድና በመሶብ እንጀራ ሥጋም እየጨመሩ ይልኩ እንደነበር ፤ የጦር ወታደሮቹም እየበሉ እየጠጡ ሕይወታቸውን ላገራቸውና ለንጉሣቸው ለመሠዋት ሲሉ ፤ አንድ ቀንም መሣሪያቸውን ትተው ሳይተኙ ጠላት ውሃ እንዳይወስድ እየተከላከሉ ቆይተው ፤ በመጨረሻው ምሽጉን እስከ ማስለቀቅ መድረሳቸውን በሚገባ ገልጠውታል ።[1]

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በዚህ ጽሑፋቸው እቴጌ ጣይቱ ፤ ከመኳንንቱ ሊቀ መኳስ (ራስ) አባተ ፤ በጅሮንድ (ደጃዝማች) ባልቻ ፤ ከወጣት ሹማምንት ገብረ ጊዮርጊስ ፤ ድልነሤና ሸዋዬ የሚባሉትን ጕበዛዝት አዘው በእንዴት ያለ እኳኋን የመቀሌን ጦርነት እንደተካፈሉ ያሳዩናል ። ከሁሉ በበለጠ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የመቀሌን ምሽግ ለማስለቀቅ ሊቀመኳስ አባተ ዐሥር ቀን ሙሉ ያለ ዕረፍት ምሽጉን እየተቆጣጠሩ የኢጣሊያ ወታደር ከሰፍራው ሲነቃነቅ በመድፍና በጥይት እየመቱ ጠላትን ዕረፍት እንዳሳጡት አሳይተውናል ። የርሳቸውም አጻጻፍ ይነስ ይብዛ ጣልያኖቹ ከጻፉት ጋር ይገጥማል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ...ምዕ. 62 ፤ ገጽ 242-249 ።



# ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

## በመቀሌ ምሽግ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ጦርነት—ምሽጉን በሰላም ለማስለቀቅ የተደረገ ስምምነት

በመቀሌ ምሽግ በተደረገው ጦርነት ፤ ሊቀ መኳስ አባተና በጅሮንድ ባልቻ ከሌሎች መኳንንት የበለጠ እንደ ተካፈሉ ባለፈው ተመልክተናል ። በምሽግ ውስጥ ያለው ጦር ያለውሃ መኖር እንደማይችል በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ ፤ "ለሚሞተው ተዝካሩን እወጣለሁ ፤ ልጁን አሳድጋለሁ ፤ ዠግንነት ሠርቶ ለተረፈው ሽልማት እሸልመዋለሁ" ብለው አበረታትተው ፤ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው ሦስት መቶ ነፍጠኛ የሚታዘዙላቸውን ድልነሤን ፤ ሸዋዬን ፤ ገብረ ጊዮርጊስን እንደ ምንም ብለው ፤ ምንጩን እንዲይዙ እንደ ላኩዋቸው ፤ እነዚህ ሦስት ወጣት የልፍኝ የበታች ሹማምንት መሆናቸው በታሪካዊው መጽሐፍ ተመልክቷል ።

በመቀሌ ምሽግ አቅራቢያ የሚገኙት ምንጮች ሦስት ናቸው ። አንዱ ከምሽጉ በስተምሥራቅ በጣም ራቅ ያለ ነው ። ሁለተኛው በስተሰሜን በኩል ያለው ነው ። ሦስተኛው በስተደቡብ በኩል ያለው ሲሆን ፤ ለምሽጉ የሚቀርበውና ሁለቱም ወገኖች ባለቤት ሆነው ይዘው ጦርነቱን ለመቀጠል የፈለጉት በደቡብ በኩል ያለውን ነው ። እንደ ኢጣልያኖቹ አጻጻፍ ፤ ይህ ውሃ ርቀቱ ከምሽጉ 400 ሜትር ያህል ነው ። ሊቀ መኳስ በግምት 150 ክንድ ያሉት ይኸንኑ መሆን አለበት ። እነሸዋዬ ሌሊቱን አድፍጠው ምሽጉን ከያዙ በኋላ ፤ በዚያ ሌሊት እጅ በእጅ አፈር በመቆለልና ካብ በመካብ ምሽጋቸውን በጣም አጠንክረውት ስለነበረ ፤ ሲነጋ ኢጣልያኖቹ ከምሽጋቸው ቢተኰሱ እነዚህ ለተተኰሱ የተኵስ መልስ በመስጠት ሊበገሩ አልቻሉም ።

እ. ኤ. አ. ጥር 9 ቀን ለዐሥር እጥቢያ ጣልያኖች ሌሊቱን በሰባት ተኩል ፤ በስምንት ተኩል ፤ በዐሥር ሰዓት ተሩብና በዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ እየወጡ በመዋጋት ምንጩን ለማስለቀቅ ሞክረው በኛዎቹ ጥብቅ ተከላካይነት ሳይሳካላቸው ስለቀረ ፤ ሁሉም ወደ የምሽጋቸው በመሸሽ ተመልሰው ገቡ ። ከዚህ በኋላ በኢጣልያኖቹ ዘንድ ምክር ተይዞ ፤ "እንግዲህ እዚሁ በፊተኛው ቀን በምሽጉ

ውስጥ የያዝነውን ለነጩም ፣ ለጥቁሩም ወታደር ለሴቱም ለሕፃናቱም
ለከብቱም በድርጎ ወሃ እየቆጠብን እየሰጠን እንጠጣ ። ይኸንንም
እየተቆጣጠረ የሚያስፈጽም አንድ ሹም ይደረግ ። የያዝነው ወሃ
አልቆ ካልቸገረን በቀር ትርፉ ሰው ማስጨረስ ስለሆነ ፣ ሁለተኛ ወጥ
ቶን ምንጭ ለማስለቀቅ አንዋጋም" ሲሉ በምክር ወስነው የኢትዮ
ጵያ ጦር ወደ ምሽጉ እየተቃረበ እንዳያጠቃ ወይም አዘንግቶ ባንደ
ኛው ግንባር እንዳይገባ በምሽጋቸው ዙሪያ ቁጥቋራቸውን በጣም
አጠበቁ ። ቀድሞውንም ቢሆን ዙሪያውን ካብና አሸዋ የሞላባት ከረ
ጢት ተደርጎ በዚያም ላይ መድፈኛው መድፉን ፣ ነፍጠኛው ጠመን
ጃውን አልቦ በተራ እየተቀያየረ ሁሉም ወደ ኢትዮጵያውያን ሠፈር
ዐይኑን አፍጦ ይጠባበቅ ነበር ።

ቪኮ ማንቴጋዛ የተባለው ጸሐፊ ፣ ባለፈው እንዳልነው እ.ኤ.አ
ጥር 9 ቀን ለ 10 አጥቢያ በደቡብ በኩል ኢጣልያኖቹ ወጥተው
ለመዋጋት ሞክረው የነበረው ሳይሳካ መቅረቱን ፣ በሰባት ተኩል ፣
በስምንት ተኩል ፣ ባሥር ተሩብ ፣ በዐሥራ አንድ ተኩል ጣልያኖቹ
ወጥተው የተዋጉ ጊዜ ባንደኛው ጦርነት ሁለት ጊዜ መድፍ ተተ
ኮሰ ። ያንደኛው መድፍ ጥይት በኢጣልያኖቹ መድፍ አፍ ገብቶ እን
ደሰባበረው ይገልጻል[1] ። ይህ መድፍ በማይጠረጠር ከሊቀ መኳስ
አባተ የተተኮሰ መሆን አለበት ። በዚሁ ምክንያትም ፣

"አባተ አባ ይትረፍ ነገረኛ አዋቫኪ ሰው
ይኸን መድፍ ከዚያ መድፍ አቆራረጠው"

ተብሎ እንደ ተገጠመላቸው በገሃድ ተነግሯል ።

በዚሁ ጊዜ ፊልተር የሚባለው ፣ ከኢጣልያ አገር የተነሣው
የኢጣልያ ጦር ውስጡን አዲግራት እስኪደርስ ድረስ ጊዜ ለማግኘት ፣
ላዩን ሁለቱን መንግሥታት ለማስታረቅ በራስ መኰንን ጥሪ መጥቶ
ነበርና ፣ ይኸው ፊልተር በንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር በነበረበት ሰዓት
ባንደኛው ግንባር የኢጣልያ ወታደሮች ከምሽጉ ውስጥ እየተኮሱ ብዙ
ሰው አጠቁ ። ዐፄ ምኒልክ ራስ መኰንንን ተቆጥተው በሐረር ጦርና
ምሽጉ ውስጥ ባሉት ኢጣልያኖቹ መካከል እ. ኤ. አ. ጥር 11 ቀን
1896 ስለ ተደረገው ጦርነት ፣ ከዚህ በፊት በዕርቅ ሰበብ መጥቶ
የነበረው በሰጠው ራፖር እንደሚለው ፣ ሲነጋጋ በሰሜንና በምሥ
ራቅ በኩል ባለው መወጣጫ ላይ ትልቅ ጦርነት ተዠመረ ። ጦርነ
ቱም በመትረየስ ጭምር ስለነበር በተከላካዮቹ ላይ ጉዳት አደረሱ።

1 In uno di essi la batteria nemica situata ad Inda Jesus sparo due colpi une dei quali imbocco una cannonier e cannonier danni in batteria, P. 258.



በጣም ተጭነው ጉዳት እንደሚያደርሱ ሲታወቅ ጣልያኖቹ ወደፊት
ቀደም ብለው ተጠምደው የነበሩትን መድፎች እየፈታቱ በትከሻ
እየተሸከሙ ወደ ውስጥ አገቡዋቸው ። ጦርነቱ እስከ 11 (5) ድረስ
ከቆየ በኋላ ፣ እንንደገና በ12 እና በ13 (6—7) ሰዓት ተፋፍሞ
ከሁለቱም ወገን ጉዳት ደርሶ ሳለ ኢትዮጵያውያኑ ወደኋላ አፈገፈጉ።
ጣልያኖቹም ሊያባርሩዋቸው አልቻሉም ።

በበኩሉ ማንቴጋዛ የሚባለው ፣ ሸዎቹና ትግሬዎቹ ብዙ ሰው ቢያ
ልቅባቸው በዚህ ቀን ምሽጉን ለመውረር ቁርጠኛ ሆነው ብዙ አደጋ
በጣልያኖቹ ላይ ባደረሱ ጊዜ ፣ ምናልባት ሐበሾቹ ወደ ውስጥ ለመግ
ባት ቢከናወንላቸው ምሽጉን በቦምብ ለማፈራረስ ዋናው አዛዥ
አስቦ ነበር ። ነገር ግን ፣ ኢጣልያኖቹ አስተካክለው በሮምታ ተኩ
ሰው ብዙ ጠላት ፈጅተው የተጠመደውንም መድፋቸውን ባፈራረሱ
ጊዜ ባንዶቹ ጠመንጃቸውን ወደ ላይ ሰቅለው በመጨፈር ደስታ
ቸውን እንደ ገለጹ ፣ ከዚያም ጨለማው ገላግሎ ሐበሾቹም ስለሸሹ
ጨለማውን ተገን አድርገው ያገር ተወላጅ ወታደሮች ከምሽጉ ወጥ
ተው ሐበሾቹ ወደ ምሽጉ አጠገብ ቀርበው ከተዋጉበት ቦታ ጠመን
ጃና ጥይት ፣ ጋሻም ሌላም ዕቃ አግኝተው ወደ ውስጥ ማግባታቸውን
ይገልጻል ። ይኸው ጸሐፊ ከዚህ አያይዞ ይኸን ትንሽ ጦር ይዞ ጋል
ያኖ አበሾቹን ከምሽግ ወጥቶ እያሳደደ ለመውጋት ባለመቻሉ መጸጸ
ቱን ፣ አበሾቹም በኃይል ወደ ምሽጉ ገብተው ለማሸነፍ ባለመቻላ
ቸው እየተናደዱ ከእንግዲህ ወዲህ በምሽጉ ያለውን ጦር በረኃብና
በጥም ብቻ እናሸንፈዋለን የሚል አሳብ እንደ ወሰኑ ያረጋግጥና በዚህ
ቀን ጦርነት ሁለት የካፖራልነት (10 አለቆች) ማዕረግ ያላቸውና
አምስት ያገር ተወላጆች ሲሞቱ ፣ አንድ ጣልያንና ሐያ አራት ባንዶች
መቁሰላቸውን ያመለክታል ።[1]

በዚህ የጦርነት ጊዜ ሁሉ ፣ አስታርቃለሁ ብሎ የመጣው ፊልተር
በንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር ነበርና ልሰ ጦርነቱ ከኛ በኩል ያለው የጽ
ሑፍ ሰነድ ደካማ ስለሆነ ፊልተር የሚለውን ማንበቡ ይጠቅማል ።
ይህ ፒዮትሮ ፊልተር የተባለው የኢጣልያ ተወላጅ ብዙ ዘመን በሐ
ረርጌ ቢዮኒፊልድ ለሚባለው ለቡና ንግድ ማኅበር ወኪል ሆኖ በተ
ቀመጠበት ጊዜ ከራስ መኰንን ጋር ተዋውቆ ነበር ። የኢጣልያ መን
ግሥትም ፒዮትሮ ፊልተርን ከቺዛሬ ኒራሲኒ ጋርም ፣ ብቻውንም ሆኖ
ከራስ መኰንን ጋር ወዳጅነቱን እንዲያጠና ፣ እርሳቸውም ከዐፄ ምኒ
ልክ ሸፍተው የሚለዩበትን መንገድ ሁሉ እንዲፈልግ ታዞ የነበረው
መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

1 L' Assedio di Macalle - V. Mantegazza, PP. 275 - 380; The Campaign of Adwa and The Rise of Menelik - Berkeley' Chap. VI-VII.

በኢጣልያ ላይ የመርነት ዐዋጅ ከታወጀ በኋላ፣ ይኸው ሰውዬ በ1888 ዓ.ም. በመስከረም ወር ከሌሎች የኢጣልያ ተወላጆች ጋር ሐረርን እንዲለቅ ታዞ ባሁኑ ሰዓት በዘይላ ይገኝ ነበር። ስለዚህ ፊላተር በቴሌግራም ከዘይላ ተጠርቶ ወደ አዲግራት ሔዶና ከጄኔራል ባራቲዬሪ ጋር ተገናኘ። ከዚያም ተልኮ ከሁለት የእንግሊዝ ሹማምንት ጋር ወደ መቀሌ መጣ። የኢጣልያ ጦር ከኢጣልያ እስኪደርስ በሐሰት ስለ ዕርቅ እንደምን እንደ ተነጋገረና የመጣበትን ጉዳይ እንደምን እፍጻሜ እንዳደረሰ ራሱ ፊላተር ከዐድዋ ድል በኋላ ተጠይቆ ለመንግሥቱ በጽሑፍ ካስረከበው ሪፖርት ውስጥ ከዚህ እንደሚከተለው ዋና ዋናውን የአማርኛውን ትርጉም እንመልከት።

መስከረም 23 ቀን ከሌሎች ጋር ሐረርን ለቅቄ ወደ ባሕር ጠረፍ ሔድሁ። በዚሁም ጊዜ ራስ መኰንን በንጉሠ ነገሥቱ ጥሪ ከሐረር ወደ ሸዋ ሔዱ። አስተዳደሩ የኛ ወረራ በትግሬ የሚቀምበትንና ወደ የሚተርፉበትን ጠይቀውኝ ነበር። እኔም ምንም እንኳን ውል ለመዋዋል ከመንግሥቱ ባልታዘዝም የውሉን አለመቅረት* እንደገና ለአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ቢገለጹ እንደዚሁም የኢጣልያ ጦር እስካሁን የያዘውን አገር እንደያዘ እንዲያደርጉለት ንጉሠ ነገሥቱ ቢፈቅዱ ይሆናል ብዬ በመልእክት ተነጋገርን ጉዳዩ ፍሬ ሳያገኝ እንደዚሁ ቀረ... ከዚያ በ6 ታኅሣሥ (ኢ.ኤ.አ.) ከዘይላ ተነሥቼ በ12 አዲግራት በደረሁ ጊዜ የአምባ አላጌ ግጭት ተፈጽሟልና ምንም ለማድረግ አልተቻለም። የሆነ ሆኖ፣ ከያለበት ሠራዊታችን እስኪሰበሰብ የምንጠብቀውም ጦር ከናግ እስኪደርስ 20 ቀን ያህል ወሳኝ ጊዜውን በከንቱ የሚያጠፋበትን መንገድ ፈልጌ እንዳገኝ አገረ ገዥው ቢጠይቁኝ እፈትናለሁ ብዬ መልስ ሰጠሁት።

ይኸን ካለኝ በኋላ ደግሞ፣ ባራቲዬሪ እንደገና የምጠብቀው ጦር የሚደርሰው በጥር 3 ነውና በ20ኛው ቀን ላይ 15 ቀን ጊዜ እንዲጨመር አድርገው ብሉ አገረ ገዥው ለመነኝ። በዚህ ዓይነት ከአዲግራት ሔጄ አጉላዕ በደረስኩ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ሰፈር ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መድረሳቸውን ሰማሁ። በኛ ዘንድ ግን፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ስለሸፈቱ ዐፄ ምኒልክ ሊወጓቸው ሔዱ ተብሎ ታምኖ ነበር። ይኸንኑ ወሬ ለጠቅላይ አገረ ገዥው አስረዳሁ። በጥር 6 ቀን ራስ መኰንን ሰፈር ደረስሁና በደህና ተቀበሉኝ። ወዲያውም ሐረርጌ የተነጋገርነውን የዕርቅ ነገር እንደምነው ቢሉኝ፣ የአምባ አላጌ ነገር በኛ ወገን ሁኔታውን አባብሶታል። ቢሆንም እንደዚያው የተነጋገርነውን መሠረት በማድረግ ውሉን መዋዋል ሳይቻል አይቀርም አልሁዋቸው። ወዲያው ይኸንኑ ለመንገር ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሔደው ምክር ተያዘና የትግሬ ግዛት ከአልተለቀቀ ውጊያው መቀጠል አለበት የሚል ውሳኔ ተደረገ። ቢሆንም ራስ መኰንን በራስ ሚካኤል እየተረዱ የመቀሌው

* የውሉን አለመቅረት የሚለው የውጫሌን ውል 17ኛውን አንቀጽ ጭምር ማለቱ ነው።



ምሽግ እንዳይወጋ ወደፊትም የኢትዮጵያ ጦር ከመገሥገሥ የሚዘገይበትን ሁኔታ ተነጋግረው ጨረሱ። ከዚህ በኋላ ወደ ዋናው ምክር ቤት ቀርበህ ተነጋገር ቢሉኝ፣ እኔ መቼም በደንብ አሳብ ለአሳብ እየተለዋወጥሁ ለመዋዋል የመኰንንነት ሥልጣን የለኝም። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ የሚፈልጉትን ለይተው በደብዳቤ ጽፈው ቢሰጡኝ ለበላይ ላደርስ እችላለሁ ብዬ መለስሁ። ራስ መኰንንም እስቲ የሚሻለኝን አደርጋለሁ ብለው እሠፈራቸው ትተውኝ ሔዱ። ከአምባ አላጌ ጦርነት የተማረከው ቴኔንቲ ስካላ ከኔ ጋር ሆኖ እንዲጫወት ፈቅደውለት ነበር።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ በምሽጉ ባሉት ጣልያኖች ያሉት ወታደሮች ተጠግተው እንዳይዋጉ የሚከለክሉ እንደ ፖሊስ ያሉ የራስ መኰንን ዘበኞች ነበሩ። ዳሩ ግን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከደረሱ ጀምሮ ባንዳንድ ክፍል ያሉ ወታደሮች መተኮሳቸው አልቀረም ነበር። በጥር 7 ቀን የባሰ ነገር ሆነ። ከንጉሠ ነገሥቱ አንድ የጦር ክፍል ትእዛዝ ሳይቀበል የመቀሌን ምሽግ ዝም ብሎ ወጋው። ነገር ግን እምሽግ ያሉ ኢጣልያኖች በቀላሉ ወግተው መለሷቸው። ከጠላት (ኢትዮጵያ) ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ይኸን ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ክፉኛ ተቆጡ። እቴጌ ጣይቱና ወገኖቻቸው ተናደው ራስ መኰንንን በገሃድ ከሰሱዋቸው። ወዲያው ምክር ተያዘ በምክሩም ውስጥ ራስ መኰንን ተገለሉ። ከዚህ በኋላ አቡነ ማቴዎስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባሉበት ንጉሠ ነገሥቱ ራስ መኰንንን ጠርተው፣ “ከኢጣልያኖች ጋር ተስማምተሃል ኰሎኔል ጋሊያኖ ምሽጉን እስኪሠራ ጊዜ ሰጠኸው። እኔ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያልኩትን (ፊላተርን) በሰፈርህ አስቀምጠኸዋል” ብለው እንደከዳተኛ ወቀሷቸው። ራስ መኰንንም “እምነቴን ለመግለጽ ምን ማድረግ ይገባኛል” ቢሉ፣ “በል አንተው ጊዜ ሰጥተህ የመቀሌን ምሽግ እንዳስመሸግኸው አንተው ራስህ ተዋግተህ አስወጣ” አሏቸው... በኔም ዘንድ ትእዛዙ ከማን እንደመጣ አይታወቅም በዙሪያዬ ዘበኛው ተጠራ ቴኔንቲ ስካላም አስተርጓሚዎቼንም ሁሉ ከኔ አራቁዋቸው...

ከዚህ በኋላ፣ ከጧቱ በ11 ሰዓት የመቀሌን ምሽግ መውጋት ተጀመረ። ወደ ተራራው የተጠጉትን ሹሞችና ወታደሮች በምሽጉ ውስጥ ያሉት የኛ ወታደሮች ፈጁዋቸው። ራስ መኰንንም ራሳቸው ራስ አሉላ በጕናቸው ሆነው እየገላገሉ ባይጠብቋቸው ኖሮ ሊዋጉ ሊሞቱ ነበር። ከዚህ በኋላ ምኒልክ ራስ መኰንንን አስጠርተው የቀድሞውን እምነታቸውን መለሱላቸው። ወዲያውም እንግዲህ ውጊያውን ትተህ ዕረፍት አድርግ። ሬሳውንም አስቀብር አሏቸውና የ12 እና የ13 ጥር ቀን በቀብርና በለቅሶ በሐዘን አለፈ።

ወደ ማታ ራስ መኰንን ጠርተው ሬሳችንን ለማንሣት እንድንችል ተኩሱ እንዲቆም ከኰሎኔል ጋሊያኖ ተነጋገር አሉኝ። እሱም ብነግረው ከጥር 10 እስከ 11 ቀን ድረስ በብዙ ውጊያና በብዙ መሥዋዕትነት የያዙትን ምንጭ ይልቀቁና ውጊያዩን ሳቁም ስላለ ምንም ማድረግ አልተቻለም። በጥር 14 ቀን ለኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ለዝግጅት ያስፈልግ የነበረው የ15 ቀን ጊዜ መሙላቱን ሳውቅ እንግ

ዱህ አሰናብቱኝና ወደ አዲግራት ልሒድ ብዬ ራስ መኰንንን ጠየ
ቅሁ ። እርሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱን ቢጠይቁ ከኔ ጋር ይነጋገር ብለው
ራስ መኰንንና ራስ ሚካኤል ባሉበት ጠርተው አነጋገሩኝ ። የምሽጉን
ጽናትና ብርታት አይቼ እኔም በአሳቤ ጸናሁ ።

ከዚህ በኋላ ፣ የንጉሡን ቃል በደብዳቤ ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ
ይዤ እንድሔድ ተደረገ ። በደብዳቤው ላይ የተገለጸው ፣ "የተከበበው
የመቀሌ ጦር በደህንነቱ ወደ አዲግራት እንዲሔድ መፍቀዳቸውና
ከኢጣልያም ጋር የሰላም ውል ለማድረግ በማዦር ሳልሳ አማካይነት
እንዲከፈት" የሚል ነው ። ከዚህ በኋላ በጥር 17 ቀን እዳጋ ሐሙስ
ደርሼ አራት ጊዜ በመካከሉ እየተመላለስሁ የገመትሁት መሣሪያ
የያዘው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ቁጥር 80000 መሆኑን ፣ የመቀሌም
ጦር ውሃ ማጣቱን ጨምሬ የንጉሠ ነገሥቱን መልእክት ለጄኔራል
ባራቲዬሪ ነገርሁ ። ከዚያ የኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የንጉሠ ነገ
ሥቱን አሳብ መቀበሉን የሚያስረዳ አንድ ደብዳቤ ላዼ ምኒልክ ፣ ምሽ
ጉን ለያዘው ለኰሎኔል ጋልያኖ አንድ ደብዳቤ ሰጥቶኝ ሁለት ጊዜ
ወደ ጠላት ሰፈር ተመላለስሁ ። ላዼ ምኒልክም የተጻፈውን ደብዳቤ
ስጠሁ ። ንጉሡም ደስ አላቸው ። ጥር 20 ቀን ወደ መቀሌ ምሽግ ገባሁ ።
ውሃ በፍጹም አልቆ ነበር ። መሣሪያም አንሷቸው ነበር ። ምንጩን
ሁለት ሺህ የሚሆኑ አበሾች ከበው ይጠብቁ ነበር ። ከምሽጉም
የተተኰሰ ጥይት እንዳይመታቸው ከለላቸውን አበጅተዋል ።. . .
ወዲያው ምክር ተደርጎ ምሽጉን ለመልቀቅ ቁርጥ አሳብ ተደረገ ።
ከሁሉም ይበልጥ የሚያስቸኩለው የውሃው ነገር ነበር ። እንስሶቹ
ከጥር 11 ቀን ጀምረው አልጠጡም ። ላንድ ሰው የተሰጠውና በጁ
ያለው ውሃ ለ6 ቀን ሩብ ሊትር ነበር ። ስለዚህ ወደ ንጉሠ ነገሥቱም
ሩጬ 1500 ሊትር ውሃ በባታዮው ልክ እንዲሰጥና ከብቶቹም እንደ
ልባቸው እንዲጠጡ አስፈቀድሁ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከዐፄ ምኒልክ ወታደሩም መሣሪያውም ሴቱም ካህ
ናቱም ከብቱም ሳይነካ መቀሌን ለቀው ወደ አዲግራት ይሒዱ
የሚል የፈቃድ ወረቀት ተቀበልሁ ። የኰሎኔል ጋሊያኖ ጦር ሲወጣ
አደጋ እንዳያገኘው ዋስ የሆኑት ራስ መኰንን ነበሩ ። ስለዚህ የመ
ውጣቱ ነገር በጥር 21 ተወስነና . . . ከምሽጉ መውጣት ተጀመረ ።
ወታደሩም መውጣት የጀመረው በራስ መኰንን ወታደር ተከቦ እየ
ተጠበቀ ነው ። ከምሽግ በሚወጣው ወታደር ላይ አደጋ እታድርጉ
የሚል የጠበቀ ትእዛዝ ተደርጎ ነበር ። ቢሆንም ትንሽ ግጭት ተደርጎ
የቆሰሉ ጥቂት ሰዎች አሉ ። ከዚህ በኋላ ለጦር መሣሪያና ለዕቃ
መጫኛ አስፈቅደን በቅሎና ግመል ከገበያ ገዝተን በጥር በ23ኛው
ቀን ወደማታ ጉዞ ተጀመረ . . . በ30 ከእዳጋ ሐሙስ ጦሩ ተጉዞ
አዲግራት ገባ ።

በፊልተር እጅ ጄኔራል ባራቲዬሪ ለጋልያኖ የላከው መልእክት
እንደዚህ የሚል ነው ። "ስለ ሕይወታችሁ የተሰጠው ዋስትና መተማ
መኛው የተረጋገጠ መሆኑን ስትረዳው ምሽጉን ለቀህ ውጣ ። ያለ
ዚያ ግን ፣ መንግሥት ባንተ ላይ ያለውን የብርታትና የልምምድ



ዕውቀት ስለሚያምነው፣ በመሰለህ መንገድ ጉዳዩን እንድትፈጽም ላንተው
ትቼልሃለሁ ።" ይኸንንም የመውጫ ቃል ያስተላለፈለት በኢጣልያ
ንጉሥ በኡምቤርቶ ስም ነው ። ምክንያቱም መኰንኑ ሞገደኛ ብጤ
ስለሆነ ፣ ባንድ ወገንም የመቀሌ ምሽግ ጉዳይ ወሬው እስከ ንጉሡ
የደረሰ ስለሆነ ፣ ይኸንኑ ተገንዝቦ ያለ ክርክር እንዲወጣ ይመስላል ።

በዚሁ ሰሞን ፣ "ጋልያኖ አንድ ጭብጥ ወታደር ይዞ የመቀሌን
ምሽግ በዠግንነት እየተዋጋ ብዙውን የኢትዮጵያ ጦር መለሰ"
የሚል ወሬ በኢጣልያ አገር ተጋኖ ተወርቶ ስለነበረ ፣ በዚህ ምክንያ
ትም የጦር ሚኒስትሩ ሞቼኒ ይኸንኑ በራፖር ለንጉሡ ለኡምቤርቶ
አመልክቶ በዚሁ በጀብዱ ሰበብ የሌተና ኮሎኔልነት ማዕረግ ታዞ
ለት በቴሌግራም ለባራቲዬሪ ተላልፎለት ነበር ።

ፊልተር ፣ እላይ የተጠቀሰውን መልእክት ወደ ምሽጉ ሔዶ የሰ
ጠው ጊዜ የመሾሙንም ወሬ ሲሰማ ጋልያኖ ፣ "ለዚህ የሚያበቃ
ሥራ መቼ እንደልቤ ሠራሁና" ብሎ አለቀሰ ። ይኸን ማለቱ ከም
ሽግ ውስጥ ሆኜ እንደልቤ አልተዋጋሁም ማለቱ ነው ። ከምሽግ ብቅ
ቢል የሚደርስበትን ስለሚያውቅ ፣ ፍርሃቱን በግልጽ መናገር አልፈለ
ገም ።

የሆነ ሆኖ ፣ ጋልያኖ ሲወጣ በርሱም በጦሩም ላይ ምንም ጉዳት
እንዳይደርስበት ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠው ተስፋ በትክክል ለመፈ
ጸም ዋሱ ራስ መኰንን ስለሆኑ ፣ ይኸንኑ እንዲያምን ፊልተር ራስ
መኰንንን ይዟቸው ወደ ምሽጉ ገባ ። ሁለቱም ከገቡ በኋላ ማዦር ጋል
ያኖ ፣ "ሲወጣ ከነወታደሮቼ ይዘው ቢያስሩኝስ ቢገድሉኝስ" የሚል
ጥርጣሬ አድሮበት ነበርና ይኸንኑ ጥርጣሬውን ደጋግሞ ለራስ መኰ
ንን ስለገለጸ ፣ ራስ መኰንንም ምንም ደጋግመው በመሐላ ቢያረጋግ
ጡለት ማመን እቃተው ። ወዲያው ራስ መኰንን እዚያው አጠገባ
ቸው እተደገነው መድፍ አፍ ፊት ሔደው ተደቅነው ፣ "በሉ እንግ
ዲህ ተኩሳችሁ እኔን ግደሉ ። እኔ እንደዚህ ሳምናችሁ እናንተ በመ
ሐላ የምነግራችሁን እንዴት አታምኑኝም" ብለው ስለ ተናገሩ ፣ ወዲ
ያው በፊልተር አጽናኝነት ጋልያኖ ልብ ገዛና ለጭፍሮቹ እንውጣ
የሚል ትእዛዝ በሰጠ ጊዜ ፣ ሁሉም ጓዙን እየጫነም እየተሸከመም
መውጣት ጀመረ ።[1]

ማዦር ጋልያኖ ፣ "እኔ እዚሁ ቀርቼ እከላከላለሁ" ብሎ ከጄኔ
ራል አሪሞንዲ ከተለያየበት ከታኅሣሥ 8 ቀን 1895 ዓ.ም. ጀምሮ

---

1 L' Assedio di Macalle . . ., PP. 277 - 408; The Campaign of Adwa. Chap. VII.

እስከ ጥር 21 ቀን 1896 ዓ. ም. እ. ኤ. አ. ድረስ አንድ ወር ከ13 ቀን ያህል መከቶ ከቆየ በኋላ፣ በዚህ ቀን ከምት እፋፍ የደረሰበትን ምሽግ ለቆ ወጣ። ባንዲራችንን አውርደን ወደ አዲግራት መሸሽ ለኛ ውርደት ነውና እዚሁ እሞታለሁ ብሎ የነበረውን አሳብ ባሁኑ ሰዓት ለውጦ ባንዲራውን ከተሰቀለበት አውርዶ ጠቅሎ መውጣት ግዴታ ሆነበት ። ሲወጣም የነጩና የጥቁሩ ወታደር፣ የወታደር ሚስቶችና ከመቀሌ ከተማ እያስገደደ ያስገባቸው ሁሉ ነበሩ ። ግማሹ የቆሰለው በቃሬዛ ሆኖ ወይም እያነከሰ፣ በበሽታና በውሃ ጥም የተጐዳው እያቃሰተ በማዝገም ላይ ነበር ። በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ላይ እንደምንረዳው፣ አንዳንዶቹ ያገኙትን ወሃ አብዝተው ከመጓጓት ጋር ስለጠጡ፣ ወዲያው የሞቱም የታመሙም አሉባቸው ።

ጋልያኖ ከነጭፍራው ከነጓዙ እንደወጣ እንዲሰፍር የታዘዘለት ስፍራ ከራስ መኰንን ድንኳን ሐያ እርምጃ ርቆ ነበርና ራስ መኰንን ባስተርጓሚው ባቶ ወልደ አማኑኤል አማካይነት ለጋልያኖና ለጭፍራው ሁሉ የሚያስፈልገውን ሁሉ አደረጉለት ። በተለይ በመቀሌው ምሽግ በተደረገው ጦርነት ዘመድና ጓደኛው የሞተበት ሁሉ ንዴቱ አልበረደም ነበርና ጋልያኖ ከነጭፍራው አደጋ እንዳይደርስበት የሰፈረበትን ቦታ ራስ መኰንን ታማኝ በሆነ ጭፍራ አስከብበው ያስጠብቁት ነበር ።

በዚህ ጦርነት፣ ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱት ስማቸው የታወቀው ፊታውራሪ ግሎህ ፣ ቀኛዝማች በሻህ አባ ሰርጃው ፣ ቀኛዝማች ታመነ፣ አቶ አባይነህ እና ሌሎች ዐሥራ አንድ ሹማምንትና ከራስ መኰንን ብቻ 500 ወታደሮች መሞታቸው በኢጣልያኖቹ በኩል ተመዝግቧል ። በኛ በኩል እስከ 150 ድረስ ብቻ እንደሞቱ ተጠቅሷል ። በዚሁ ጦርነት ራስ መኰንን ወደፊት ቀድመው ለመዋጋት ሲሉ፣ ራስ አሉላ በእጠገባቸው ሁነው እየከለከሉ ሲጋብዟቸው ነበርና የራስ አሉላ ጋሻ ጃግሬ ተመትቶ በዚሁ ወቅት መሞቱን ኮንቲ ሮሲኒ ይጠቅሳል[1] ።

በዚህ በመቀሌ ጦርነት፣ ከኢጣልያ ወገን የሞቱትና የቆሰሉት ስማቸውና ማዕረጋቸው በደንብ ተመዝግቦ ስለሚገኝ እንደኛው አያጠራጥርም ። የእነሱም ቁጥር ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተመለከተው ነው ።

1 Itallia ed Etlopia . . ,P. 251



| | |
|---|---|
| የነጭ ወታደሮች የሞቱ | 4 |
| የነጭ የበታች መኰንንኖች የሞቱ | 5 |
| የጥቁር ወታደሮች በውጊያ የሞቱ | 17 |
| በውጊያ ቆስለው በኋላ የሞቱ | 6 |
| የነጭ ወታደሮች የቆሰሉ | 6 |
| የበታች ሹማምንቶች የቆሰሉ | 3 |
| በውጊያ የቆሰሉ ጥቁሮች | 62[1] |

ከምሽግ በሚወጡበት ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፊልተርን ለማነጋገር መላክተኛ ሲልኩበት ከመላክተኛው ጋር ካለመግባባት የተነሣ፣ ጋልያናን ይዘህ ና ያሉት መስሎት ፊልተር ጋልያናን ይዞት ወዳፄ ምኒልክ ሔደ ። በሔደም ጊዜ ጋልያናን ሰው ሁሉ ይመለከተው ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት አዳራሽ በር ሁለቱም በተጠሩ ጊዜ የልፍኝ አስከልካዩ ወጣ ብሎ የተጠራኸው አንተ ብቻ ነህ እንጂ፣ እሱ አል ተጠራምና አይገባም ብሎ ጋልያናን ከለከለው ። በዚህ ጊዜ ከምሽግ ድረስ እኔ ይዤው መጥቼ ትቼው መግባት አይሆንልኝም ብሎ ስላመለከተና እንዲገቡ ስለ ተፈቀደ፣ ሁለቱም ወዳፄ ምኒልክ የድንኳን አዳራሽ ገቡ ። በገቡም ጊዜ ፊልተርን ለሰላምታ ሲጨብጡ ንጉሠ ነገሥቱ ጋልያናን አልጨበጡትም ። የተዘጋጀውም ወንበር ለፊልተር ብቻ ነበርና ፊልተር ራሱ በመቀመጥ ፋንታ ለማስከበር ሲል ጋልያናን አስቀመጠውና እርሱ ስለቆመ፣ ለርሱም ሌላ ወንበር መጥቶለት ተቀመጠ ።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ፣ "ይኸን ሰው ለምን ይዘኸው መጣህ" የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡለት፣ ስሕተቱ የመልክተኛው መሆኑን ገልጾ፣ "ይኸን የመሰለ የርስዎ ወታደር ለንጉሡ ለመሞት የቆረጠ ዠግና እኔ ንጉሥ ዘንድ ቢቀርብ በጣም ያከብረዋል" ብሎ መለሰ ። ፊልተር ራሱ እንደ ጻፈው፣

> በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ላንድ የልፍኝ አሽከራቸው በዣርው አንድ ትዕዛዝ ሲሰጡት መላክተኛው እንደ ቀስት ተወርውሮ ወጣ ። ሩብ ሰዓት ያህል ከእኔ ጋር ብቻ እንደ ተነጋገርን መላክተኛው አንድ በሐበሻ የርሱዋን ዓይነት ያላየሁዋት በብር የመረሸት ሥራ የተንቆጠቆጠች በቅሎ ይዞ መጣ ። በዚያን ጊዜ ምኒልክ፣ "ያውልህ ፊልተር የኛ አገር ሌላ ነገር እንደናንተ አገር አያፈራምና ይኸን (ለጋልያኖ) ስጠው እንደሚያስደስተው ተስፋ አለኝ" ብለው የኔን እጅ ብቻ ጨብጠው አሰናበቱን . . . ።[2]

ሲል ያረጋግጣል ።

1 L'Assedlo di Macalle . . PP. 390 - 429.
2 La Vicenda Africana - Pietro Felter, PP. 47 - 52.

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

## የመቀሌው ጦርነት በኛ በኩል ባለው ሰነድ—የማገር ጋልያና ጦር ከመቀሌ ወደ አዲግራት መሔድ

ባለፈው ያነበብነው፣ ይነስ ይብዛ ከኢጣልያኖቹ ጽሑፍ የተገኘ ነው። በኛ በኩል ዝርዝር ጽሑፍ ስለሌለን እስከዛሬ ድረስ የአላጌን፣ የመቀሌንና የዓድዋን ጦርነት የምናውቀው በመጠኑ ነው። እርሱም ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ነጋድራስ አፈወርቅ ባጫጭሩ በተዉልን መጽሐፍ አማካይነት ነው። ከነርሱ ወዲህ ብላቴን ጌታ ኅሩይና ከዚያ ወዲህ በመጠኑ ሁላችንም ጽፈናል። የታሪክ መጽሐፍ ነገር ሁል ጊዜ ባገራችን በዝርዝር ማስፈር ስላልተለመደ፣ እንኳን ሩቅ ያለው የዓድዋ የቅርቡ የማይጨውም ጦርነት ጣልያኖቹ ለሕዝባቸው በብዛት ባገለጡት ዓይነት በዝርዝር ለሕዝባችን አልጻፍንም። ጦርነቱ ካገር ነጻነት አልፎ የብዙ ሕዝብ ሕይወት የተሠዋበት እንደመሆኑ መጠን ዝርዝሩን በሕይወት ላሉና ወደፊት ለሚወለዱት ኢትዮጵያውያን ማቆየት የሚገባ መሆኑ የታወቀ ነው።

በዚህ በዓድዋ ጊዜ፣ በኢጣልያኖቹ በኩል በየጦሩ ግንባር ሆነው የተደረገውን ሁሉ እየጻፉ በየላኩዋቸው የጋዜጣ ቡድን ወኪሎች ወደ ኢጣልያ አገር የሚያስተላልፍ ቢዞኒ የሚባል የሴኮሎ ወኪል፣ ሜርካቲሊ የሚባል የትሪቡና ወኪልና ሌሎችም ነበሩ። በኢጣልያ አገር የቀኝና የግራ ክፍሎች የፖለቲካ ቡድኖች ስላሉ፣ ጋዜጠኞች የሆነውን ሁሉ እየሰበሰቡ ለየክፍላቸው ስለሚልኩ፣ አንባቢው ሕዝብ እንደየጣዕሙ ጉዳዩን መከታተል ይችላል። አንዳንድ ጊዜም በጦር መሪዎቹ ላይ ስሕተት ሲገኝ እየነቀፉ ወይም መሪዎቹ ከመንግሥታቸውና ከሕዝባቸው ለመሰወር የሚፈልጉትን እነሱ እያጋለጡ ስለሚገልጹት፣ ያልሆነ ነገር ጽፋችኋል እየተባሉ አላግባብ እየተወነጀሉ በዋናው አዛዥ በጄኔራል ባራቲዬሪ ትእዛዝ ከኤርትራ ይባረራሉ።

የኛዎቹ በዚህ ለዓት እዚህ ደረጃ ስለ አልደረሱ፣ ያዲስ አበባና የሌላውም የኢትዮጵያ ወረዳ ሕዝብ የጦርነቱን ወሬ የሚያዳምጠው ወሬው ካረጀ በኋላ ከመንገደኛ ነው። ይሁን እንጂ፣ ከዚህ በፊት በአ

ላኔ ጦርነት ላይ እንደ ተመለከትነው ፣ አዲስ አበባ የሚቀመጡ ብዙ የውጭ አገር ሰዎች የኢትዮጵያና ያኔ ምኒልክ ወዳጆች ነበሩ ። ከእነ ሱም አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ወዳጆች ሆነው ወደ አውሮፓ መሪ ዎች ዘንድ በመላክ የጦር መግሪያ በማቅረብ ለዘመኑ የሚበጀውን የፖለቲካና ያስተዳደር ጉዳይ በመምከር አገልግሎታቸውን የሚያበረ ክቱ አሉ ። ከነርሱም መካከል ሞንዶን ቪዳዬ የሚባለው ለታ ለሚባ ለው ጋዜጣ ወኪል የሆነ ብቻ ሳይሆን ፣ ብዙ ጠቃሚ አሳብና የአውሮ ፓንም ወሬ ለንጉሠ ነገሥቱ በማቅረብ የሚያገለግላቸው ከዚህ ከኢ ትዮጵያ የተደረገውን ሁኔታ ለዚሁ የጋዜጣ ድርጅት ወደ ፓሪስ በማ ስተላለፍ ፣ የጣልያን ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዝሩትን መጥፎ ወሬ ያስተባብል ነበር ።

ለርሱም በጦሩ ግንባር ሆነው የተደረገውን በጽሑፍ የሚያስተ ላልፉለት ዋናዎቹ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ዋናው አስተርጓሚ ግራዝማች ዮሴፍ ናቸው ። አንድ አንድ ጊዜም ንጉሠ ነገሥቱ ራሳ ቸው በቀጥታ በስማቸው ይጽፉለታል ። በፊት ስለ አምባአላጌ እንዳየነው አሁን ደግሞ ግራዝማች ዮሴፍ ስለ መቀሌው ጦርነት ለዚሁ ጋዜጣ ወኪል በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ የጻፉትን ስናነብ ፣ ፊልተር በእርቅ አስመስሎ ጊዜ ለማግኘያ ወደ ሰፈር የመጣው ለማታለል መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተገነዘቡት ይገልጻል ። ጽሑፉ ከአምባ አላጌው ታሪክ የቀጠለ መሆኑን እያስታወስን ፣ የዮሴፍን አባባል በቀጥታ እን መልከት ።

. . . ከዚህ በኋላ የጃንሆይ ሠራዊት የመቀሌን እርድ (ምሽግ) ከቦ ተቀመጠ ። እርሱ ግን ቀን የእርቅ ነገር እየተላላከ እያታለለ ሌት ሌት ካቡን እየካበ እርዱን አጠነከረ ። ጃንሆይ ግን ከአሸንጌ ተጉዘው አላጌ ላይ በጦር የሞተው ሰውና የከብት ጥንብ ሽታው በመንገድ አላሳልፍም ቢላቸው ፣ የዋዥራትን መንገድ አስጠርገው ተጉዘው ጨለቆት ገቡና ሰፈሩ ። ከጃንሆይ ጋር የነበረው ሠራዊት እርዱን ከቦ ለማፍረስ ሲፈልግ የጃንሆይ ብልህነት ከሠራዊታቸው አለወገን በከንቱ አንድ ሰው እንኳን ቢሞትባቸው እንዳይወዱ ያውቁታል ። ከእር ድም ውስጥ የሚያስነብት ውሀ እንደሌለው ቢያውቁ በዙሪያው የነበረ ውን ምንጭ ሁሉ በዘበኛ አስጠበቁት ። እርሱ ግን ፣ የኛን ሰዎች በእርቅ ስም ያታለለ ጊዜ ሌትም ቀንም እየቆፈረ በጉድጓድም በበርሜልም ጥቂት ውሃ አጠራቅሞ ነበር ። እንደሱ ብልሃት ስንቅ የሌላቸው ዘር ፊው የሚያድሩ ናቸው ። ጥቂት ቀን ጠብቀውኝ ፓለውኝ ይሔዳሉ መስሎት ነበር ። ውሃም የሰረቀ መስሎት ፊርቶ ይለቅልኛል ሲል ከነ ግሀ እስከ ማታ ድረስ መድፍና ነፍጥ ይተኩስ ጀመር ። የኛ ወታደ ሮች ግን በልባቸው ብዙ ንዴት ነበረና ጠንክረው ጠበቁ ። በመስከ ትም እያቸለኩ ብዙ ሰው ብዙ ከብት ፈጁበት ። ውሃ ሲጠብቁ የራስ መኰንን ዘበኞች ቢሞቱ ራሳቸውን አላስነካ ብለው በራስ መኰንን ሰው መድፍ እየተኮሰ አላስቀርብ አላቸው ። ከፍርሃታቸው ብዛት



የተነገ በእርዱ ፊት ለፊት አንድም ሰው ሲያልፍ አንድ ግርም አሜጁ ሲታይ መድፍ ሲተኩስ ይውል ነበር ። እርሱ ግን የእርዱን ካብ ሲከብ በመቀሌ ዙሪያ የነበሩትን ባላገሮች ካህናቱንም ወንዶቹ ንም ሴቶቹንም ልጆቹንም ሰብስቦ አግብቷቸው ነበርና በኢጣልያኖ ቹም ዘንድ ርኀራኄ ስለሌለ ፣ ውሃ ጥም ቢጸናባቸው አንዳንድ ሴቶች ሌሊት በካቡ እየተንከባለሉ ይወርዱ ጀመር ። ውሃም ብናጠጣቸው ወሬውን ሳይነግሩን ውሃውን ጠጥተው ይሞቱ ጀመር ። ከነዚያም ቀጥሉ ሠራተኛው ወታደሩ ውሃ ጥም ቢበረታበት እየከዳ መውጣት ጀመረ ። ከእርዱም ውስጥ ያለው ከብትና ባላገር ሁሉም በውሃ ጥም አለቀ ። እርዱም ቀባሪ ቢጠፋበት በሩቅ ይገማ ጀመር ። አንድ ቀን ውሉ ቢሆን ሁሉም አልቆ ያድር ነበር ። ጃንሆይም እንደ ተጨነቀ ቢያዩት ፣ ልባቸው ራርቶ በእርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን ሕዝብ እኔ የክርስቲያን ንጉሥ እንደ አሕዛብ ንጉሥ ክርስቲያኑን በውሃ ጥም አልፈጀውም ብለው ፊልተር የሚባለውን የሐረርጌውን የኢጣልያ ነጋዴ አስታርቃለሁ ብሎ መጥቶ ከራስ መኰንን ሰፈር ቆይቶ ነበርና አስጠርተው "ከሆነ ራችሁ መምጣታችሁ የሰው አገር እንይዛለን ማለታችሁ ከጉድባ ውስጥ ገብቶ በውሃ ጥም ለማለቅ ነውን" ብለው ጠየቁት ። እርሱ ግን የታየ ነገር ስለሆነ ምላሽ አጣ ። ጃንሆይም እንደናንተ ክፉት ብሔድ ፍጥረት ሁሉ ያልቅ ነበር ። አሁንም ለጄኔራል ባራቲዬሪ እንዲህ ብለህ ንገረው ። "የሰው አገር እይዛለሁ ብሎ የመጣ ሰው ከጉድባ ውስጥ እየ ገባ በውሃ ጥም አያልቅም ነበር ። ጠላታችሁን ውደዱ (አፍቅሩ ጸላዕተክሙ) ያለውን የወንጌል ቃል ለመፈጸም እኔ ግን ፣ የክርስቲያን ንጉሥ ነኝ እንጂ የአሕዛብ ንጉሥ አይደለሁም ። አሁንም ክርስቲያኖች በከንቱ አይለቁ ሰዎችህን ልከህ አስወስድ ፣ ትጥቁንም እንደ ሆነ አን ድነት ተሰብስበባችሁ ቀዩኝ እኔም እመጣለሁ" ብለው ፊልተርን ላኩበት ። ሰዎቼን ይልቀቁልኝ የእንዳ ኢየሱስን እርድ ያስረክቡም የሚል ቃል ከንጉሥ ኡምቤርቶ ይዞ በተላከ በአራተኛው ቀን ተመ ልሶ መጣ ። ከሞት የተረፉት ከጉድባ የነበሩ ኢጣልያኖች ያለቃቸው ደብዳቤ ቢመጣላቸውም እርዳታም እንዳጡ ቢያዩት ጭንቅም ቢበ ዛባቸው ነጭ ሰንደቅ ዓላማ ተከሉ ። ውሃም ለራሳቸውና ለከብታቸው ለመኑ ። ጃንሆይም ከእርዱ ውስጥ ያለውን ደሃ አስወጡ ብለው አዝዘው አስወጡት ። ለነዚያም ለከብቶቻቸውም ውሃ ዳረጓቸው ። ደሃ ውም ከብቱም ወሀ እየጠጣ ይሞት ጀመር ። እንኳን ሰው ውሻውም ውሃ እየጠጣ ሞተ ። የኛም ሠራዊት ይኸን እያየ በድፃው ሞት አዘነ ። ነገር ግን የኛ ሠራዊት ጃንሆይ በሠሩት በጎነት አገራችንን ለዘረፈ ታቦታችንን ላቃጠለ እንዲህ ያለ ወረታ ለምን ይደረግለታል ብሉ ተከፉ ። አይዋጋላቸው ካቡን ጨረሰ በኋላ ሰላምን ከእርዱ ውስጥ ውሃ እንደሌለ ምስጢር እንዳያወጡባቸው* ነው አሉን ። ይሀም ለቀባሪው አረዱት የሚሉት ተረት አይደለምን ? ያገራችንን መሬት አጣ ነው እንዚያ ደብቀው ሊያድኑ ብለን ሳትንባቸው ። ጃንሆይ ግን

* እዚህ ላይ የተዘለለ ዓረፍተ ነገር አለ ። የተዘለለው ዓረፍተ ነገር "ላይዋጋላቸው ሕዝቡን ለምን ከምሽግ አጉዘቶ ዘጋበት ቢሉ ውሃ ያለመኖሩን ምሥጢር እንዳያወጡ ብት ነው አሉን" ይመስላል ።

እነዚያንም ዕቃቸውንም የሚጭኑበት ቢያጡና እጅግ ቢቸገሩ የገንዘብ መውደድ ይመስልብኛል ብለው የኪራይ በቅሎ ሰጥተው ከነዕቃቸው ሒዱ ብለው ሰደዱአቸው ። እነዚያ ጣልያኖች ግን ከውሃው ጥፋት የተነሣ ከባሻ ባዙቁ (የጥቁር ሹማምንት) ጋር ሊዋጉ ደርሰው ነበር ። እንደነዚያ ክፋት ቢሆን አንድ ወሬ ነጋሪ ባላመለጠም ነበር ። የምኒልክን ደግነት ሲቻለው የሚተው ንጉሥ በኢትዮጵያ መኖሩን የሰማ አውሮፓ ምን ይል ይሆን እንላለን ። እስከዛሬ ድረስ የተደረገውን የጦር ነገር ይኸውና ላኩሁብዎ[1]

እንዲሁም እኝሁ ግራዝማች ዮሴፍ ፡

...ይህ ሁሉ ሲሆን ከመቀሌ ተነሥተን ያል (ፈረሰማይ) እስከን ደርስ ድረስ ኢጣልያኖች የእርቅ ወሬ ሲያወሩ ሰነበቱ ። የነዚያ ሹማምንቶችና ፌልተር የሚባለው ነጋዴ ከሰፈር ሲመላለሱ ነበር ። ጃንሆይም ተንኮላቸውን ዐውቀውባቸው ቶሎ ቶሎ ገሥግሠን ዛታ ላይ ሰፈርን ። ኢጣልያኖቹም ከአዲግራት ወጥተው አዳጋ ሐሙስ ላይ ሰፍረው ነበር ። የኛም ጦር ወጥቶ አጠገባቸው ሰፈረ ። እነዚያም የጦሩን ብዛት ባዩ ጊዜ ለመድፍ የሚያመች ስፍራ ፈልገው ካብ ይከቡ ጀመር ።

ብለው ሲጽፉ ፡ ፌልተር ከኢጣልያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሰላም ፈላጊ መስሎ የመዘጋጃ ጊዜ ለማስገኘት ተልኮ እሰፈራቸው የመጣበትን የማታለል ሰበብ ዐፄ ምኒልክ እንደ ተረዱት ያስታውቃል ። በዚህም ንጉሠ ነገሥቱ የጦር ድርጅቱን ሥራ ከማከናወናቸውም በላይ ወሬና መረጃ መጥቀሙን ተረድተው የየጊዜውን ሁኔታና የጠላትንም አሳብ ያስመረምሩ ነበር ማለት ነው ። በተረፈ በሌላ ረገድ የፌልተርና የግራዝማች ዮሴፍ አጻጻፍ በመሠረቱ አንድ ነው ። ግራዝማች ዮሴፍ ባጻጻፋቸው ንጉሠ ነገሥታቸውን የማድነቅና የማስደነቅ ፡ የማክበርና የማስከበር ነገር ሲያሳዩ ፡ ጣልያኑም የራስ መኰንንን የቅን ወዳጅነት መሳሪያ አድርጎ የኢትዮጵያን መንግሥት በዕርቅ ስም እያታለለ ከኢጣልያ አገር የሚመጣው የእርዳታ ጦር እንደርታ እስኪገባ ድረስ የ35 ቀን ጊዜ እንዲያሰጥ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ተልኮ የመጣበትን መልእክት ፈጽሞ ከተመለሰ በኋላ ፡ ባለፈው ባነበብነው ራፖር ውስጥ የርሱን ወገኖች በአጻጻፉ ለመደገፍና ለሚሠሩት ሁሉ ደንበኛ መንገድ ለመስጠት እንደ ሞከረ ያሳያል ። ቢሆንም ነገሩን በጠቅላላው ስንመለከት ያፄ ምኒልክ ዋና አሳብ ፡ "በወሃ ጥም ሊያልቅ የነበረውን የጦር ሠራዊት ከሞት አትርፌ ዕቃውን የሚጭንበት አጋሰስ አዝዤ ሸኚ ሰጥቼ ስልከለት የአውሮፓ ሕዝብ ይፈርደኛል ፤ ጠላቴንም ይወቅስልኛል ፡ እርሱም ይኸን ሁሉ አመዛዝኖ ሕዝቤን ሳላስጨርስ በእርቅ አገሬን ለቆ ይሔዳል ፤ እምቢ ቢልም የተከተለኝ የጦር ሠራዊት

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ቪዳዬ ዶሲዬ የተገኘ ።



የርሱን ጦር ለመምታትና ለማሸነፍ በማናቸውም ሥፍራ በማናቸውም ጊዜ አይሰንፍም የሚል ነው ።

በዚህ የተደራረበ አሳብና ተስፋ ላይ በመመሥረት ለጠላት የእርቅና የሰላም መንገድ ማሳየታቸውን ሳይለቁ ደግሞ የፍርሃት መስሎት የልብ ልብ እንዳይበቃው ፡ "የክርስቲያን ንጉሥ ነኝ እንጂ ፡ የአሕዛብ ንጉሥ አይደለሁም አሁንም ክርስቲያኖች በከንቱ አይለቁ ሰዎችህን ልከህ አስወስድ ፤ አገር ሊፈልግ የመጣ ጦር ጉድባ ውስጥ አይገባምና ትዋጉም እንደሆነ አንድነት ተሰብስባችሁ ቆዩኝ" ብለው ለዋናው ጠቅላይ አዛዥ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ላኩበት ። እርሱ ግን ፡ ርኅራኄያቸውንም ጉልበታቸውንም ቢሆን የፖለቲካና የእርቅ መንገዳቸውንም ከምንም አልቆጠረውም ። የጠበቀው የእርዳታ ጦር ከጥር ወር ጀምሮ ከኢጣልያ በመርከብ እየተጋዘ ሲደርስለት ፡ በወሃ ጥም ሊሞት የነበረው የመቀሌው ጦር በነጻ ተለቆ በእጁ ሲገባ የዕርቁን ነገር በጭራሽ ትቶ ለዋናው ለዓድዋ ጦርነት ይዘጋጅ ጀመር ።

ቢሆንም ፡ የኢጣልያ ጦር ያላግባብ የሰው አገር ወሰን ጥሶ የወራሪነት ሥራ በሚፈጽምበት ጊዜ ፡ ከዚሁ ያንድ ባታዮ ጦር በመቀሌ ምሽግ ውስጥ ሆኖ የብዙ ኢትዮጵያውያን ደም አፍስሶ ሳለ በወሃ ጥም ቢያልቅም ፡ ሊዋጋ የመጣ ጠላት ነውና ዐውቆ እጁን ካልሰጠ ዝም ብለው ቢረጁት ያም ቢቀር ያለውል እጁን እንዲሰጥ አድርገው መሣሪያውን በሙሉ ቀምተው ወታደሩን በምርኮኝነት ይዘው ለሚፈልጉት የእርቅ ድርድር ሊጠቀሙበት በቻሉ ነበር ። ይኸንንም ሲያደርጉ ከጦርነትና ከወታደርነት ሕግ ወጡ ተብሎ በዓለም አያስፈርድባቸውም ነበር ።

ይኸን የመሰለውን ከዚህም የባሰውን ሁለት የአውሮፓ መንግሥታት በሚዋጉበት ጊዜ እርስ በርሳቸው ይፈጽሙታል ። ሲፈጽሙም ደንበኛ አፈጻጸም መሆኑ በማንም ዘንድ ይገመታል ። በዚህ ዘመን በቅኝ አገርነት ለመገዛት የተፈረደባቸው የአፍሪካና የእስያ አገር መሪዎች ግን ፡ ከፈረንጆች ጋር በሚዋጉበት ጊዜ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ሰበብና ቋፍ ያለበት ነው ። የአንድ አውሮፓዊ መቁሰልና መሞት አገር ወረራን የሚያስከትልበት ጊዜ ነው ። ይኸንንም የገዥነትና የተገዥነት መደብ ለይቶ የፈጠረው አውሮፓውያን በቴክኒክና በሌላው የመሠልጠናቸው ጉዳይ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ በዕርቅና በሰላም ጣልያንን ለማስወጣት የመቀሌንም ጦር በነጻ ለቀው የርኅራኄ ፡ የሥርዓት መንገድ በጥብቅ የፈለጉበት ምክንያት ከአውሮፓ የሚሰነዘረውን ሰበብና ምክንያት ለማስወገድ ሲሉ ነው ። በዚህ ጊዜ የፈረንሳይና የመስኮብ መንግሥታት ለኢትዮጵያ

እጋሹ ቢሆኑም ፣ የጀርመንና የእንግሊዝ መንግሥታት ለኢጣልያ የቃል ኪዳን ጓደኛ ስለነበሩ በተለይ የሱዳን ፣ የኤደንና የሕንድ ጌታ የሆነውና እንዲሁም በበርበራና በዘይላም መዳፉን ያሳረፈው የእንግሊዙ እያያዝ ለኢትዮጵያ እስፈሪ ነበር ። ስለዚህም ጠብ ላለመፍጠርና ሰላማዊ ሆኖ ለመታየት የኛዎቹ ይጣጣሩ ነበር ።

እ.ኤ.አ. 1936 (1927 ዓ.ም) የሙሶሊኒ መንግሥት በጕንደር ቆንስላ ዘበኞች መካከል በተነሣው የርስ በርስ ጠብና የወልወል ግጭት ራሱ ፈጥሮ ጠቅላላውን ወረራ ለመፈጸም ተጠቅሞበት እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

በዓድዋም ጊዜ ፣ በኢጣልያኖች ጋዜጣ አማካይነት ያንዳንድ ጸሐፊ ወሬ በመስማት ፣ "የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭን አገር ሰው የማያከብር ፣ እርስ በርሱ የሚፋጅ ፣ በጠላቱና በምርኮኛው ላይ የጭካኔና የአረመኔነት ሥራ የሚሠራ ነው" እየተባለ በአውሮፖች ዘንድ ይወራ ስለነበረ ፣ ይህ ወሬ ሐሰት መሆኑን ለማስተባበል በንጉሠ ነገሥቱና በራስ መኰንን ዘንድ ከፍ ያለ ጥረት ይደረግ ነበር ። ሞንዶን ቪዳዬ ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ የጋዜጣ ወኪል ከመሆኑም በላይ አዲስ አበባ ላሉት ለኢትዮጵያ ወዳጆች ለነሙሴ ኢልግ ፣ ለነሙሴ ሽፍነ ፣ ለነሙሴ ሳቡሬ ፣ ለነሙሴ ሊዎንቴቭና ለቀሩትም ሁሉ እንደ ሽማግሌ የሚቀጠር ሰው ስለነበረ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ማናቸውንም የጦርነቱን ሁኔታ ለርሱ በቀጥታ ይጽፉለት ነበር ። በዚህም ላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ለአውሮፓ ፣ የአውሮፓንና የኢጣልያንን አገር ሁኔታ ፣ በምክር ቤትና በጋዜጣ የተባለውን ሁሉ ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ በጽሑፍ ይገልጽል ። ማናቸውንም ደኅኛ ነገር የሚመክር ሰው ነበርና ንጉሠ ነገሥቱም በበኩላቸው ፣ ኢጣልያኖቹ ስለሚያወሩት ሐሰተኛ ወሬ የጻፉለትን በሚከተለው እንመልከት ።

> ምን እንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን እንዴት ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። በታኅሣሥ 16 ቀን በአዲስ አበባ ከተማ የተጻፈ ደብዳቤህ ደረሰኝ ። ከአውሮፓ የመጣውን ወሬ ስለላክህብኝ እግዚአብሔር ያመስግንህ ። እንግዲህም የሚመጣውን ወሬ ተሉ ተሉ እንድትልክልኝ ይሁን ። የኛን የጦርነት ደብዳቤ ከግራዝማች የሴፍ ደብዳቤ ታገኘዋለህ ። የኢጣልያኖች የውሸት ወሬ አያልቅም ሁላችንን እንደ ገደሉ ያወራሉ ። እኛ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ሁላችንም ደህና ነን ። እኛን በሕይወት ያለነውን ሞቱ እያሉ ይልቅ የሞቱትን የሰዎቻቸውን ቁጥር ማወቅ ደግ ነበር ። የተማረኩትን ኢጣልያኖች እንዳይበደሉ ብለህ የላክብኝን እኛ ባገራችን እንኳን ክርስቲያንን ፣ አሕዛብንም ቢሆን ከተማረከ በኋላ እንዳንበድል ታውቁታላችሁ ። እውነም አክብሬ ማስተመጨ ኢጣልያኖች ያመሰግኑኛል ብዬ አይደለም ። የክርስቲያን ሥርዓት እንዳይጐድል ብዬ ነው ። በአዲስ



> አበባ ከተማ ያሉት ፈረንጆች አንተ ቤት ተሰብስበው እኔን ላይ የኔ ሰዎች ስለአደረጉት ድል ብዙ ደስታ ስላደረጉ እኔም ደስ አለኝ ። በየካቲት 13 ቀን በ1887 ዓ.ም. ተጻፈ ።

ሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ፣ በራስ ዳርጌ አማካይነት ወይም በግራዝማች የሴፍ በኩል የሚደርሰውን ደብዳቤና የጦርነቱን ማስረጃ አዲስ አበባ ላሉት የውጭ አገር ሰዎች ጓደኞቹ ነገሩን ማስረዳቱን ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን የጦርነት ድል ባገኙ ጊዜ ፈረንጆቹ እርሱ ቤት ተሰብስበው የደስታ በዓል ያደርጉም እንደነበረ በደብዳቤው ተገልጿል ።

በርሱና በእንደቤራው በራስ ዳርጌ መካከል የቅርብ ግንኙነት ነበር። እርሱም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የሚልከው በርሳቸው በኩል ስለነበረ ፣ በተረፈ የጦርነቱንም ሁኔታ የድሉንም ደስታ ይካፈሉ እንደ ነበር ከዚህ ቀጥሎ ያለው ወደርሱ የተጻፈው የትልቁ የራስ ዳርጌ ደብዳቤ ያስረዳል ።

> የተላከ ከራስ ዳርጌ ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን ከተለያየን ብዙውን እንዴት አመሸህ ። የሰደድህልኝንም ደብዳቤ አየሁት ። ነገር ግን ይድረስ ወደ ጃንሆይ የሚል ቢሆን ጃ(ደንገር) ብሎኝ ነበር ። ከቤትህ ሽማግሌዎች ጠርተህ የደስታ ፈንጠዝያ ያደረግኸውን ሰማሁ ። እኔም እንደዚሁ ከቤቱ ገብቼ ከአሽከሮቼ ጋር ፈንጠዝያ ሳደርግ ዋልሁ ። እግዚአብሔር ደግሞ ጭራሹን ያብጅልን ። ደግሞ ሙሴ ኮለሽት ሲሔድ ተገናኝተን ተመካከረን ሁሉንም እንልክሃለን ።*

ዝ ማኅተም ዘእራስ ዳርጌ ርእሰ መኳንንት [1]

ስለ መቀሌ ምሽግና ስለ ጋልያኖ አወጣጥ ጉዳይ ፣ በበኩላቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በመጽሐፋቸው እንደዚህ ሲሉ አስፍረውታል ።

> . . . ሬልተር የሚባል የኢጣልያ ነጋዴ . . . ኢጣልያኖችን ለማስታረቅ ወደ አዲግራት ሔዶ ነበርና ያንለት ወደ ሰፈር መጣ ከዚ ምኒልክም ዘንድ በደረሰ ጊዜ እንደዚህ አለ ። መቀሌ ከእርድ ውስጥ የነበሩት ኢጣልያኖች ተመልሰው አዲግራት ካልገቡልን የእርቅ ነገር መነጋገር አይሆንልንም አሉ ብሎ ነገራቸው ። ዐፄ ምኒልክም በመሃ ግም ተከበው በእጂ ወብማቸው ፣ በእግሬ ረግጫቸው የነበሩትን እነዚህን አልነካቸውም። አንተው እንደ ተመኘኸው ስጥቼ እሰድጋለሁ።

* ኮለሽት የሚባለው በዓድዋ ጦርነት ጊዜ በበጅሮንድ ባልቻ ውስጥ ሆኖ የዓድዋን ጦርነት የተካፈለ ፈረንሳዊ ነው ይባላል ። ለመካፈሉ የተረጋገጠ ምንጭ የለም ። ይልቁስ የመትረየስና የመድፍ አተኳኰስ ለኢትዮጵያውያን ያስተማረ ይመስላል ።
1 እነዚህ ለሞንዶን ቪዳዬ የተጻፉት ደብዳቤዎች በፓሪስ ቤተ መዛግብት በእጅ ለንድ ክፍል በቍጥር 82 በሙሴ ሞንዶን ፋይል ይገኛሉ ።

ነገር ግን ፣ እነዚህን ሰዎች ከነመድፋቸው ፣ ከነነፍጣቸው መስደዴ የሞኘነት አይምሰልህ ። ስለፍቅር(ስለሰላም) ያደረግሁት ነው ። ደግሞ እነዚህን ጥቂት ሰዎች አልነካቸውም ማለቴ መንግሥቴን ለማክበር ነው ። አሁንም ብትታረቁም ድንቅ ፤ ጦርነትም ከከጀላችሁ እነዚህን ጨምራችሁ ጠቅላችሁ ኑ ።[1]

ፊልተር "እነዚህ ካልተቀቁ የሰላም ንግግር አይጀመርም" ብለዋል ያለው ሐሰትን የተንተራሰ አባባል ነው ። ባዬ ምኒልክ ዘንድ ያለውን ሰላም ፈላጊነት በመጠቀም ሰዎቹን ለማስለቀቅና ከዚያ በኋላ ለመዋጋት በኢጣልያኖቹ በኩል ያሰውን የጋለ ፍላጎት ያውቀዋል ። የርሱም አመጣጥ ጊዜ ለማግኚያ መሆኑን ባሰፈው ተመልክተነዋል ። ዳግማዊ ምኒልክም ባነጋገራቸው ፣ "እነዚህን መስደዴ የሞኘነት አይምሰልህ" ሲሉ የኢጣልያኖቹን ተንኮል እንደተገነዘቡት ያመለክታል። ነገር ግን ከላይ እንዳመለከትነው ፣ እነዚህን በመልቀቅ ለጢብ ምክንያትና ሰበብ የሚሆነውን ሁሉ በማስወገድ የዓለምን ፍርድ ለማግኘት በጣልያን ላይ ለማስፈረድ ሲሉ የተቻለውን ያህል እንደተጣጣሩ ይታያል ። ባንደ ወገን ደግሞ ፣ "ብትታረቁም ድንቅ ፣ ጦርነትም ከከጀላችሁ እነዚህን ጨምራችሁ ኑ" ማለታቸው ለድል አድራጊነታቸው የተማመኑ ይመስላል ።

የዚህን የፖለቲካ ውዝግብ ደህና አድርጎ የማያጤነው ወታደር የጋልያኖ ጦር ከነጦር መሣሪያው ኋዙን ጠቅሎ ከምሽጉ በወጣ ጊዜ ዘመድና ወገኑ የሞተበት ሁሉ በቁጭት እያወካ ለመቃወም የንቅናቄ ምልክት ባሳየ ቁጥር ፣ "ተው እርጋ" እያሉ ጠመንጃቸውን አንግበው ፣ በቀኝ እጃቸው ዘንግ ይዘው ኢጣልያኖቹን ከነባንዳዎቻቸው ከበው ይከላከሉ የነበሩት በመቀሌው ጦርነት ይበልጥ የተጎዱት የሐረር የጦር ሹማምንት ናቸው ። በምኒልክ ቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓትን የተካኑት ወደ አውሮፓ በመሔድ ዘመናዊው የሥልጣኔ ጮራ ገረፍ ያደረጋቸው ራስ መኰንን በፋንታቸው ይህን ግብረ ገብነት ለጭፍሮቻቸው አስተምረዋል ማለት ነው ። መኰንን ለምኒልክ አገረ ገዥና የጦር መሪ ከመሆናቸው አልፈው ፣ ልክ እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚቆጠሩ የዲፕሎማቲክ ኃላፊ ጭምር ናቸው ። ሰላዩ ካፑቺ ለኢጣልያን ባለሥልጣኖች በጻፈው ራፖር ውስጥ ፣ "ከሁሉ የበለጠ የኛ ኃይለኛ ጠላት ራስ መኰንን ነው ፤ ምክንያቱም መኰንን ባንድ ወገን ብልህና ታታሪ ፣ በሌላ ወገን የምኒልክ ታማኝ በመሆኑ ነው" የሚሉ ቃላት አስፍሯል ።[2]

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ.62 ገጽ 249,250

2 1 Russi in Etiopia - Carlo Zachi, P. 76.



ከመቀሌ ምሽግ የጋልያኖ ጦር ከመውጣቱ በፊት ስምምነት እንደ ተደረገ የኢጣልያ ባንዲራ ወርዶ ነጭ ባንዲራ ተሰቅሎ ነበር። አሁን ደግሞ ፣ ምሽጉን በሙሉ እጅ ካደረጉ በኋላ በጅሮንድ ባልቻ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዘው ሔደው ግባት (የደስታ ተኩስ) እየተተኮሰ የኢትዮጵያ ባንዲራ በገሃድ ተሰቀለ ።

ማናቸውም ዝግጅት በዚህ ዓይነት ከተፈጸመ በኋላ ፣ ጋልያኖ ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው በቅሎ ተቀምጦ ጉዞው ተጀመረ ። ምንም እንኳን ለጠቅላላው የበላይ ጠባቂነት የራስ መኰንን ቢሆንም ፣ እርሳቸው ደግሞ ፊታውራሪ ደሳለኝን በቅርብ ሆነው እየጠበቁ አዲግራት እንዲያደርሱት አዘዋቸው ነበርና በማናቸውም ዝርዝር ጉዳያቸውን ጣልያኖቹ በአቶ ወልደ አማኑኤል አስተርጓሚነት ይጠይቁ የነበረው ፊታውራሪ ደሳለኝን ነበር ። ለፊታውራሪ ደሳለኝም ረዳት ከዚህ በፊት በዕርቅ ምክንያት ወደ መቀሌ ምሽግ ተመላልሰው የነበሩትና ከጋልያኖም የተዋወቁት ብላታ እንግዳ የሚባሉ ነበሩ ።

እ.ኤ.አ. ጥር 22 ቀን ወደ ማታ ጋልያኖ ከነጓዙ ሰፈሩን ለቆ በራስ መኰንን ጦር እንደ ተከበበ ፣ የኢትዮጵያን መኳንንት የበረከቱ ድንኳኖች እያቋረጠ ወጥቶ በቅርብ ከሰፈረ በኋላ ፣ በማግሥቱ እዚያው ውሎ ሆኖ በጥር 24 ቀን እሱና ጦሩ ጉዟቸውን ቀጥለው የንጉሠ ነገሥቱ ቀዩ ድንኳን የተተከለበትን የማሳቦን ሜዳ እያዩ ወደ ማይመኸያን አመሩ ። በዚህ ዓይነት በየመንገዱ እያረፉ በጥር 28 ቀን አይባ ደርሰው ሳለ ፣ በመካከሉ አስቀድሞ እንደተነጋገሩት ስለእርቅ ጉዳይ ከባራቲዬሪ ትልቅ ሰው ተመርጦ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ ነበርና ሳይመጣ ስለዘገየ ራስ መኰንንም አይባ ላይ ሰፈሩ ። ጋልያኖ እስከ ድንኳናቸው ድረስ እየሔደ ፣ "ጉዟችን ዘገየብን" እያለ ሲከራከር እርሳቸውም ፣ "ባራቲዬሪ ማገርር ሳልሳን እልካለሁ ብሎ እስካሁን ባለመላኩ ቃሉን አልጠበቀም" እያሉ ሲመልሱ ቆዩና በመጨረሻ ሹማምንቱ መያዣ ሆነው እንዲቆዩ ተደረገ ። ጋልያኖና ጓዙ በፊታውራሪ ደሳለኝ መሪነት ወደ አዲግራት ጉዟቸውን ቀጥለው በሐውዜን አልፈው እዳጋ ሐሙስ ደርሰው የሁለት ሰዓት ዕረፍት አደረጉ ። አዲግራት በናፍቆት የሚጠበቀው ጋልያኖና ጓዙ እዳጋ ሐሙስ የመድረሳቸው ወሬ ሲሰማ ፣ ጠቅላይ አዝማቹ ሌተና ጄኔራል ባራቲዬሪ ራሱ እንደ ታጀበ ጋልያኖን ለመቀበል ጉዞ ጀምሮ በጥር 30 ቀን ተገናኙ።

በመንገድ በተገናኙ ጊዜ ፣ ጄኔራሉ ከፈረሱ ላይ ወርዶ አንገቱን እንቆ ሲስመው ሌሎቹ የጦር አለቆች የቀሩትን እያቀፉ ይስሙ ነበር ። "የኢትዮጵያ ጦር በወሃ ጥም ይጨርሳቸዋል እንጂ በዋዛ አይለቃቸውም ። ከምሽግም እንዲወጡ ያደረገው በእጁ ከገቡ በኋላ እንደ

ልቡ ለመፍጀት ሲል ነው ። አልነካቸውም ብሎ ቢምልም ፣ ቃሉን ሊያከብር አይችልም” የሚል እምነት በኢጣልያኖቹ ዘንድ ነበርና አሁን በዚህ ዓይነት ሁሉም በደህና ሁኔታ ደርሰው ከፊታውራሬ ደሳለኝ እጅ በክበረታና በሐቅ ሲረከቧቸው ከደስታ ጋር መደነቃቸውን አልደበቁም ። ከዚያ ጀኔራል ባራቲዬሪ ከፊታውራሪ ደሳለኝ ጋር መያዣ ሆነው ወደ ኋላ ስለቀሩት ሹማምንት ወዳጄ ምኒልክ ስለሚላከው ባለሥልጣን አጭር ንግግር ካደረጉ በኋላ ፣ በፈረሱ ላይ ወጥቶ በጉኑ የሌተናና ኮሎኔልነት ማዕረግ የተቀበለውን ጋልያኖን አድርጎ ጉዞውን በመቀጠል ወደ ዋናው ሰፈሩ ወደ አዲግራት ሔደ ። እዚያም በደረሱ ጊዜ የጦር ሠራዊቱ በሙሉ በሰልፍ በብረት ሰላምታ ሲያቀርብ ለዚህ ሰላምታ መልሱን ይሰጥ ዘንድ ጄኔራሉ በፈቃዱ ለማስከበር ሲል ለኰሎኔል ጋልያኖ ተወለት ።

ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት በሰልፍ ፣ በሙዚቃና በዘፈን ከተፈጸመ በኋላ ፣ ቁስለኛውንና ደካማውን ወደ ሆስፒታል የማስተኛቱ ፣ ለተራቆቱት ወይም ልብሳቸው ለተጐሳቆለው ለነጭና ለጥቁር ወታደር ልብስና ጫማ የማደሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ ፣ እነዚህ የኤርትራንና የኢጣልያንን አገር ወሬ ሲጠያየቁ ፣ እነዚያ ደግሞ በ43 ቀን ውስጥ በመቀሌ ምሽግ ስለ ተደረገው ጦርነት ፣ ስለ አወጣጣቸውና ስለ ጠቅላላው ሁኔታ ማወቅ እየፈለጉ ሲጫወቱ ሰነበቱ ።[1] በኢጣልያ አገር የጋልያኖ ከመቀሌ ወደ አዲግራት ለመሔድ መቻል እንደ አንድ ታላቅ ድል ተቆጥሮ ሰሞኑን ሕዝቡ ሁሉ በዘፈን ፣ በደስታና በዕልልታ በዓል አድርጎ ስላከበረ ፣ ዶሚኒኮ ፋሪኒ የሚባለው ጸሐፊ ፣ “የኢጣልያን ሕዝብ ዘፋኝነትና ቀላልነት ያሳያል” ሲል ከተቸ በኋላ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ፣ “በመቀሌ ምሽግ ተከላክለው ወደ አዲግራት ለተመለሱት ልዩ ኒሻን ተዘጋጅቶ ይሰጥ” የሚል አሳብ ለምክር ቤቱ ቢያቀርብ ሲድኔይ ሶኒኖ የሚባለው አባል ፣ “ለተሸነፉት ይኸ ይሰጥ ካልክ ላሸነፉት ምን ልትሰጥ ነው” ብሎ አፌዘበት ።[2]

1 L' Assedio di Maccalle, V. Mantegazza, PP. 398 - 428 ; Memoire d' Afrique,O. Baratieri , PP. 322 - 330; Gli Italiani in Africa Orientale, A.Del Boca, PP. 624-657.

2 Gli Italiani in Africa Orientale PP. 626 -627.



# ክፍል አራት

## የዓድዋ ጦርነት

## ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

### የኢትዮጵያ ጦር ከመቀሌ ወደ ዓድዋ መዛወር—ስለ እርቅ ጉዳይ ማጆር ሳልሳ ተልኮ ወደ ዐፄ ምኒልክ እንደመጣ

በመቀሌ ምሽግ መለቀቅ በተደረገው ስምምነት ሁለቱም መንግሥታት ተጠቅመዋል ማለት ይቻላል ። የኢጣልያ ጥቅም አንደኛ በስምምነቱ ሰበብ ከኢጣልያ ለሚመጣው ጦር የመዘጋጃ ጊዜና ሁለተኛ በውሃ ጥምና በረኃብ ሊያልቅ የነበረውን አንድ ክፍል ጦር ከነመሣሪያው በደህና ማግኘቱ ነው ። የኢትዮጵያ ጥቅም ደግሞ በማናቸውም ረገድ በተለይ ለትግሬ እንደዋና ከተማ የሚቆጠረውንና ያፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የሚገኝበትን መቀሌን አስለቅቆ ጠላትን እስከ አዲግራት ድረስ መግፋቱ ከአላጌ ጦርነት ወዲህ ይኸኛው ደግሞ እንደ ሁለተኛ ድል መቆጠሩ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ሁልጊዜ ደም ሳይፈስ ጠላትን ካገር አስወጣለሁ የሚለው ተስፋ ፈጽሞ ከአሳባቸው ስለ አልጠፋ ፣ የስምምነቱን ጉዳይ ወደ ፍጻሜ ላደረሰው ለፌልተር ፣ “የሰው አገር እወስዳለሁ ብሎ የመጣ እንድባ ተብቶ በውሃ ጥም አያልቅም . . . አሁንም በከንቱ አይለቁ ፤ ሰዎችህን ልከህ አስወስድ ፤ ትጥቅም እንደሆን አንድነት ተሰብስባችሁ ቆዩኝ ፣ እኔም እመጣለሁ” የሚል በራስ የመተማመንና የከረረ ቃል ነግረው ወደ ባራቲዬሪ ከላኩ ወዲህ ፌልተርም ፣ “እኔ የመዋዋል ሥልጣን የለኝም ፣ ሌላ ትልቅ ሰው ይመጣል” ብሎ ቃል ሰጥቶ ነበር ። ነገር ግን ፣ ጣልያኖቹ ጊዜ ለማግኘት እንጂ ሰላም ለማድረግ በፍጹም ስለማይፈልጉ ፣ ለወሬ ያህል ይመጣል የተባለው ሳይመጣ በመዘግየቱ ከጋልያኖ ጭፍሮች ውስጥ ዘጠኝ መኰንኖች እንደ መያዣ ቆይተው ነበር ። እነዚህም “ግደለም ይሒዱ” ተብለው በመጨረሻ ተለቀው ወደ ወገኖቻቸው ሔዱ ። በኋላም ባራቲዬሪ ስለ ሰላም ለመዋዋል ትልቅ ሰው ይላካል ያለውን በማመን ዳግማዊ ምኒልክ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ከንጉሥ መንገሻ አቲከም ፣ ይልቁንም የውጭ ጉዳዮን ተግባር ከሚፈጽሙት ከራስ መኰንን ጋር ተመካከረው

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለኢጣልያ ንጉሥ ጽፈው ለባራቲዬሪ ላኩለት ።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ. . .ለግርማዊ ኡምቤርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ሰላም ለርስዎ ይሁን ። ስላምና ወዳጅነት መፈለግዎን ጄኔራል ባራቲዬሪ ስለነገረኝ ደስ ብሎኛል ። የራሴን የክርስቲያንነት እምነት ለመግለጽ ስል በእንዳ ኢየሱስ ምሽግ ተከበው ተጨንቀው በወሃ ጥም አልቀው በአገራችን ውስጥ ሊረገጡ የቀረቡትን ከነዕቃቸው በመልካም ሁኔታ በራስ መኰንን ሸኚነት አስወጥተን ሰደድናቸው ። አሁንም ተነጋግሮ ስለ ሰላም ሊዋዋል የሚፈልጉትን ሰው ያስታውቁኝና እኔም ጠቡ ቀርቶ ስለ ስላም የሚነጋገረውን ወኪሌን አደርጋለሁ ።

ይኸን ከጸፉና ለንጉሡ ይልክ ዘንድ ለባራቲዬሪ ከላኩ በኋላ ፣ዳግማዊ ምኒልክ ከሰፈሩበት ከመቀሌ በማግሥቱ ተነሥተው ወደ ሐውዜን ፣ ከሐውዜን ወደ ፈረስ ማይ ፣ ከፈረስ ማይ ወደ ሳውሪያ ፣ ከዚያም ወደ ግራቸው ታጥፈው በገንደብታ አድርገው ዓድዋ ገብተው በተለይ ዬሐ ከሚባለው ጥንታዊና ታሪካዊ ቦታ ሠፈራቸውን አደረጉ። ሐውዜን የነበሩ ጊዜ ወደ አዲግራት ስለቀረቡ ፣ ይወጉናል የሚል ፍራቻ ኢጣልያኖቹ አድሮባቸው ለጦርነት መሰናዳት ይዘው ነበር ።

ዋናው አዝማች ፣ ያዜ ምኒልክን ደብዳቤ ራሱን ወደ ሮማ ለመላክ ጊዜው አጣዳፊ ስለሆነ ፣ የደብዳቤውን አሳብ በቴሌግራም አስታውቆ በጠቅላላው የመንግሥቱ አሳብ ምን እንደሆነ እንዲገለጽለት በጥር 28 ቀን ጠይቆ ስለነበረ ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከባሮን ብላን ዘንድ እንደዚህ የሚል ቃል ዕለቱን መጣለት ።

> ባሁኑ ለጦርነት በተሰለፍንበት ሰዓት ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ላይ የሚኖረንን አቅዋማችንን የሚያረጋግጥ አንድ የጦርነት ድል ኢጣልያ ሳታገኝ አሁን በሚደረገው የስላም ውል ምንም ዐይነት ጥቅም እንደ ማይገኝ የንጉሡ መንግሥት ያምናል ።[1]

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ደግሞ በበኩሉ ፣ "እምባ አላጌና መቀሌ ክብር ቢኖረውም ፣ ሁለት ውድቀት ያገኘንባቸው ናቸው ። የኢጣልያ የንጉሡ ክብር በእጅህ ነው ያለው" ሲል አስተላለፈለት ። ትርጓሜው በአላጌና በመቀሌ መካከል ምንም እንኳን የኛዎቹ ክብር ያለው የመከላከል ሥራ ቢሠሩም ፣ መጨረሻው መሸነፍ ስለሆነ እንደ ምንም ተዋግተህ አሸንፈህ አንድ ድል አግኝተህ ክብራችንን አድስ የሚል ነው ። በነዚህ ዐይነት ከዚህ ከሁለት የኢትዮጵያ ድሎች በኋላ አንድ የመመለሻ ድል በጣም እንደ ናፈቃቸው ይታያል ።

1 Italia ed Etiopia .. Conti - Rossini . . . PP. 257 - 264; Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca, PP.629 -630; The Campaign of Adwa and the Rise of Menelik, Chap. VII, PP. 217 -238.



ስለዚህ ባራቲዬሪ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ወደ ዓድዋ ሲጓዝ ፣ ሐውዜን በሰፈረበት ጊዜ ከአዲግራት ወጥቶ መዋጋት እየዳዳው ፣ ማሸነፍም እየጓጓ ደግሞ እየፈራና እያመነታ ፣ በዚሁ መካከል ጠቅላይ ሚኒስትሩም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም ጦርነቱን እየገፉፉ ለሚያስተላልፉለት ቴሌግራም እርሱም በበኩሉ የኢትዮጵያን 'የጦር ድርጅት እየጠቀሰ በሌላው ወገን ደግሞ ፣ በገዳሪፍ ደርቡሾች ለውጊያ መሰብሰባቸውን በመግለጽ ለጊዜው ውጊያው አስቸጋሪ መሆኑን ገልጾ ነበር። በዚህም ዓይነት ብዙ ውዝግብ ካለቆቹ ጋር ከገጠመ በኋላ መደምደሚያውን ከኢትዮጵያ ጋር የእርቅ አሳብ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተነድፎ ቀደም ብሎ ተልኮለት ነበር ። ከሮማ የተላከው ኩራትና ዕብሪት የተሞላበት የዕርቅ ድርድር የሚከተለው ነው ።

፩ኛ. የኢጣልያ መንግሥት እስከ አሸንጌና እስከ ተከዜ ድረስ ሙሉ ትግሬን ጠቅሎ በቀጥታ ገዥነት እንዲኖረው ፣

፪ኛ. የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ በቀረው እስከ ሱማልያ ፣ ከወዲህም እስከ ኦሞ ወንዝ መጨረሻ ድረስ ባለው በኢትዮጵያ ግዛት ላይ የበላይነቱ እንዲታወቅ ፣

፫ኛ. ለውጭው ዓለም የኢትዮጵያ ወኪልና ጠባቂ ኢጣልያ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅና በኢትዮጵያ ያሉ የውጭ አገር ሰዎች (ይኸውም ማለት ለኢትዮጵያ የሚረዱት የመስኮብና የፈረንሳይ ተወላጆች) እንዲወጡ ፣

፬ኛ. ንጉሠ ነገሥቱና የአውራጃ ገዥዎች ቁጥሩን ከሚወስንላቸው አልፈው የኢጣልያ መንግሥት ሳይፈቅድ ወታደር እንዳያደራጁ፣

፭ኛ. ራሶችና ያውራጃ ገዥዎች ከመሾማቸው በፊት ለፈቃድ የኢጣልያ መንግሥት እንዲጠየቅ ፣

፮ኛ. በኤርትራ አንድ ወራሪ ቢመጣ ንጉሡና ራሶቹ ኃይላቸውን ይዘው ወጥተው እንዲረዱ ፣

፯ኛ. በንጉሡና በራሶቹ መካከል ፣ በራሶቹና በሹሞቻቸው መካከል ክርክር ቢፈጠር ጉዳዩ ለኢጣልያ መንግሥት ቀርቦ እንዲወሰን የሚል በ7 አንቀጽ ላይ የተመደበ ነበር ።[1]

ጄኔራል ባራቲዬሪ ይኸን የመሰለ የማይታሰብ የስምምነት አሳብ ቢደርሰውም ፣ ራሱ እንደ ገለጸው በነጻነቱ የሚኮራና ተዋጊ ሕዝብ የተዘጋጀ ጦር እያለው ተዋግቶ ከመሸነፉ በፊት ይኸን የመሰለውን

1 Tomasso Salsa, E Canevari E Comisso PP 288—290

አሳብ እንደማይቀበል ስለሚያውቅ ፤ ይኸንኑ ከበላዮቹ ጋር በምስጢር ሲነጋገርበት ቆይቶ ነበር ። የበላዮቹም ኢትዮጵያን ገና ከመጀመሪያ እንደ ራሳቸው ይዞታ በመቁጠር በአዳጊና በመቀሌ መሸነፋቸው እየቆጠቆጣቸው ፤ ይኸ ሁሉ ሁኔታ ሊታደስ የሚችለው ከዚህ በላይ ያለው ጥያቄ ሲፈጸም ብቻ ነው የሚል አሳብ ነበራቸው ። ነገር ግን ፤ ባራቲዬሪ እንደ ምንም የቀረበውን አሳብ አስቀርቶ ጉዳዩን ከሁለት መድቦ አቀረበ።

፭ኛ. የውጫሌ ውል ታድሶ እንዲረጋ ፤

፮ኛ. የኢጣልያ ባንዲራ እስከ ተሰቀለበት ድረስ ያለው አገር ለኢጣልያ እንዲሰጥ ።

የሚል አሳብ ባጭሩ አዘጋጅቶ በማዦር ሳልሳ እጅ እ. ኤ. አ. የካቲት 11 ቀን 1896 ወዳጼ ምኒልክ ላከ ። ማዦር ቶማሶ ሳልሳ በዚህ ጊዜ ዋና የፖለቲካውን ክፍል የሚመራ የታወቀ ወጣትና ብልህ የጦር መኰንን ነው ። ምክትል ሹፍ ዶታ ማዦሩም እርሱ ነው ። ከርሱም ጋር ካፒቴን አንጌራ የሚባለው የኢጣልያ ጦር መኰንንና የታወቁት አስተርጓሚ ገብረ እግዚአብሔር አብረው መጥተዋል ። ነገር ግን ፤ ስብሰባውን በምንም አኳኋን አልተካፈሉም ። በንግሩም ጊዜ ዋናዎቹ የንጉሠ ነገሥቱ አስተርጓሚዎች ግራዝማች የሴፍና አቶ ወልደ አማኑኤል ናቸው ። ወደ ፍሬው ነገር ከመግባታችን በፊት ከአዲግራት ወደ ዓድዋ (ዩሃ) መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር የሰነበተ ጊዜ ያየውን ራሱ ማዦር ሳልሳ ኢጣልያ አገር ላለው ለወንድሙ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ያሰፈረውን መመልከቱ ይጠቅማል። ቃሉ እንደዚህ የሚል ነው ።

ውድ ወንድሜ ሆይ . . . መንግሥታችን ምንም እንኳን ሊሆን የማይችለውን ውል ጨምር ዕርቅ እንድናደርግ ቢፈቅድ አገረ ገዥው (ባራቲዬሪ) ይኸንን ዕርቅ እንድፈጽም ሳይሆን የቀረው ቢቀር አገረ መንግዴን የጠላትን ኃይልና አቀማመጥ እንድመለከት አዞኝ ወደዚያ ስሔድ መጀመሪያ ከራስ መኰንን ሰፈር ደረስሁ ። እዚያም ሆኜ ባለቆቻቸው ዙሪያ በደንብ የተተከሉትን 2500 ድንኳኖች ያሉበትን ስፍራ ተመለከትሁ ። ከኔም ጋር ካፒቴን አንጌራ ነበር ። ራስ መኰንንም ምንም እንኳን ቢታመሙ ፤ በቶሎ በፍቅር መልክ ተቀብለውን የመጣንበትንም ጉዳይ ባጭሩ ከተነጋገርን በኋላ መሪ ሰጥተው ወዳጼ ምኒልክ ላኩን ። . . . 2 ኪሎ ሜትር ስፋት 5 ወይም 6 ኪሎ ሜትር ቁመት ባለው በዩሃ ረባዳ ስፍራ ላይ ከራስ መኰንን ሰፈር በስተጀርባ ስንደርስ አስደናቂውን የንጉሡን ሰፈር አየን ። ሸለቆዎቹና ስፍራዎቹ በሙሉ በድንኳን ተሸፍነዋል ። የድንኳኖቹም ቁጥር 20000 ይመስለኛል ። የነርሱም የትልቅነታቸው መጠን የቀለማቸው ዓይነት ልዩ ልዩ ነው ። አብዛኛው ነጭ የቀረው ጥቋቁር የሸዋ ጨርቅ ነው ። በረባዳው ስፍራ ከመካከል ልዩ ልዩ የሚያማምር ቀለም ያላቸው ከከበረ ጨርቅ የተሠሩት የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳኖች አሉ ። ቁመታቸው 2 ሜትር ተኩል ሆኖ በዚያው በድንኳኑ ዙሪያ ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ትልቅ



የዙሪያ መጋረጃ ክፍል አለ ። የውጭው ክፍል የጨርቅ ፤ የውስጠኛው ንጉሡ ታላላቅ ሰዎችን የሚቀበሉበት የሐር ነው ።

ንጉሡ እስካሉበት እስከምንደርስ በምናቋርጥበት ሰፈር ሰው ሁሉ በመገረም ይመለከተን ነበር . . . ሰፈሩን ሰናልፍ እዳጋ ሥሉስ ከሚባለው ገበያ ደረስን ። በዚህም ገበያ 5 ወይም 6 ሺህ የሚሆኑ ወታደሮች እህልና ጨርቃ ጨርቅ በትሩም ይገበያዩ ነበር ።

በንጉሡ ድንኳን አጠገብ ትንሽ ደቂቃዎች እንደ ቆየን ዐጼ ምኒልክ ወዳሉበት ገባን ። እርሳቸውም በአንድ በወርቅ የተሠራ ልብስ በለበሰ መከዳ ላይ . . .ተቀምጠው ባሉበት ክፍልም የፈረንሳይና የሩሲያ ብዙ ሥጋጃዎች ተነጥፈው ነበር ። 2 የእንጨት ባለቆዳ ወንበሮች ነበሩ . . . በንጉሠ ነገሥቱም ዙሪያ ራሶች ተቀምጠው ነበር ። ንጉሡና ከነርሱም ትራ ጥቁር በርኖስ ለብሰው ራሳቸውን ሻሽ አስረው ሲታዩ በንጉሡ በስተጀርባ በልዩ ልዩ ልብስ ያጌጡ አለቆች ቆመው ነበር ።

ምኒልክ በፍሥሐ ገጽ ከተቀበሉኝ በኋላ ፤ እንደ አውሮፓ ደንብ እጃቸውን ዘርግተው ጨበጡኝና ቀጥሎ እወንበሩ ላይ እንድቀመጥ አመለከቱኝ ። ትንሽ የሰላምታ ንግግር ከተለዋወጥን በኋላ ፤ ሒዱ ትንሽ ዕረፉና በኋላ እንነጋገራለን ብለው ሲያሰናብቱንም እንደዚሁ በደስታ እጃችንን ጨበጡን ። በዚህ በመጀመሪያው ግንኙነት ከምኒልክ በቀር የቀሩትን ራሶች በጨረፍታ እንጂ ደህና አድርጌ አልተመለከትኋቸውም ። እነርሱም (እኔና ምኒልክ በምንነጋገርበት ጊዜ) አንድ ጊዜም ንግግር ከአንደበታቸው አልወጣም ። ምኒልክ 53 ወይም 54 ዓመት ዕድሜ እያላቸው ከ40 ዓመት ትንሽ የሚያልፉ ይመስላሉ ። ቆዳቸው ብዙ ጥቁር አይደለም ጠይም ናቸው ፤ ጠይምነታቸውንም በመጠኑ ሽበት ወርሶታል ። ደስ የሚያሰኝ መልክ(ገጽታ) አላቸው ። . . . ከብዙ አስደሳች ሁኔታ ጋር ፤ ሲነጋገሩ ደጋግመው ፈገግታ እያሳዩ ነው ። . . .ከዚያ ወጥተን ወደ መድፈኞች አለቃ ወደ በጅሮንድ ባልቻ ዘንድ. . .ሔደን ባበሻ ደንብ ቁርስ አደረግን . . . ቀድሞ የማውቃቸውንም ሹማምንት አገኘሁ እኔ ያመጣሁትን ወይን ጠጅ አብረን ጠጣን ። በዚሁም ጊዜ ንጉሡ ሳያስጠሩን ብዙ ሰዓቶች አለፉ ። በመጨረሻው አንድ ሹም መጥቶ "በንግግሩ ላይ ራስ መኰንን እንዲገኙ ፈልጌ ነበር ። ዳሩ ግን ፤ ቢጠሩም በጊዜው ስለታመሙ አልቻሉምና ለዛሬ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ቢሆንም መጥታችሁ ሰላምታ ብንገናኝ መልካም ነው" የሚል የንጉሡን ቃል ነገር ይዞን ሔደና ሰላምታ ተሰጣጣን ። ከዚያም ጉዳዩ በመዘግየቱ ይቅርታ ጠይቀው አሰናበቱንና ወደ በጅሮንድ ባልቻ ድንኳን ሔደን ወደ 12 ሰዓት ግድም እራት ተጋበዝን ። በዚያም ጭውውት ተደርጎ በየሸለቆው የሚታየውን የሰፈር እሳት በአድናቆት ከተመለከትን በኋላ ወደ መኝታችን ሔድን ። በማግሥቱ በ2 ሰዓት ተኩል ተጠርተን ከራስ መኰንንና ከአቶ(ፊታውራሪ) ሀብተ ጊዮርጊስ ጋር ስንነጋገር ሁለቱም አለቆች ንጉሡ ወዳሉበት ድንኳን እየሔዱ ንግግሩ 4 ሰዓት ሙሉ ፈጀ . . .በመጨረሻ ንጉሡን ለመሰናበት በሔድን ጊዜ በንጉሡ አጠገብ ከንጉሡ መቀመጫ ዝቅ ያለ ተደርጎላቸው የተቀመጡት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ ። ሰውነታቸው ወፍራም . . . ነው ። መልካቸው ግልጽና አስደሳች ፤ ዓይናቸው የብልህ የሆነው

የወሎው ራስ ሚካኤል ጢማቸውን ያሳደጉት ራስ መንገሻ (ዮሐንስም) ሰውነታቸው ጠንከር ፤ የራስ ጠጉራቸው ጢማቸው እጠር ያለው መልካቸው የሚያስፈራው ራስ አሉላ ነበሩ ።

ለመሔድ ተሰናብተን በየበቅሎቻችን ከወጣን በኋላ አንዳንድ ሹሞች በንጉሡ ቃል የምንነግራችሁ አለና ቆዩ እያሉ ሰበብ እየፈለጉ ሊያቆዩን አሰበው ነበር ። እኔ ግን ፤ በከንቱ ጊዜ መፍጀ መሆኑን ተረድቼ መንገዴን ቀጠልሁ ።...[1]

ማጆር ሳልሳ ፤ ይኸን ደብዳቤ ኢጣልያን አገር ላለው ወንድሙ ሲጽፍ ያየውን ቀላሉን ነገር እንጂ ስለእርቁ ጉዳይ የተነጋገረውን ፍሬ ነገር አይገልጽም ። ምክንያቱም የእርቅ ነገር በዚያን ጊዜ እንደ ምስጢር የሚታይ የመንግሥት ጉዳይ ስለሆነ ነገሩን ላለማባከን መሆኑ የታወቀ ነው ። ነገር ግን ማጆር ሳልሳ ላፄ ምኒልክ ወይም ለራስ መኰንን ያቀረበው ያው ከዚህ ቀደም ያነበብነው ነው ። ይኸንንም አሳብ ዐፄ ምኒልክ በፍጹም ሳይቀበሉት ቀርተው እንደ መለሱት ጄኔራል ባራቲዬሪም ፤ ማጆር ሳልሳም በኋላ ዘመን ባዘጋጁት ጽሑፍ ይገኛል ። በኛም በኩል ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በጻፉት መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ቀጥሎ ያለው ነው ።

...ከዚህ በኋላ ለኢጣልያ ወታደር ስንቅና ገንዘብ* ማጆር ሳልሳ ጸሐፊውንና ትንሽ አበሻ ብዙቅ ወታደር አስከትሎ መጣ ። የኛ ወታደር እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበረከተውን በሩቅ የሚታየውን ጦራችንን በዐይኑ አይቶ ለመሰለልና ለመገመት እንጂ ምናልባት ለእርቅ ብቻ አልመጣም ። ለርሱም በበጅሮንድ ባልቻ ሰፈር ድንኳን ተተከሎለት ነበር ። ሲመሽም ጠጅም የጮማ ከብት ዳቦ (እንጀራ) ለራት ተላከለትና በክብር አስተናገዱት ። የመጣለትም እቴጌ ጣይቱ "ይህ ሰው ለሰለላ እንጂ ለእርቅ የመጣ አይመስለኝም" ብለው ለባለሟሎቻቸው ተናግረው ነበር ። በማግሥቱ ባዳራሽ ሥጋጃ ተነጠፈ ። ዐፄ ምኒልክንም ፤ ራስ መንገሻ አቲከምን የሳይንትን ገዥ ፤ ራስ መኰንንና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን ጠሩዋቸው ። እነርሱም ከንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ከተቀበሉ በኋላ ማጆር ሳልሳ ወደሚገኝበት አዳራሽ ሒዱና የመጣበትን ምክንያት ጠየቁት ። እርሱም "ከዚህ ቀደም ባንዲራችን ተተክሎበት እስከነበረው እስከ አላጌ ድረስ ያለውን አገር ልቀቁልንና እንደገና ባንዲራችንን እንትከልበት" ብሎ ለጆሮም ለልብም ደስ የማያሰኝ መልስ ሰጠ ። ለንጉሠ ነገሥቱም ሊያቀርብ ያሰበው የዕርቅ አሳብ ይህ መሆኑን ስለገለጸ ፤ ይኸው ቃል ላፄ ምኒልክ ተነገረና እንደዚህ የሚል የንጉሠ ነገሥቱ መልስ ተሰጠው ። "እኔ የመጣሁት እናንተ የተከላችሁትን ባንዲራ ለመንቀልና ለመጣል ነውና ይኸን የመሰለውን የሰላም ውል አልቀበልም. . . በተረፈ ግፍ

1 Tomasso Salsa, E. Canevari E. Comisso, PP. 288- 290.

* የስንቅና የገንዘብ ኃላፊ የሆነውን ለማለት ነው ።



የማይወደው በእግዚአብሔር ተማምኜ በመጣችሁበት መንገድ እቀበላችኋለሁ ። በአገሬ በኢትዮጵያ ላይ የሮማ ሰንደቅ ዓላማ እንዲተከልበት አልፈቅድም ።"

ከዚህ በኋላ ፤ ማጆር ሳልሳ ተሰናብቶ ሲሔድ ራስ ቢትወደድ መንገሻ ወደ እቴጌ ጣይቱ እልፍኝ ገብተው ማጆር ሳልሳ የጠየቀውን ነገሩዋቸው ። በዚያን ጊዜ እቴጌዪቱ ፤ "የእሥራኤል አምላክ ሆይ ይኸን ግፍ ተመልከት ፤ በመድፉቸውና በጠበንጃቸው ተመክተው የፈቀዳቸውን ተናገሩ ፤ እኛም በክርስቶስ ኃይል እንፈራቸውም" ብለው በራስ ቢትወደድ ፊት ተናገሩ ።

ማጆር ሳልሳም ከንጉሡ ከተሰናበተ በኋላ ፤ ሰፈሩን እስኪወጣ ድረስ በበጅሮንድ ባልቻ እየተሸኘ ወጣና ወደ አለቃው ወደ ጄኔራል ባራቲዬሪ ተመለሰ ።[1]

ይህ በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ የሚገኘው እነጋገር ታሪኩ ባራቲዬሪም ሳልሳም ከጻፉት ጋር ይጋጠማል ። እንዲያውም ሳልሳ የእርቁን ቃል በራስ መኰንንና በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አማካይነት ብቻ መሆኑን ሲጽፍ ጸሐፌ ትእዛዝ ፤ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም መኖራቸውን በመግለጽ አብራርተውታል ። የሆነ ሆኖ ማጆር ሳልሳ ካፄ ምኒልክ የተቀበለውን ቃል ለጠቅላይ አዛዡ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ከአስረዳ በኋላ ፤ ጄኔራል ባራቲዬሪ ግራዝማች ዮሴፍ ያቆዩንን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጽፎ ለጦርነት ይዘጋጅ ጀመር ።

ትብጻህ ኀበ ጥቀ ልዑል ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተላከ ከጄኔራል ባራቲዬሪ የመንግሥት ታላቅ መኰንን የኤርትራ ግዛት ገዥ እግዚአብሔር ለጃንሆይ ሰላምና ጤና ይስጥልኝ ። ጃንሆይ ለመንግሥታችን የሰደዱትን ማጆር ሳልሳ ቃል በቃል ነገረኝ ። ጃንሆይ ይህ ይሁንልኝ ብለው የተናገሩትን መንግሥታችን ሊቀበለውና ነገሩንም በእንዲያው ሊያስረዝመው አይችልም ፤ ጃንሆይ የኔ መንግሥት የሚፈልገውን ውል ያውቃሉ ። የኢጣልያ መንግሥት ጃንሆይን ደስ ለማሰኘት የእርቁን ነገር ለማድረግ አንድ ሰው ሰደደ ። ተስፋም አድርጎ ነበረ ለኛና ለጃንሆይ አንድ የሚጠቅም ነገር ለማድረግ እንዲህ ከሆነ የእርቁ ነገር እንደቀረ ይቁጠሩት ። ከኛ እያንዳንዱ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ይሆንለታል ።[2]

በዚህ ደብዳቤ ፤ ጄኔራል ባራቲዬሪ የዕርቁን አሳብ ለዘለቄታው እንደ ዘጋው ያመለክታል ። በደብዳቤው መጨረሻ ፤ "እንዲህ ከሆነ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ምዕ.62 ገጽ 252-254

2 ከሞንዶን ቪዳዬ ዶሲዬ ፤ ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቁ. 82
Memoire d' Afrique, PP. 346 - 355

የዕርቁ ነገር እንደቀረ ይቈጠሩት ። ከኛ እያንዳንዱ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ይሆንለታል” ማለቱ ፤ ከጠረፍ እስከ አላጌ ድረስ ሙሉው የትግሬ ግዛት ካልተሰጠን ጦርነት ለማድረግ መዘጋጀታችንን ይወቁት ማለቱ ነው ። ለዚህ ደብዳቤ ዐፄ ምኒልክ መልስ መስጠታቸው በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ፤ በጄኔራል ባራቲዬሪም በሌላም መጽሐፍ አልተገኘም ። የሆነ ሆኖ ፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሁለቱም ወገኖች አሳብ ለአሳብ በግልጽ ስለ ተዋወቁ ከቀድሞ የበለጠ ለጦርነቱ ይዘጋጁ ዠመር ።[1]

1 Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca, PP. 633-636.





ዐፄ ምኒልክ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ
ከኔላ ቴራ ዴ ንጉሥ ከተባለው መጽሐፍ